CAHIERS DE LA SOCIÉTÉ ASIATIQUE

XI

CENT FABLES AMHARIQUES

MISES EN ÉCRIT
PAR
LE DABTARA KENFÉ

TRADUITES ET ANNOTÉES
PAR
MARTINO MARIO MORENO



PARIS
IMPRIMERIE NATIONALE

MDCCCCXLVII

LE DABTARĀ KĔNFĒ

natif du Godjam

a écrit toutes ces fables pour Monsieur MONDON-VIDAILHET

à Addis Ababa

au temps de l'Empereur Mĕnīlĕk, roi des rois d'Éthiopie.

ደብተራ ፡ ክንፌ ፡ በጐጃም ፡ የተወለደ ፡ እነዚህን ፡ ተረት ፡
ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሙሴ ፡ ምንዶን ፡ ጻፈ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡
ከተማ ፡ በዘመነ ፡ አጤ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ።

CENT FABLES AMHARIQUES

I

LE BOUC DU ROI ET LE RUSÉ DABTARĀ.

La première fable éthiopienne dit ainsi :

Un puissant roi régnait. Dans sa grande puissance, il pensa faire une chose qui n'avait jamais été faite par les rois précédents. Il possédait un bouc très beau et très gras. Ayant mis dans une corne des condiments menus et dans un étui un couteau, il les attacha au cou de ce bouc et l'envoya circuler sans berger, en disant : «Je verrai bien qui aura l'audace de ne pas me respecter». Les soldats qui étaient dans la ville, loin de penser à l'abattre, n'osaient même pas s'en approcher, comme s'il avait été un lion ou un léopard ou une autre bête féroce, disant : «Si quelqu'un le mange, le roi, nous dira : «C'est vous qui l'avez mangé». Et si quelqu'un s'en approchait, ils l'arrêtaient et le remettaient au souverain.

De cette façon, il circula longtemps avec ses condiments et son couteau, sans qu'aucun animal ne l'effrayât, ni qu'aucun homme ne le tuât. Voyant cela, le roi s'enorgueillit et disait : «Un roi comme moi n'a jamais régné par le passé, ni ne régnera dans l'avenir. Un roi craint et respecté comme moi n'existe pas». Il agissait ainsi parce qu'il pensait que personne n'oserait le défier. Dans le peuple, il n'y avait personne qui demandât à qui appartenait le bouc, tous le connaissaient.

A la fin, trois *dabtarā* pensèrent défier le roi. Un beau jour ils s'emparèrent du bouc royal, l'égorgèrent avec le couteau qu'il portait suspendu au cou, l'emportèrent dans une maison de campagne; le firent cuire avec les condiments qu'il avait attachés à son cou et le

dévorèrent, en disant grand bien. Après avoir mangé, pour autant que leur audace ne pouvait leur être utile[1], ils tirèrent de la peau râclée du bouc un parchemin et y écrivirent dessus : «O roi, le bouc a été très savoureux et très appétissant. Nous l'avons tué avec le couteau et mangé avec les condiments menus qu'il portait suspendus à son cou. Tu es curieux de savoir, ô roi, qui nous sommes? Coucou!»[2].

Ils jetèrent, pendant la nuit, l'écrit dans la cour, et se retirèrent dans leurs maisons.

Le roi fut absolument indigné non seulement qu'ils aient mangé son bouc, mais qu'ils l'aient raillé en lui faisant coucou. Raisonnant ainsi, il conclut : «Celui qui a fait ceci est certainement un *dabtarā*. Une autre personne n'aurait pas osé me défier». Ayant préparé un grand banquet, avec des boissons enivrantes à profusion, il y invita tous les *dabtarā*, sans en excepter un seul. Et tous les *dabtarā*, nul excepté, passèrent la journée en mangeant et en buvant.

A côté de chacun des *dabtarā*, il plaça un de ses hommes pour qu'il cherchât à savoir qui avait mangé le bouc. Un des trois *dabtarā* qui avait bu à l'excès, parla en disant : «C'est moi qui l'ai mangé avec mes compagnons». L'investigateur, triomphant, alla en référer au roi : «J'ai découvert celui qui l'a mangé». En attendant, tandis qu'on mangeait et qu'on buvait, le soir était venu.

Le roi ordonna qu'on entaillât l'oreille du *dabtarā* afin qu'il pût être reconnu par ce signe : «Qu'il reste cependant cette nuit avec ses compagnons; demain matin je l'interrogerai», et il fit condamner la porte du local dans lequel ils se tenaient.

Ce *dabtarā* auquel on avait entaillé l'oreille, en se tâtant, sentit son oreille coupée. «Qui sait ce que j'ai dit»! — pensa-t-il. Pour cette raison et afin de détruire le signe, il entailla les oreilles de tous ses collègues. Ayant fait cela, il se recoucha bien tranquillement. Le matin, le roi ordonna qu'on lui amenât d'urgence les *dabtarā*. Une fois qu'ils furent tous en sa présence, il constata que tous avaient l'oreille entaillée; et ainsi le roi n'eut pas le signe d'identification.

De cette façon le *dabtarā* qui avait confessé avoir mangé le bouc

(1) C'est-à-dire : «sans se préoccuper des conséquences — qui ne pouvaient être bonnes — de leur audace».

(2) *engällĕh* = «je ne le sais pas pour toi»; correspond à l'italien «indovinala grillo» (voir d'autre part Marcel Cohen, *Nouvelles études d'éthiopien méridional*, p. 151).

royal se sauva, grâce à son ingéniosité et à sa présence d'esprit, du châtiment du souverain, qui dit : « Combien devrais-je en punir? » et, étonné et diverti, il les laissa aller avec Dieu [1].

፩ኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተረት ፡ እንዲህ ፡ አለ

፩ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነገሠ ፤ ከገናንነቱም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ያላደረጉትን ፡ ነገር ፡ አሰበ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ። ፩ ያማረ ፡ እጅግ ፡ የሰባ ፡ የፍየል ፡ ሙክት ፡ ነበረው ። የብትን ፡ አዋዜ ፡ በቀንድ ፡ ቢላዋ ፡ በማኅደር ፡ ከቶ ፡ በዚያ ፡ ሙክት ፡ አንገት ፡ አሥሮ ፡ ያለረኛ ፡ ሰደደው ፡ የሚደፍረኝን ፡ አያለሁ ፡ ብሎ ። በከተማው ፡ ያሉ ፡ ሠራዊቱም ፡ እንኳንስ ፡ ያርዱትና ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እንደ ፡ ነምር ፡ እንደሚፈሩ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ አይቀርቡትም ፤ እኛን ፡ በላችሁት ፡ ይሉናል ፡ ቢሉ ፤ የቀረቡትም ፡ ሰዎች ፡ ወስደው ፡ ለንጉሥ ፡ ይሰጣሉ ። እንዲህ ፡ እየሆነ ፡ ከነኣዋዜው ፡ ከነቢላዋው ፡ ብዙኅ ፡ ቀን ፡ ኖረ ፡ አውሬ ፡ ሳያስደነግፀው ፡ ሰውም ፡ ሳያርደው ። ንጉሥም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ ትምክህትን ፡ አደረገ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞም ፡ አልነገሠ ፡ ከኔም ፡ በኋላ ፡ አይነግሥ ፤ እንደኔ ፡ የሚፈራ ፡ እንደኔ ፡ የከበረ ፡ የለም ፡ ብሎ ። ንጉሥ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ማድረጉ ፡ የሚደፍረኝ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ነው ። ከሕዝቡም ፡ ይህ ፡ ፍየል ፡ የማነው [2] ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቅ ፡ ፩ ሰው ፡ የለም ፤ ሁሉም ፡ አወቁት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፫ ቱ ፡ ደብተሮች ፡ ንጉሥን ፡ በድፍረት ፡ አሰቡት ፤ ከዕለታቱም ፡ ፩ ቀን ፡ ያን ፡ የንጉሥ ፡ ፍየል ፡ ከአንገቱ ፡ በታሠረው ፡ ቢላዋ ፡ አረዱት ፤ ከባዶ ፡ ቤት ፡ አግብተው ፡ ከአንገቱ ፡ በተገኘው [3] ፡ አዋዜ ፡ በሉት ፡ እያመሰገኑ ። ከበሉትም ፡ በኋላ ፡ ድፍረቱ ፡ የማይጠቅማቸው ፡ ቢሆን ፡ በዚያ ፡ ሙክት ፡ ብራና ፡ ፍቀው ፡ ጻፉበት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ሙክት ፡ እጅግ ፡ የጣፈጠ ፡ የጣመ ፡ ሆነልን ፤ ከአንገቱ ፡ በተገኘ ፡ ቢላዋ ፡ አርደን ፡ ከአንገቱ ፡

(1) Comparer J. I. Eadie, *An Amharic Reader,* Cambridge, University Press 1924, p. 717.
(2) የማነው = የማን ፡ ነው
(3) Remarquer la graphie.

በተገኘ ፡ ብትን ፡ አዋዜ ፡ በላነው ፡ ብለው ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እነማ
ናችኁ[1] ፡ ብለህ ፡ ትጠይቀን ፡ እንደሆን ፡ እንጃልህ ፡ የሚል ፡
ጽፈው ፡ ከአደባባዩ ፡ በጨለማ ፡ ጥለውት ፡ ወደቤታቸው ፡ ሄደው ፡
ተቀመጡ ። ንጉሥም ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ ተናደዱ ፡ እን
ዲህ ፡ እያሉ ፤ ያን ፡ ሙክት ፡ ከመብላታቸው ፡ እንጃልህ ፡ ብለው ፡
የሰደቡኝ ፡ አስቆጪኝ ፡ አሉ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡
መከሩ ፤ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ደብተራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡
አይደፍረኝም ፡ ብሎ ። ብዙ ፡ ድግሥ ፡ ደግሦ ፡ የሚያሰክር ፡ መጠ
ጥንም ፡ ፈልጎ ፡ ደብተራውን ፡ ሁሉ ፡ ፩ ልጅ ፡ ሳይቀር ፡ አስጠራ ፡
ደብተራውን ፡ ሁሉ[2] ። አንድ ፡ ልጅ ፡ ሳይቀር ፡ ደብተሮችም ፡
ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ዋሉ ። በየራሳቸው ፡ ከርሱ ፡ ሰው ፡ አቆመ ፡
የንጉሥን ፡ ፍየል ፡ የበላው ፡ ማነው ፡ እያሉ ፡ ይመረምሯቸው ፡
ዘንድ ። ከነዚያ ፡ ከ፫ቱ ፡ ፩ዱም ፡ ደብተራ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኔ ፡
ከወንድሞቸ ፡ ጋራ ፡ በላነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረ[3] ፡ ከመጠጥ ፡ ብዛት ፡
የተነሣ ። ያም ፡ የመረመረ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ሄዶ ፡ ለንጉሥ ፡
ነገረው ፤ የበላውን ፡ አገኘሁት ፡ ብሎ ። ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ስለ ፡
ዋሉ ፡ መሸ ፤ ንጉሥም ፡ ምልክት ፡ ጆሮውን ፡ አስቆርጠ ፡ ከወንድ
ሞቹ ፡ ጋራ ፡ ይደር ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ በነግህ[4] ፡ እመረምረዋለሁ ፡ ብሎ
ያሉበትንም ፡ ቤት ፡ አዘዘ ፡ ዝጉ ፡ ብሎ ። ያም ፡ ጆሮውን ፡ የተቆ
ረጠ ፡ ደብተራ ፡ ቢዳስስ ፡ ተቆርጠ ፡ አገኘው ፤ ምን ፡ ተናግሬ ፡
ይሆን ፡ ብሎ ፡ ወንድሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ዦሯቸውን ፡ ቆረጠ ፡ ምልክት ፡
ለማጥፋት ፤ ይህንም ፡ አድርጎ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አደረ ። በነጋውም ፡
በችከላ ፡ ቃል ፡ አምጡልኝ ፡ ደብተሮችን ፡ አለ ። እለዚያም ፡ ሁሉ ፡
ቢመጡ ፡ ጆሮአቸውን ፡ የተቆረጠ ፡ ሆኖ ፡ አየ ። በንጉሥ ፡ ምል
ክት ፡ ጠፋበት ። ያ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የንጉሥን ፡ ፍየል ፡ የበላሁ ፡ ብሎ ፡
የተናገረ ፡ ደብተራ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ በጥበቡና ፡ በምክሩ ፡ ከንጉሥ ፡
ቅጣት ፡ ዳነ ፤ ንጉሥም ፡ ስንቱን ፡ እቀጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሁሉንም ፡ ስቆ ፡
ተደንቆ ፡ ተዋቸው ።

(1) እነማናችኁ = እነማን ፡ ናችሁ

(2) ደብተራውን ፡ ሁሉ plutôt qu'une dittographie est une répétition emphatique.

(3) ተናገረ : le manuscrit porte ተናገሬ

(4) Noter la forme archaïque.

II

LE LÉOPARD, LA CHÈVRE ET LE CHOU[1].

Un homme dit à son compagnon : «Mon ami, je veux te demander une chose; voyons si tu la sais». L'autre répondit : «Qu'est-ce donc que je ne sais pas? Interroge-moi». Et le premier de dire : «Fais-moi traverser un cours d'eau, un par un, à un chou, à une chèvre, et à uu léopard; tous les trois en trois fois».

«Je ferai passer d'abord le léopard.»

Et l'interrogateur : «Et alors la chèvre te mangera le chou».

«Je laisserai le léopard et le chou de l'autre côté, je ferai passer la chèvre, puis je transporterai le chou.»

«Mais la chèvre te mangera le chou. Si ensuite tu veux faire traverser le léopard avant le chou, il te mangera la chèvre.»

Embarrassé, son compagnon lui dit : «Je ne devine pas; toi, dis-le moi».

«Puisque tu ne devines pas, voici ce qu'il en est. Je ferai traverser avant tout la chèvre, ensuite le chou; je ramènerai en arrière la chèvre et je ferai traverser le léopard; en dernier lieu, je ferai traverser la chèvre.»

L'homme demeura étonné.

፪ ተኛ ፡ ተረት

፩ ድ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ ወንድሜ ፡ ታውቅልኝ ፡ እንደሆነ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ አለው ፡ ወንድሙን ። እርሱም ፤ እኔ ፡ የማላውቀው ፡ ምን ፡ አለ ፤ ጠይቀኝ ፡ አለው ። እርሱም ፤ ጎመንን ፡ ፍየልን ፡ ነብርን ፡ በየራሳቸው ፡ ፩ድ ፡ አንዳቸውን ፡ ወሀውን ፡ አሻግርልኝ ፡ አለው ፤ ፫ ቱን ፡ ፫ ት ፡ ጊዜ ። በፊተ ፡ ነብርን ፡ አሻግራለሁ ፡ ቢለው ፡ ጠያቂ ፤ ጎመኑን ፡ ፍየል ፡ ይበላብሃል ፡ አለው ። ፍየልን ፡ አሻግራለሁ ፡ ቢለው ፡ ነብርንና ፡ ጎመንን ፡ ትቸ[1] ከወዲህ ፤ አሁንም ፡ ቀኖዬ ፡ ጎመንን ፡ እወስዳለሁ ፡ ቢል ፡ ፍየል ፡ ጎመንን ፡ ይበላብሃል ። ጎመንን ፡ ትቸ ፡ ነብርን ፡ አሻግራለሁ ፡ ብትል ፡ ፍየልን ፡ ይበላብሃል ፡ እያለ ፡

(1) Récit bien connu dans les recueils de fables d'Europe.

ቢያስቸግረው ፤ ጠፋኝ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ከጠፋህስ ፡ እንዲህ ፡ እን
ዲህ ፡ ነው ፡ አለና ፡ ነገረው ፤ በፊት ፡ ፍየልን ፡ ቀጥየ ፡ ጎመንን ፡ አሻ
ግሬ ፡ ፍየልን ፡ መልሼ ፡ ነብርን ፡ አሻግራለሁ ፤ በመጨረሻ ፡ ፍየልን ፡
አሻግራለሁ ፡ አለ ። ያም ፡ ሰው ፡ አደነቀ ።

III

UN MARIAGE ILLÉGITIME CONJURÉ.

Un habitant du Godjam allait en mission au Bégamder. Un habitant du Bégamder allait en mission au Godjam. Tous deux se rencontrèrent sur le Nil Bleu et se demandèrent l'un à l'autre : « Où vas-tu? ». Le Godjamite dit à l'habitant du Bégamder : « A tel endroit habite ma mère. Repose-toi chez elle ». Il lui donna les indications nécessaires et le congédia.

L'habitant du Bégamder, à son tour, dit au Godjamite : « A tel endroit habite ma mère. Repose-toi chez elle ». Et il lui donna les indications nécessaires.

Le Godjamite eut de la mère de l'envoyé du Bégamder un fils; l'habitant du Bégamder eut de la mère du Godjamite une fille : tous deux furent pères! Les deux enfants grandirent. Ceux qui n'étaient pas au courant émirent cet avis : « Lui est du Bégamder; elle est une Godjamite. Il n'y a pas d'empêchement entre eux. Ils peuvent s'épouser ». Mais les hommes qui connaissaient la chose émirent cet avis : « Ils ne peuvent pas s'épouser. Ils sont parents. Ils ne peuvent pas s'épouser ».

— Comment sont-ils parents? L'un est Godjamite; l'autre est du Bégamder. Quelle parenté y a-t-il?

— Par rapport à la jeune fille; le jeune homme est le fils de son frère, répondirent-ils; et les autres comprirent et se convainquirent [1].

፫ ተኛ ፡ ተረት

፩ የጎጃም ፡ ሰው ፡ ተልኮ ፡ ወደ ፡ ቤገምድር ፡ ሲሄድ ፡ ፩ የቤገምድር ፡
ሰው ፡ ተልኮ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሲሄድ ፡ ፪ ቱም ፡ ዓባይ ፡ ወንዝ ፡ ተገ

(1) En fait la jeune fille était la sœur utérine de l'envoyé godjamite, père du jeune homme.

ኖኙ ። ወደዬት ፡ ትሄዳለህ ፡ አሉና ፡ ተጠያየቁ ። ያ ፡ ጐጃሜ ፡ ለቤገም ድሩ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፤ ከዚህ ፡ ሰፍራ ፡ እናቴ ፡ አለችና ፡ ከዚያ ፡ አርፈህ ፡ ሰንብት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጥቶ ፡ ሰደደው ፤ ይህም ፡ ቤገምድሬ ፡ ለጐጃሜ ፡ መልከተኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ከዚህ ፡ ሥፍራ ፡ እናቴ ፡ አለች ፤ ከዚያ ፡ አርፈህ ፡ ሰንብት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጠው ። ጐጃሜው ፡ ከቤገምድሬው ፡ መልከተኛ ፡ እናት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ። ቤገምድሬውም ፡ ከጐጃሜው ፡ መልከተኛ ፡ እናት ፡ ወለደ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፤ ፪ ቱም ፡ ወለዱ ። ተወልደው ፡ አደጉ ፡ ሁለቱም ። ያላ ወቁ ፡ ሰዎች ፡ ያ ፡ ቤገምድሬ ፡ ነው ፡ ይህች ፡ ጐጃሜ ፡ ናት ፤ ምን ፡ ይከለከላቸዋል ፡ ይጋቡ ፡ አሉና ፡ በየኑ ። ብልሆች ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ አይ ጋቡ ፤ ዘመዶች ፡ ናቸውና ፡ አይጋቡ ፡ ብለው ፡ በየኑ ። እንደ ፡ ምን ፡ ዘመድ ፤ ያች ፡ ጐጃሜ ፡ ይህ ፡ ቤገምድሬ ፡ ምን ፡ ዘመድነት ፡ አላቸው ፡ ቢሉ ፤ ለሴቷ ፡ ልጅ ፡ ወንዱ ፡ ልጅ ፡ የወንድ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አሉ ። እነዚያም ፡ አወቁ ፡ ተረዱ ።

IV

LES TROIS PHILOSOPHES.

Un caravanier perdit en chemin une jument privée d'un œil, avec tout son chargement. Tandis qu'il était en train de la chercher il rencontra trois philosophes mais il ne les reconnut pas (comme tels). Il avait plu et l'heure était avancée. «J'ai perdu une bête de somme», leur dit-il.

«Elle était privée de l'œil gauche?» demanda le premier philosophe.

«Oui», répondit-il.

«Elle portait un chargement pesant?» demanda le deuxième philosophe.

«Oui, répondit-il, le chargement lui pesait sur le dos».

«Avait-elle l'échine blessée?» demanda le troisième philosophe.

«Oui, elle avait le dos blessé», répondit le caravanier. A chaque demande, il répondit : oui.

Après cela, il leur dit : «Où est-elle?».

«Nous ne l'avons pas vue», répondirent-ils.

Alors le caravanier dit : «C'est vous qui l'avez prise»; et il les conduisit au roi.

Le roi dit : «Exposez-moi votre cas».

Le caravanier dit : «O roi, j'ai interrogé les trois et ils m'ont répondu : «Tu as perdu une bête de somme de telle et telle façon».

«C'est vrai. Nous lui avons parlé ainsi», reconnurent ceux-ci.

Le roi les ayant pris l'un après l'autre pour les interroger; le premier philosophe dit : «J'ai dit qu'elle est privée d'un œil, parce que le chemin parcouru par elle s'écarte de la route, allant un peu à droite et un peu à gauche; voilà pourquoi j'ai dit qu'elle est privée d'un œil».

Le deuxième philosophe dit : «J'ai dit que son chargement lui pesait sur le dos, parce que son sabot apparaissait enfoncé dans le sol; voilà pourquoi j'ai dit que son chargement lui pesait sur le dos».

Le troisième philosophe dit : «J'ai dit qu'elle avait le dos blessé, parce que j'ai vu les insectes fourmiller autour du sang et du pus qui coulaient, à cause de l'inflammation produite par la charge, dans tous les endroits où elle s'était arrêtée. C'est pourquoi j'ai dit qu'elle avait le dos blessé».

«Mais la bête elle-même, personne de nous ne l'a vue», ajoutèrent-ils en chœur.

Émerveillé par leur sagesse, le roi dit : «Ceux-ci doivent rester à mon service» et il accorda aux trois philosophes en rétribution un repas composé de deux pains et de deux bouteilles d'hydromel pour chacun, en sus de la viande.

Une autre fois, les philosophes s'exprimèrent ainsi :

Le premier dit : «Le roi est un rustre parvenu [1]».

Le second dit : «Le miel avec lequel est fait l'hydromel est gâté».

Le troisième dit : «La viande qui nous a été servie est celle d'une bête sauvage».

Entendant cela, le roi les fit appeler, se demandant : «Qui donc leur a dit que je suis né d'une esclave ?».

Le premier philosophe dit : «J'ai dit que tu es un rustre parvenu parce que tu as ordonné que notre *dĕrgo* [2] fût composé identiquement pour les trois de deux bouteilles d'hydromel et de viande en quantité égale pour tous. Voilà pourquoi j'ai dit que tu es un rustre parvenu».

[1] *bālaǧu* équivaut ordinairement à «ouvrier».

[2] On appelle *dĕrgo* la nourriture allouée à une personne à charge du Trésor public ou d'une collectivité.

Le deuxième philosophe dit : «J'ai dit que le miel était une marchandise gâtée et avancée, parce que l'hydromel fait avec du miel gâté est imbuvable et boueux».

Le troisième philosophe parla ainsi : «J'ai dit que la viande était celle d'une bête sauvage, parce que quand elle provient d'une bête sauvage, la viande se transforme en eau dans la bouche, et en outre sent mauvais. Voilà pourquoi j'ai dit que c'était de la viande d'un animal sauvage».

Le roi fit appeler celui qui était chargé de l'hydromel et lui demanda : «De quelle provenance était le miel avec lequel tu as fait cet hydromel ?»

Le préposé à l'hydromel répondit : «O roi, étant venu à manquer temporairement de miel récolté dans les mois de *ḫĕdār* et de *taḫsās* j'ai fait l'hydromel avec du miel vieilli et diminué récolté dans les mois de *gĕnbot* et de *sanē*».

Ensuite le roi fit appeler le préposé à la viande et lui demanda : «La viande que tu as donnée hier aux personnes ayant droit au plat de service, de quelles brebis provenait-elle?». Le préposé à la viande répondit au roi en ces termes : «O roi, n'ayant pas de brebis à ma disposition et ayant sous la main une brebis née d'une loutre [1], je l'ai égorgée et je l'ai accommodée comme plat de service».

Quant à la phrase dite par le troisième philosophe, par celui qui avait dit : «C'est un rustre parvenu», c'était une chose que le roi seulement savait (et c'est la raison pour laquelle il n'eut pas besoin de demander d'autres explications).

Le roi resta émerveillé de la perspicacité des trois et leur donna des charges à sa cour. Le philosophe qui avait dit : «C'est de la viande sauvage», il le nomma préposé à la viande; celui qui avait dit : «C'est du miel vieilli», il le nomma préposé à l'hydromel et le troisième philosophe qui avait dit que le roi était un rustre parvenu, il le fit surintendant général de sa maison [2].

፬ ተኛ ፡ ተረት

፩ ነጋዴ ፡ መንገድ ፡ በሄደበት ፡ ፩ ድ ፡ ዓይኗ ፡ የጠፋ ፡ ፈረስ ፡ ከነጭነቷ ፡ ጠፋችበት ። ያ ፡ ነጋዴ ፡ ሲፈልግ ፡ ሰስት ፡ ፈላስፎች ፡ አገኘ ።

(1) Manière comique de dire «ayant une loutre sous la main».

(2) La première partie de ce récit est répandue dans la littérature arabe, comme exemple de l'habileté des Bédouins dans l'interprétation des traces.

እርሱ ፡ ግን ፡ አላወቃቸው ፡ ጊዜውም ፡ ዝናም ፡ ዘንሞ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ከብት ፡ ጠፍቶብኝ ፡ አላቸው ። ፩ኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ዕውር ፡ ናት ፡ ግራ ፡ ዓይኗን ፡ ቢለው ፤ አዎን ፡ ናት ፡ አለ ። ፪ተኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ጭነት ፡ የከበዳት ፡ ናት ፡ አለው ፤ አዎን ፡ ጭነት ፡ ከብዷታል ፡ አለ ። ፫ተኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ገጣባ ፡ ናት ፡ አለው ፤ አዎን ፡ ገጣባ ፡ ናት ፡ አለ ፡ ነጋዴ ፤ የሁሉንም ፡ ቃል ፡ አዎን ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደሄት ፡ ናት ፡ አላቸው ፤ አላየንም ፡ አሉት ። ያ ፡ ነጋዴም ፡ ወስዳችኋል ፡ ብሎ ፡ ወሰዳቸው ፡ ከንጉሥ ። ንጉሥም ፡ ነገራችሁን ፡ አስሙ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ነጋዴ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ፫ቱን ፡ ጠየቅኋቸው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከብት ፡ ጠፍቶብሐል[1] ፡ አሉኝ ፡ አለ ፤ እነዚያም ፡ አዎን ፡ ነገርነው ፡ አሉ ። ንጉሥም ፡ ፩ድ ፡ አንድ ፡ ቢመረምራቸው ፡ ፩ኛው ፡ ፈላስፋ ፤ ዕውር ፡ ናት ፡ ያልሁ ፡ የረገጠችው ፡ ቀኝም ፡ ግራም ፡ ሆኖ ፡ ያለጎደና ፡ ሄዳ ፡ አየሁ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ዕውር ፡ ናት ፡ አልሁት ፡ አለ ። ፪ተኛው ፡ ፈላስፋም ፡ ጭነት ፡ ከብዷታል ፡ ያልሁ ፡ ሰኰናዋ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ አየሁ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጭነት ፡ ከብዷታል ፡ አልሁ ፡ አለ ። ፫ተኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ገጣባ ፡ ናት ፡ ያልሁ ፡ ጭነት ፡ እየጋመባት ፡ በያረፈችበት ፡ ስፍራ ፡ የፈሰሰውን ፡ ደምና ፡ እዥ ፡ ተሐዋስያን[2] ፡ እየወረሩት ፡ አየሁ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ገጣባ ፡ ናት ፡ አልሁ ፤ መልኳን ፡ ግን ፡ ፫ታችንም ፡ አላየናት ፡ ቢሉት ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ጥበባቸውን ፡ አድንቆ ፡ እነዚህስ ፡ ለመንግሥት ፡ አሽከሮች ፡ ይሆኑናል ፡ ብሎ ፡ ድርጎ ፡ አወጣላቸው ፤ ለ፫ቱ ፡ ፈላስፋ ፡ ፲፪እንጀራ ፡ ፲፪ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ ሥጋ ፡ ጨምሮ ፡ ዳረጋቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፪ተኛ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤ ፩ኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ንጉሡ ፡ ባለጌ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ፪ተኛ ፡ ፈላስፋ ፡ ዕባሽ ፡ ማር ፡ ነው ፡ አለ ፤ ፫ተኛው ፡ ይህ ፡ የመጣልን ፡ ሥጋ ፡ ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ አለ ። ይህንም ፡ ንጉሥ ፡ ሰምቶ ፡ ፫ቱንም ፡ አስጠራቸው ፡ ከገረድ ፡ መወለዴን ፡ ማን ፡ ነገራቸው ፡ ብሎ ። ፩ኛው ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ባለጌ ፡ ያልሁት ፡ ለ፫ታችን ፡ ድርጎ ፡ ትክክል ፡ ፲፪ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ ፲፪እንጀራ ፡ ሥጋውም ፡ ትክክል ፡ ስለሆነ ፡ ባለጌ ፡ ነው ፡ አልሁ ፡ አለ ። ፪ተኛው ፡

(1) ጠፍቶብሐል = ጠፍቶብሃል

(2) ተሐዋስያን (ተሐዋሲያን) «insectes, animaux qui rampent», mot guèze. Le manuscrit a ተሐዋሳያን

ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ዕባሽ ፡ ኢላቂ ፡ ማር ፡ ነው ፡ ያልሁ ፡ ጠጁን ፤ ዕባሹን ፡ መዓር[1] ፡ ጠጅ ፡ ቢያደርጉት ፡ ከዳ ፡ ከዳ ፡ አፈር ፡ አፈር ፡ ይላል ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ዕባሽ ፡ ማር ፡ ነው ፡ አልሁ ፡ አለ ። ፩ተኛው ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ያልሁ ፡ ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ወሀ ፡ ይሆናል ፡ በአፍ ፡ ፪ተኛም ፡ ደግሞ ፡ ይከረፋል ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ አልሁ ፡ አለ ። ንጉሥም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጠጅ ፡ መልከኛውን ፡ ጠየቀው ፡ ይህን ፡ ጠጅ ፡ የጣልህ ፡ ከወደዬት ፡ የመጣ ፡ ማር ፡ ነው ፡ ብሎ ። የጠጅ ፡ መልከኛም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በጊዜው ፡ በኅዳር ፡ በታኅሣሥ ፡ የተቆረጠው ፡ መዓር ፡ ሲያልቅብኝ ፡ በግንቦትና ፡ በሰኔ ፡ የተቆረጠ ፡ ዕባሽ ፡ ዕላቂ ፡ መዓር ፡ ነበር ፤ የርሱ ፡ ጠጅ ፡ ነው ፡ አለ ። ፪ተኛ ፡ የሥጋ ፡ መልከኛውን ፡ አስጠርቶ ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትላንት ፡ ለባለድርጎ ፡ የሰጠኸው ፡ ሥጋ ፡ ከወደዬት ፡ የመጣ ፡ በግ ፡ ነው ፡ ብሎ ። የሥጋ ፡ መልከኛውም ፡ ለንጉሥ ፡ ነገረ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የቀረበው ፡ በግ ፡ ቢያልቅብኝ ፡ ከአቁስጣ ፡ የተወለደ ፡ በግዕ[2] ፡ ነበር ፤ ያን ፡ አርጀ ፡ ለድርጎኛ ፡ ሰጠሁ ፡ አለ ። የ፫ተኛውን ፡ ፈላስፋ ፡ ባለጌ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ንጉሥ ፡ ብቻውን ፡ አወቀ ። የ፫ቱንም ፡ ነገር ፡ አደነቀ ፡ በቤቱም ፡ ሹመት ፡ ሰጣቸው ። ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ፈላስፋ ፡ የሥጋ ፡ መልከኛ ፡ አደረገው ፤ ፪ተኛውን ፡ ፈላስፋ ፡ ዕባሽ ፡ ማር ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ የጠጅ ፡ መልከኛ ፡ አደረገው ፤ ፫ተኛውን ፡ ፈላስፋ ፡ ንጉሡን ፡ ባለጌ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ምሉዕ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ አደረገው ።

V

LE RICHARD MODESTE.

Il y avait un homme très riche. Aucunement enorgueilli par sa richesse, il se rendit à son champ, modestement vêtu, travailla la terre toute la journée et quand le soir fut venu, il retourna à la maison en portant sur ses épaules l'outil avec lequel il avait travaillé tout le jour et sans faire attention qu'il était tout couvert de boue. Les visi-

(1) Noter les graphies différentes : መዓር et ማር

(2) Noter les graphies በግዕ et በግ

teurs qui étaient en train d'attendre le maître de la maison ne se levèrent pas à son passage et ne le saluèrent pas. Le riche, entré chez lui, se lava, endossa un vêtement convenable, laissa dans la maison son habit de travail et sortit sur la porte pour inspecter le bétail. Ceux qui ne s'étaient pas levés d'abord à son passage et étaient restés assis, en le voyant décemment vêtu, se hâtèrent de se lever et de le saluer.

«Je suis celui de tout à l'heure, saluez mon habit!» leur dit-il.

Les visiteurs dirent : «Vraiment nous avons été des ignorants! Nous ne nous sommes pas levés devant le maître de la maison et nous nous sommes levés devant l'habit». Ils avaient, en fait, agi sans discernement.

፭ተኛ ፡ ተረት

፩ሰው ፡ ዕጅግ ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር ፡ በባለጸግነቱም ፡ አይከራም ፡ ነበርና ፡ ትንሽ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ወደርሻው ፡ ሄዶ ፡ ሲያርስ ፡ ዋለ ። በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ዕቃ ፡ ሲያርስበት ፡ የዋለውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሰውነቱን ፡ ሳይፈቅድ ፡ ጭቃ ፡ እንደሆነ ፡ ወደቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ባለቤቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ይመጣልናል ፡ ብለው ፡ እንግዶች ፡ ሳይነሱለት ፡ ኖርም ፡ ሰይሉት ፡ ቀሩ ። ያበለጸጋ [1] ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ሰውነቱን ፡ ታጥቦ ፡ ደኅና ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ የሥራ ፡ ልብሱን ፡ ከቤት ፡ አኑሮ ፡ ከብት ፡ ለማየት ፡ ወደደጅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሳይነሱለት ፡ ተቀምጠው ፡ ያዩት ፡ ሰዎች ፡ ለብሶ ፡ ከብሮ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ እየተነሱ ፡ ደንግፀው ፡ ኖር ፡ አሉት ። እኔ ፡ የቅድሙ ፡ ነኝ ፤ ልብሴን ፡ ኖር ፡ በሉት ፡ አላቸው ፤ እንግዶችም ፡ አለማወቃችን ፡ ለባለቤቱ ፡ ሳንነሳ ፡ ለልብስ ፡ ተነሳን ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፤ አላዋቆች ፡ ስለሆኑ ።

VI

LE RAT AFFAMÉ.

Un rat, n'ayant pas de quoi manger, tourmenté par la faim, se rendit au marché pour acheter des céréales; mais le marché en était

[1] Dans le manuscrit le démonstratif *yā* est presque toujours, comme ici, attaché au substantif auquel il se rapporte.

dépourvu. Tandis qu'il s'en retournait les mains vides, il rencontra un homme qui lui demanda : «Où vas-tu ?» — «Je suis allé au marché acheter des céréales, mais on en manquait et c'est pourquoi je suis revenu sans nourriture pour la journée.»

«En passant sous le nez du chat on trouve l'abondance : on y vend les céréales à foison», lui dit l'homme.

«Pourquoi te moques-tu de moi ? La belle indication que tu me donnes!»[1], dit le pauvre rat.

፮ተኛ ፡ ተረት

፩ዲት ፡ አይጥ ፡ ለምትቀምሰው ፡ አጥታ ፡ እጅግ ፡ ተርባ ፡ ደክማ ፡ ሳለች ፡ እህል ፡ ልትሸምት ፡ ወደገቢያ ፡ ብትወጣ ፤ ገቢያ ፡ ተርቦ ፡ አጥታ ፡ ስትመለስ ፡ ፩ ሰው ፡ አገኛት ፡፡ የት ፡ ትሄጃለሽ ፡ አላት ፡፡ እህል ፡ ልሸምት ፡ ወደገቢያ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ፤ ተራበና ፡ የዕለት ፡ ዕራት ፡ አጥቼ ፡ ተመለስሁ ፡ አለችው ፡፡ ያ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤ በድመት ፡ አፍንጫ ፡ አልፎ ፡ ያለመጠን ፡ ጸግበ ፡ ጫን ፡ ጫን ፡ ይሸመታል ፡ ቢላት ፤ ለምን ፡ ትቀልድብኛለህ ፡ በሄት ፡ አልፎ ፡ አለችው[2] ፡፡

VII

LE PAUVRE DÉMENT ET LES RICHES.

Il y avait un homme à qui la raison manquait : c'était un dément. Il avait faim, il était dans la misère, mais il ne se demandait pas : «Que mettrai-je comme habits ? Que mangerai-je ?». Il ne savait pas ce que signifiait le mot «maison». Il se nourrissait de ce que lui fournissait la charité publique.

Celui qui est pauvre est le dernier des hommes. Un jour, quelques

(1) Littéralement : «en passant par où ?».

(2) Noter l'expression ጫን ፡ ጫን ፡ ይሸመታል, ጫን est une mesure pour le blé. Voir Guidi, col. 850, Baeteman, col. 233.

riches, pour se moquer de lui, lui demandèrent : «Un tel, jeûnes-tu le vendredi et le mercredi ?».

«Pour l'heure, donnez-moi : puis le temps (du jeûne) viendra», répondit-il avec humilité.

Il répondit ainsi, parce que, ce jour-là, il n'avait pas de quoi souper.

En entendant les paroles du pauvre, les riches qui l'avaient raillé eurent pitié de lui et, confus, dirent : «Nous aussi, si Dieu ne nous donnait pas, nous serions comme lui».

፯ተኛ ፡ ተረት

፩ሰው ፡ ነበር ፤ ልቡን ፡ ያጣ ፡ ዕብድ ፡ ነበር ፡ እጅግ ፡ ተርበ ፡ ተቸግሮ ፡ ይኖራል ፤ ምን ፡ ዕለብሰ ፡ ምን ፡ እበላ ፡ አይልም ፡ ነበር ፤ ቤትም ፡ የሚሉትን ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፤ የሰው ፡ እጅ ፡ እየጠበቀ ፡ ሲመገብ ፡ ኖረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደሀ ፡ ከሆነ ፡ የሰው ፡ ታናሽ ፡ ነውና ፡ ባለጸጎች ፡ ሲቀልዱበት ፤ እገሌ ፡ ዓርብ ፡ ረቡዕን ፡ ትጾማለህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እርሱ ፡ ግን ፡ በትሕትና ፡ ቃል ፡ መለሰላቸው ፡ እስኪሰጡኝ [1] ፡ ጊዜው ፡ ይደርሳል ፡ አለ ። ለራሱ ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ አልነበረውምና ፡ ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ኋላ ፡ ግን ፡ የቀለዱበት ፡ ባለጸጎች ፡ የደኃውን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ አዘኑለት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ እኛም ፡ እንጂ ፡ ጌታ ፡ ካልሰጠን ፡ እንደርሱ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ተደነቁ ።

VIII

LE CÉLIBATAIRE ET LE PHILOSOPHE.

Dans un pays habitait un homme qui, ne sachant pas économiser l'argent qu'il gagnait, se trouvait dans la gêne. Ayant rencontré un philosophe, il lui dit : «Frère, donne-moi un conseil. Quand je trouve de l'argent, celui-ci ne se laisse pas accumuler. Conseille-moi».

Le philosophe lui conseilla de prendre femme. L'homme lui répondit : «Eh quoi ? Je n'ai pas de quoi manger ni de quoi me vêtir, et tu penses que je réussirai à trouver des habits et de la nourriture

[1] እስኪሰጡኝ = እስኪ ፡ ይሰጡኝ

aussi pour ma femme. Ce conseil que tu me donnes me semble mauvais et pas très juste።.

Ce philosophe avait une importante récolte (d'orge) à moissonner : «Coupe l'orge avec la main droite, prends-en en abondance, autant que tu le désires, sans te servir de la main gauche, et apporte-le moi», dit-il au pauvre. Le pauvre entra dans le champ et commença à en couper. Au bout d'une heure, le riche (philosophe) l'appela. L'autre se présenta à lui avec une petite quantité d'épis d'orge.

— Comment donc en as-tu récolté si peu jusqu'ici ?

«Au fur et à mesure que je coupais le dernier épi, ceux que j'avais coupés auparavant tombaient à terre, parce que je me servais de la main droite», répondit le pauvre.

Alors le riche parla au pauvre en ces termes : «Coupe avec la droite, tiens avec la gauche et apporte-moi les épis d'orge».

Le pauvre entra dans le champ du riche et coupant avec la droite et tenant avec la gauche, il mit aussitôt ensemble de quoi se satisfaire.

Le philosophe dit alors au pauvre :

«As-tu vu ? Retiens-le dans ton esprit. La main droite et le mari sont une chose; la main gauche et la femme sont une même chose pour tenir. De même que tu as tenu (l'orge) avec la gauche de même ton épouse tiendra pour toi et l'argent s'accumulera. De même qu'en coupant et en tenant d'une seule main tu n'as pas réussi à accumuler, de même un homme ne peut rien sans son épouse. (Si tu ne réussis pas à économiser) c'est parce que tu es seul.»

Le pauvre l'admit, prit femme et avant que ne se terminât l'année, il fut en possession d'une grosse fortune.

፳ተኛ ፡ ተረት

፩ ሰው ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ሲኖር ፡ ገንዘብ ፡ እያገኘ ፡ አይጠራቅም[1] ፤ በችግር ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ፩ድ ፡ ፈላስፋ ፡ አገኘና ፡ ወንድሜ፡ ምከረኝ ፡ ገንዘብ ፡ አገኛለሁ ፡ አልሰበሰብ ፡ አለኝ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ምከረኝ ፡ አለ ። ያም ፡ ፈላስፋ ፡ ሲመክረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከረው ። ምሽት ፡ አግባ ፡ አለው ። ያም ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኔ ፡ እበላውና ፡ አላብሰው ፡ ሳጣ ፡ ደግሞ ፡ የምሽት ፡ ልብስና ፡ ቀለብ ፡ ታገኛለህ ፡ ትለኛለህ ፤ ይህስ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቀና ፡ ምክር ፡

(1) Noter la forme. Peut-être አያጠራትም

መስሎ ፡ አልታየኝም ፡ አለው ። ያም ፡ ፈላስፋ ፡ እጅግ ፡ ብዙኅ ፡ አድርጎ ፡ የሽት ፡ አዝመራ ፡ አለው ፤ ከዚህ ፡ ገብስ ፡ ያን ፡ ደኃ ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ቈርጠህ ፡ በግራ ፡ እጅህ ፡ ስትቀበል ፡ የሚያጠግብህን ፡ ያህል ፡ በብዙኅ ፡ አምጣ ፡ አለው ። ያም ፡ ደሀ ፡ ከርሻው ፡ ገብቶ ፡ ይቈርጥ ፡ ጀመረ ። ያ ፡ ባለጸጋ ፡ ፩ ድ ፡ ሰዓት ፡ ቈይቶ ፡ ጠራው ፤ ጥዊት ፡ ይዞ ፡ መጣ ፡ ገብስ ፡ እሸት ። ምነው ፡ እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ጥቂቱን ፡ ይዘህ ፡ መጣህ ፡ አለው ። ያ ፡ ደሀ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፤ የኋለኛውን ፡ እሸት ፡ ስቈርጥ ፡ የቈረጥሁት ፡ እየወደቀብኝ ፡ በአንድ ፡ በቀኝ ፡ እጄ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ አለ ። ፪ ተኛ ፡ ባለጸጋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ለደሀው ፡ ሲነግር ፤ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ እየቈረጥህ ፡ በግራ ፡ እጅህ ፡ እየተቀበልህ ፡ ገብስ ፡ እሸት ፡ አምጣ ፡ አለው ፤ ያም ፡ ድሀ ፡ ከባለጸጋው ፡ እርሻ ፡ ገብቶ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ እየቈረጠ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ እየተቀበለ ፡ በ፩ ጊዜ ፡ የሚያጠግብ ፡ አመጣ ። ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ለደሀው ፤ እየው ፡ ተመልከተው ፤ ቀኝ ፡ እጅና ፡ ባለቤት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ግራ ፡ እጅና ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ በተቀባይነት ፤ በግራ ፡ እጅህ ፡ እንደተቀበልህ ፡ ምሽትህ ፡ ትቀበልሀለች (1) ፡ ገንዘብህም ፣ ይሰበሰባል ፤ በአንድ ፡ እጅህ ፡ ቈርጠህ ፡ በአንድ ፡ እጅህ ፡ እንዳልተሰበሰበልህ ፡ ያለሴትም ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ብርቱ ፡ የለውም ፤ አንተም ፡ ብቻህን ፡ ብትሆን ፡ ነው ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ ተረዳና ፡ ምሽት ፡ አገባ ፡ እጅግ ፡ ብዙኅ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘ ፡ ፩ ዓመት ፡ ሳይሆነው ።

IX

L'AGRICULTEUR DÉSAPPOINTÉ.

Il y avait un homme qui était un cultivateur très actif. Tout ce qu'il semait poussait. Il faisait de grosses récoltes. Mais une fois, ayant semé dix *dāwŭllā* (de céréales) (2) il n'en retira que neuf : une en moins. Irrité de la chose, il en parlait à tout le monde.

Un jour, il rencontra un homme qui, dans le cours de la conversation, l'interrogea sur sa récolte.

(1) = ትቀበል + ልህ + አለች

(2) Une *dāwŭllā* équivaut à 20 *qunnā*. La *qunnā* est une corbeille contenant de 4 à 5 litres de céréales. BAETEMAN, col. 2233).

— Cette année, quelle quantité as-tu semée et quelle quantité as-tu retirée ?

Le cultivateur lui répondit : « Cette année, j'ai semé dix *dāwŭllā*, pensant en retirer beaucoup et, au contraire, je n'en ai obtenu que neuf *dāwŭllā* seulement ».

L'autre le railla en ces termes : « Mais c'est bien ! Tu n'y as rien perdu ! Si sur dix *dāwŭllā*, il t'en manque une, c'est un effet de la seconde mesure ! En fait les dix de la première mesure deviennent neuf à la seconde ».

Le cultivateur se sentit piqué au vif, mais ne répondit rien, ni en mal, ni en bien.

፱ነኛ ፡ ተረት

፩ ሰው ፡ እጅግ ፡ አራሽ ፡ ነበር ፡ የዘራው ፡ ሁሉ ፡ የሚበቅልለት ፤ እህል ፡ ብዙኅ ፡ ያገኝ ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ፲ ዳውላ ፡ ቢዘራው ፡ ፩ ዳውላ ፡ አጎደለና ፡ ፱ ዳውላ ፡ ሆነ ። በዚህም ፡ እየተናደደ ፡ ለሁሉ ፡ ያጫውተው ፡ ነበር ። ፩ ሰው ፡ አገኘና ፡ ከዚያ ፡ ጋራ ፡ ሲጫወቱ ፡ ያዝመራ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ዘንድሮ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘርተህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አገኘህ ፡ አለው ። ያም ፡ አራሽ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፤ ዘንድሮስ ፡ ይበዛልኝ ፡ ብዬ ፡ ፲ ዳውላ ፡ ብዘራው ፡ ፱ ዳውላ ፡ ሆነ ፡ አለው ። ያም ፡ ሰው ፡ ቀለደበት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ደግ ፡ ሆኖሀል ፡ አላጐደለህም ፡ ከ ፲ ዳውላ ፡ ፩ ማጐደሉስ ፡ ዳግሚያ[1] ፡ ስፍር ፡ ነው ፡ አለ ፤ ፩ ጊዜ ፡ የሠፈሩት ፡ ፪ ተኛ ፡ ደግሞ ፡ የሠፈሩት ፡ እንደሆን ፡ ፲ሩ ፡ ፱ኙ ፡ ይሆናል ፡ አለው ። ያም ፡ አራሽ ፡ ተናደደ ፡ ስለዚሁ ፡ ነገር ፣ ክፉም ፡ መልካም ፡ አልተናገረ ፡ ዝም ፡ አለ ።

X

LE CULTIVATEUR TOURNÉ EN RIDICULE.

Un homme était agriculteur et ne connaissait pas d'autre métier que l'agriculture. Une fois, il sema trois *dāwŭllā*[1] et il en retira quatre

(1) Noter ዳግሚያ sur le modèle de መጀመርያ, au lieu de l'habituel ዳግመኛ

(2) Sur la *dāwŭllā*, voir le texte IX.

dāwŭllā. De ce fait, il se dit en lui-même : « Il y a longtemps que je sème des céréales et je ne me souviens pas avoir jamais eu une mauvaise récolte. Mais cette fois, je ne sais pas si ce qui m'arrive est du bien ou du mal ». S'étant assis avec quelqu'un, il lui dit au cours de la conversation : « J'ai semé trois *dāwŭllā* de fèves et j'en ai retiré quatre ».

Celui-là le tourna fortement en ridicule : « Si tu avais fait bouillir la même quantité de fèves, tu aurais obtenu aussi le rendement de quatre pour trois sans avoir besoin de labourer, ni de bêcher ».

፲ኛ ፡ ተረት

አንድ ፡ አራሽ ፡ ነበረ ፡ ከርሻ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የማያውቅ ፤ እርሱም ፡ ፫ ዳውላ ፡ ዘርቶ ፡ ፬ ዳውላ ፡ ሆነው ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ስኖር ፡ እህል ፡ ዘርቸ ፡ ጠፍቶብኝ ፡ አላውቅም ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ የነካኝ ፡ ነገር ፡ አላውቅም ፡ የደህንነትም ፡ ይባልልኝ ፡ የከፋም ፡ ይሁን[1] ፡ ነገር ፡ ይሁን ፡ አላወቅሁ ፡ አለ ። ከ፩ ሰው ፡ ጋራ ፡ በ፩ ተቀምጠው ፡ ሲጫወቱ ፡ ፫ት ፡ ዳውላ ፡ ባጨላ[2] ፡ ዘርቸ ፡ ፬ ዳውላ ፡ ባጨላ ፡ ሆነኝ ፡ ብሎ ፡ ቢነግረው ፡ ያሰው ፡ ብዙኅ ፡ አድርጎ ፡ ቀለደበት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ይህንስ ፡ ያህል ፡ ብትቀቅለውም ፡ የንፍሮው ፡ ውልድም ፡ ፫ቱ ፡ ፬ት ፡ ይሆንህ ፡ ነበር ፡ ሳታርስ ፡ ሳትቆፍር ፡ አለው ።

XI

LE VALET DE CHAMBRE DU ROI ET L'INTRIGANT.

Un roi avait un serviteur auquel il était attaché et il en fit son valet de chambre. A cause de cela, les autres serviteurs le jalousèrent. Poussé par une violente envie (l'un d'entre eux) lui parla ainsi :

« Le roi a dit de toi que, lorsque tu le sers à table, tu l'incommodes avec la mauvaise odeur qui s'exhale de ta bouche. C'est pourquoi,

(1) Le premier ይሁን est une diplographie. — (2) *bāčalā* = *bāqēlā*, avec la palatisation du *q* (cf. M. Cohen, *Traité de langue amharique*, Paris, 1936, p. 35).

lorsque tu le sers, couvre-toi la bouche avec (le bord) de ton vêtement. Je te dis cela, parce que je te veux du bien : s'il s'était agi d'un autre, je ne lui aurais rien dit. Et toi, ne fais savoir à personne ce que je t'ai dit.»

Le valet de chambre pensa : «Il m'a révélé mon défaut par amitié», et il se mit à aimer cet intrigant.

Celui-ci compléta sa manœuvre en allant chez le roi et en lui parlant ainsi :

«Il dit que votre haleine l'incommode, c'est pourquoi, quand il Vous sert, il détourne sa bouche. Si Vous pensez que je mens, observez le quand il Vous sert.»

Le roi, impatient d'en faire la preuve, donna un banquet avant le temps qui avait été fixé. Or, le valet de chambre, quand il servit, se couvrit la bouche avec (le bord de) son vêtement, exactement comme l'avait dit l'intrigant.

Le roi, donc, voulut le punir et l'envoya à l'un de ses fonctionnaires, préposé à un puits hérissé d'épées dont il se servait pour punir (les délinquants) en lui disant : «Dépêche-toi, ne t'arrête pas ni durant le jour ni durant la nuit».

Mais la nuit étant arrivée, le valet de chambre s'arrêta pour passer la nuit dans un autre endroit.

Puis le roi envoya l'intrigant en lui disant : «Va voir comment il a été puni et reviens».

Et il est bien vrai que l'intrigant ne finit pas sa vie tranquillement.

Étant arrivé auprès du fonctionnaire, l'intrigant l'interrogea. Mais celui-là à peine le vit-il arriver qu'il le jeta dans le puits hérissé d'épées.

Le valet de chambre arriva plus tard, vit le supplice de l'intrigant et en référa au roi.

Puis le roi lui dit : «Reprends ton service de valet de chambre».

Pendant son service, il se couvrit la bouche avec (le bord de) son vêtement. «Pourquoi te couvres-tu la bouche» ? lui demanda le roi voyant cela.

Le valet de chambre répondit au roi, en ces termes : «Cet homme qui a été puni était un de mes chers amis. Il m'avait dit : «Quand tu «sers, couvre-toi la bouche, parce que le roi dit que ton haleine le «gêne». Je me couvre la bouche précisément pour ne pas offenser le roi avec ma mauvaise odeur».

Le roi apprenant que l'intrigant était mort de sa perfidie et que son valet de chambre n'avait pas éprouvé de dommage de la faute qu'il n'avait pas commise et qu'il avait échappé au châtiment, pro-

nonça la sentence suivante : «Ne travaille pas contre les autres parce qu'ils travailleront contre toi. Ne fais pas de complot; laisse comploter les autres. Ils ne manqueront pas de tomber dans le fossé qu'ils ont comploté (de creuser)» (1).

፲፩ኛ ፡ ተረት

የንጉሥ ፡ ፩የሚወደው ፡ አሽከር ፡ ነበር ፣ የንጉሥ ፡ አሳላፊ ፡ ሆኖ ፣ ስለዚህ ፡ አሽከሮች ፡ ሁሉ ፡ ይቀኑበት ፡ ነበር ። ከብዙኅ ፡ ቀንዓት ፡ የተነሳ (2) ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፣ ንጉሥ ፡ ሲያሳልፍልኝ ፡ አፉ ፡ ሸተተኝ ፡ ብለውሀልና ፡ ለሚመጣው ፡ ስታሳልፍ ፡ አፍህን ፡ እዮሸፈንህ (3) ፡ በልብስህ ፡ አሳልፍ ፣ ይህን ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ መናገሬ ፡ ብወድህና ፡ ባፈቅርህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ ቢሆን ፡ አልነግረውም ፡ ነበር ፣ አንተም ፡ ለማንም ፡ አትናገር ፡ እንዲህ ፡ ኳለኝ ፡ ብለህ ፡ አለው ። ያ ፡ የንጉሥ ፡ አሳላፊ ፡ ግን ፡ የነገረኝ ፡ ነውሬን ፡ ቢወደኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያን ፡ ሸውከኛ ፡ ወደደው ። ፪ተኛ ፡ ለንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገር ፡ ሠራ ፣ የንጉሥ ፡ አፍ ፡ ሸተተኝ ፡ ብሎ ፡ ሲያሳልፍ ፡ አፉን ፡ እየሸፈነ ፡ ነው ፣ ይህም ፡ ሐሰቴ ፡ እንደሆነ ፡ ሲያሳልፍ ፡ ይመልከቱብኝ ፡ አለ ። ንጉሥም ፡ ቸኩለው ፡ ለማየት ፡ ከፊቱ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድመው ፡ ግብር ፡ አገቡ ። ያም ፡ አሳላፊ ፡ ነገረ ፡ ሰሪ ፡ እንደነገረው ፡ ሲያሳልፍ ፡ አፉን ፡ ሸፈነ ፡ በልብሱ ፣ ንጉሥም ፡ ሊቀጣው ፡ ወደደ ። የሰይፍ ፡ አግዳሚ ፡ ያለው ፡ ዓዘቅት ፡ መቅጫ ፡ ነበረው ። ከዚያ ፡ ከሹሙ ፡ ዘንድ ፡ ሰደደው ፣ አትዋል ፡ አትደር ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ። መሸበትና ፡ ከሌላ ፡ ቦታ ፡ አደረ ፡ በዚያው ፡ ዋለ ። እድሜ ፡ በነገረ ፡ ሰሪ ፡ አያልቅምና ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ነገረ ፡ ሰሪ ፡ ሂድ ፡ አይተህ ፡ አቀጣጡን ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ። ከዚያ ፡ ከሹሙ ፡ ደረሰና ፡ ጠየቀው ፣ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ከሰይፍ ፡ ዓዘቅት ፡ ጨመረው ። አሰላፊ ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ደረሰና ፡ የነገረ ፡ ሠሪውን ፡ መቀጣት ፡ አየና ፡ ለንጉሥ ፡ ነገረው ። ኋላም ፡ ንጉሥ ፡ እንደቀደሙ ፡ አሳልፍ ፡ አለው ።

(1) Les thèmes de ce récit sont répandus dans les contes d'Orient et d'Occident.

(2) Après የተነሳ le sujet de ነገረው manque. Suppléer አንድ ፡ አሽከር

(3) እዮሸፈንህ = እየሸፈንህ

ሲያሳልፍ ፡ አፉን ፡ በልብሱ ፡ ሸፈነ ። ንጉሥም ፡ አይቶ ፡ አፍህን ፡ ለምን ፡ ትሸፍናለህ ፡ አለው ። አሳላፊ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ ለንጉሥ ፤ ያ ፡ የተቀጣ ፡ ሰው ፡ ወንድሜ ፡ ወዳጄ ፡ ነበር ፤ አፍህን ፡ እየሸፈንህ ፡ አሳልፍ ፤ ንጉሥ ፡ ይሸታል ፡ አፉ ፡ ብሎሃል ፡ ቢለኝ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አፌ ፡ እንዳይሸትዎ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለ ። ንጉሥም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገረ ፡ ሰሪ ፡ በከፋቱ ፡ እንደሞተ ፡ የንጉሥ ፡ አሳላፊ ፡ ባላደረገው ፡ ነገር ፡ እንዳልተጎዳ ፡ ከቅጣትም ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አትዋል ፡ ይዋልብህ ፤ አትምከር ፡ ይምከሩ ፤ በመከሩት ፣ ጕድጓድ ፡ ሳይገቡም ፡ አይቀሩ ፡ አለና ፡ ተረተ ።

XII

L'HYÈNE AVIDE.

Une hyène était très amaigrie et très affaiblie par la faim. S'étant mise en chemin pour prendre des nouvelles des pays où régnait l'abondance, elle entendit sur la route des personnes qui disaient : «Il y a un endroit où les charpentes [1] (des cabanes) sont faites d'os et les traverses [2], de chair».

Ayant entendu ces paroles, elle prit sa course sans même demander : «Et où est-ce» ?, avec une telle impétuosité qu'elle roula dans un ravin. Elle craignait que d'autres arrivassent avant elle.

Ce qui advint à l'hyène arrive à tous les gens pressés [3].

፲፪ ተረት

፩ ጅብ ፡ እጅግ ፡ በረኃብ ፡ የከሳ ፡ የደከመ ፡ ነው ። እርሱም ፡ የጠገበት [4] ፡ አገር ፡ ወሬ ፡ ለመጠየቅ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በሄደበት ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ፤ ያጥንት ፡ ግድግዳ ፣ የሥጋ ፡ ማገር ፡

(1) *gĕdgĕdā,* «poutres verticales de la cabane».

(2) *māgar,* «pièces horizontales de la cabane».

(3) Cf. M. Moreno, *Favole e rime galla,* Roma, Tipografia del Senato, 1935, Favola n. XXX, p. 54-55 et Baeteman, col. 1013.

(4) የጠገበት à corriger en የጠገበበት

IMPRIMERIE NATIONALE.

የሆነበት ፡ ሥፍራ ፡ አለ ፡ ሲሉት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሳይጠይቅ ፡ ጣፕ ፡ ሮጠ ፡ ገደል ፡ ገባ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ሳይቀድ ሙኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ የቸከለን ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ጅብ ፡ ያገኝ ፡ ያገኘዋል ።

XIII

LE MOINE ET LE SOLDAT.

Un moine en montant une route, se fatigua et se sentit incapable de continuer. Voyant apparaître une montagne devant lui, il adressa cette prière à Dieu : «Accorde-moi un cheval pour escalader cette montagne», et il s'assit en attendant.

Survint un soldat qui portait sur ses épaules le poulain que sa jument avait mis bas. Lui aussi était fatigué et ne se sentait pas le courage de continuer.

Le moine qui cherchait un cheval fut le premier à parler et il lui dit : «Mon fils, je t'en prie fais-moi monter sur ton cheval pour atteindre le sommet de cette montagne».

Le soldat asséna au moine un coup avec l'extrémité de sa lance, chargea le poulain sur les épaules de ce dernier et l'obligea à grimper à travers la montagne.

Le moine resta déconcerté et dit : «O Seigneur, je te priais de me donner un cheval pour le monter et tu m'as donné un cheval à transporter». Et il ajouta : «O Seigneur, donne de la force à mes jambes pour l'avenir»[1].

፲፫ ተኛ ፡ ተረት

፩ መነኵሴ ፡ ጎደና ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደከመ ፡ ለመሄድም ፡ ተሳ ነው ። ከፊቱም ፡ ተራራ ፡ በተጋረደበት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ የም ወጣበት ፡ ፈረስ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየለመነ ፡ ተቀ ምጦ ፡ ሲጠብቅ ፡ ፩ ወታደር ፡ ፈረሱ ፡ ወልዳበት ፡ የፈረሱን ፡ ግልገል ፡

(1) Littéralement : «bénis mes genoux pour l'avenir».

ተሸከሞ ፡ ደከመ ፤ ለመሄድ ፡ ተቸግሮ ፡ ሳለ ፡ ያን ፡ መነኵሴ ፡ ፈረስ ፡ የሚፈልገውን ፡ አገኘ ። አስቀድሞ ፡ መነኵሴ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ልጄ ፡ አባክህ ፡ በፈረስህ ፡ ይህችን ፡ ተራራ ፡ ልውጣባት ፡ አለ ። ያ ፡ ወታደር ፡ ግን ፡ መነኵሴውን ፡ ፭ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ጀንፍ ፡ መታና ፡ የፈረሱን ፡ ግልገል ፡ አሸከሞ ፡ ተራራው ፡ አስወጣው ። መነኵሴም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ጌታዬ ፡ የምሄድበት ፡ ፈረስ ፡ ስጠኝ ፡ ብየ ፡ ብልህ ፡ የምሸከመው ፡ ፈረስ ፡ ሰጠኸኝ ፡ ብሎ ፡ አደነቀ ፤ ጌታዬ ፡ ለሚመጣው ፡ ጉልበቴን ፡ ባርክልኝ ፡ አለ ።

XIV

L'ÉPOUSE, LE MARI ET L'AMANT.

Il y avait un mari et une épouse. Celle-ci prit un amant. Le mari se mit au lit, disant qu'il était malade des yeux et l'amant venait à la maison et y demeurait en présence du mari, croyant ne pas être vu.

Le mari allait s'asseoir dehors, se faisait donner par sa femme son javelot et l'affilait.

Un jour, tandis que l'amant était à la maison, badinant avec l'épouse, le mari lança le javelot, disant à sa femme : «Prends-le, remets-le en place», et transperça l'amant. Aux cris de l'épouse bouleversée, il répondit en la raillant : «Qu'ai-je cassé ? Ce sont des choses qui arrivent aux aveugles, à ceux qui ne voient pas».

L'épouse enterra son amant dans la maison.

Après cela elle décida, pour se venger, de tuer son mari, et s'étant procuré un poison mortel, elle le mit sur le feu dans un récipient pour le lui servir chaud et sortit. Le mari, s'étant aperçu de la manœuvre, jeta le poison, lava le récipient, mit sur le feu de l'eau pure et attendit.

Ayant fait chauffer le breuvage, la femme, pour s'excuser de ne pas le goûter, se mit au lit faisant semblant d'être malade.

Alors, étant donné que la femme ne voyait pas d'un œil, le mari fit ainsi. Ayant goûté le breuvage une première fois, il regarda et dit : «Je vois d'un œil». L'ayant goûté une seconde fois, il dit : «Je vois de l'autre œil».

Il n'avait jamais été malade (des yeux), mais sa femme, qui avait cru son infirmité véritable, voulant, elle aussi, guérir son œil, se prépara une dose de poison double de celle que le mari avait fait semblant de prendre et l'avala.

Au lieu de se guérir l'œil, elle en mourut.

Et son mari débarrassé de tous ses ennemis, vécut en bonne santé et tranquille.

፲፱ ኛ ፡ ተረት ፡

፪ ት ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ነበሩ ፤ ያችም ፡ ምሽቱም ፡ ውሽማ ፡ ያዘች ። ባሏም ፡ ዓይኔን ፡ አመመኝ ፡ ብሎ ፡ ተኛ ፤ ውሽማዋም (1) ፡ አያዩኝም ፡ ብሎ ፥ ባሏ ፡ ከቤት ፡ እያለ ፡ ውሽማ (2) ፡ መጣና ፡ ከቤት ፡ ተቀመጠ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባሏ ፡ ከዳሬ ፡ ተቀምጠ ፡ ጠሬን ፡ ስጭኝ ፡ እያለ ፡ ይስላል ። ከዕለታቱ ፡ ፩ ቀን ፡ ውሽማ ፡ ከቤት ፡ ሳለ ፡ ከምሽቱ ፡ ጋራ ፡ ሲጫወት ፡ ንሽ ፡ ጠሩን ፡ አኑሬ ፡ ብሎ ፡ ወረወረና ፡ ውሽማውን ፡ ወጋው ። ደነገጠችና ፡ ምሽቱ ፡ ብትጮህ ፡ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቀለደ ፤ ምን ፡ ዕቃ ፡ ሰበርሁ ፡ የሰውር ፡ ነገር ፡ አያስተውል ፡ ብሎ ። ውሽማዋን ፡ ከቤት ፡ ቀበረችው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባሏን ፡ ለመግደል ፡ ተበቀለችው ። የሚገድል ፡ መርዝ ፡ ፈልጋ ፡ በሙቅ ፡ ልትሰጠው ፡ መርዙን ፡ አድርጋ ፡ በዕቃ ፡ ጣደችውና ፡ ወደ ፡ አዳሬ ፡ ወጣች ። ባሏም ፡ አውቆ ፡ ያን ፡ መርዝ ፡ አውጥቶ ፡ ጥሎ ፡ አጥበ ፡ መለሰና ፡ ወሀ ፡ ብቻ ፡ ጣደና ፡ ቆዬ ። አሞቀችና ፡ ሳትቀምስለት ፡ አመመኝ ፡ ብላ ፡ ተኛች ። እርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ፩ ድ ፡ ዓይኗ ፡ ዕውር ፡ ነበረና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ፩ ድ ፡ ጊዜ ፡ ቀምሶ ፡ ዓይኔ ፡ ፩ ዱ ፡ በራልኝ ፡ አለና ፡ አየ ። ፪ ተኛ ፡ ሲቀምስ ፡ ፪ ተኛ ፡ ዓይኔ ፡ በራልኝ ፡ አለና ፡ አወራ ። ፊትም ፡ አላመመውም ፡ ነበርና ፡ እርሷ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ስለ መሰላት ፡ ፩ ድ ፡ ዓይኗን ፡ ለማዳን ፡ ከባሏ ፡ መርዝ ፡ ይልቅ ፡ ፪ ት ፡ እጅ ፡ መርዝ ፡ አደረገችና ፡ በላችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንኳን ፡ ዓይኗ ፡ ይድንላት ፡ ሞተች ። ባሏ ፡ ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ አጥፍቶ ፡ በሕይወት ፡ ተቀመጠ ።

(1) Cp. *Favole e rime galla*, XXV, p. 44-47.

(2) Noter la répétition du sujet : ውሽማ

XV

ASTUCE D'UNE ADULTÈRE.

Une femme avait épousé un commerçant borgne. Celui-ci s'étant rendu dans des pays lointains pour son commerce, elle prit un amant. Longtemps après, le mari commerçant revint. L'amant de l'épouse, pris à l'improviste, se réfugia dans le *māğet*[1]. Pour lui en rendre la sortie possible, la femme imagina un expédient : «Si maintenant Dieu — puisse-t-il ne pas te le faire ! — couvrait ton œil unique de cette manière, que dirais-tu?». L'amant, voyant qu'elle lui couvrait l'œil, chercha de sa cachette, à sortir de la maison, mais arrivé sur le seuil, il trébucha. La femme trouva immédiatement le remède : «Mais combien vous êtes amis, vous deux! Dans l'impatience de revoir mon mari, il s'est précipité et a fait une mauvaise chute!». Entendant dire cela, son amant fit semblant de venir de l'extérieur et embrassa le mari cou contre cou, de façon à ne pas se faire reconnaître.

De cette manière la femme, avec ses expédients et son astuce, sauva son amant des mains de son mari.

፲፭ተኛ ፡ ተረት

፩ት ፡ ሴት ፡ ነበረች ፤ ነጋዴ ፡ አገባች ፤ እርሱም ፡ ፩ ዓይን ፡ ነው ። ለንግድ ፡ እሩቅ ፡ ሀገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ውሽማ ፡ ያዘች ። ያም ፡ ነጋዴ ፡ ባልዋ ፡ በብዙኅ ፡ ቀን ፡ መጣ ፡ የሚስቱ ፡ ውሽማም ፡ ድንግያ ፡ ከማጀት ፡ ተሸሸገ ። ምሽቱም ፡ ውሽማዋን ፡ ለማስወጣት ፡ ምክንያት ፡ ፈለገች ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ባሏን ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤ አሁን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አያድርግብህና ፡ ይህን ፡ ፩ ዱን ፡ ዓይንህ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ቢጨፍንህ ፡ ምን ፡ ባልህ ፡ አለችና ፡ ስትጨፍነው ፡ አይቶ ፡ ውሽማዋ ፡ ከማጀት ፡ ወደ ፡ እዳሪ ፡ እወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ከደጃፍ ፡ ሲደርስ ፡ ወደቀ ። እርሷም ፡ ምሽቱ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ምክንያት ፡ አመካኘች ፤ የ፪ ታችሁ ፡ ፍቅር ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይበዛ ፡ ነው ፤ ናፈቁና ፡ ባሌን ፡ ለማዬት ፡ ሲቸ ኰሉ[2] ፡ ከፉኛ ፡ ወደቁ ፡ ብላ ፡ ስትናገር ፡ ሰምቶ ፡ ውሽማዋ ፡ ከዳሪ ፡

(1) Petit enfoncement à l'intérieur des maisons.

(2) ሲቸኰሉ = ሲቸኩሉ

የመጣ ፡ መሰለና ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡ አንገት ፡ በአንገት ፡ ተቃቅፈው ፡ ተገናኙ ፤ ሳይታወቅ ፡ ቀረ ። ምሽቱ ፡ በምክንያቷ ፡ በጥበቧ ፡ ውሽማዋን ፡ ከባልዋ ፡ እጅ ፡ አዳነችው ።

XVI

LA GUENON ET SA FILLE.

Une guenon conseillait sa fille lui parlant ainsi : «Ma fille, si un homme vient et s'étant approché de toi, il se baisse, il le fait pour prendre une pierre et la jeter sur toi. Ne reste pas là à attendre; sauve-toi, parce qu'il veut te frapper!».

La fille lui répondit : «Ma mère, tu m'as conseillé ainsi. Mais si cet homme a ramassé une pierre pendant que je suis encore éloignée, s'il l'a mise dans son vêtement et qu'il vienne à ma rencontre, dois-je rester ?» (1).

Sa mère lui répondit : «Ce sont des choses qui se feront de ton temps!» (2).

፲፮ተኛ ፡ ተረት ።

፩ድ ፡ ዝንጀሮ ፡ ልጇን ፡ መከረቻት ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፤ ፡ ልጄ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ሲደርስ ፡ ያጎነበሰ ፡ እንደሆነ ፡ ድንጊያ ፡ አንስቶ ፡ ሊመታሽ ፡ ነውና ፡ ፩ድ ፡ ላይ ፡ ቆመሽ ፡ አትቆይው ፡ ሊመታሽ ፡ ነውና ፡ ሽሽ ፡ አለቻት ። ልጇም ፡ መለሰችላት ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፤ እናቴ ፡ አንቺ ፡ ይህን ፡ መከርሽኝ ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ከሩቅ ፡ ድንጊያ ፡ በልብሱ ፡ ውስጥ ፡ ይዞ ፡ ቢመጣስ ፡ ልቆይ ፡ አለቻት ፤ እናቷም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ ይህስ ፡ በአንቺ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡ አለች ።

(1) La guenon s'aperçoit que sa fille a raison, mais pour ne pas reconnaître qu'elle est plus avisée qu'elle, elle lui dit : «De mon temps, les hommes, quand ils voulaient frapper une guenon, ramassaient les pierres sous leurs yeux. De ton temps, il peut se trouver qu'ils fassent comme tu dis».

(2) Cr. E. Mittwoch, *Abessinische Erzählungen und Fabeln*, Berlin, Reichsdruckerei, 1911, Texte XVI, p. 48 et 49.

XVII

LA GUENON CULTIVATRICE.

Une guenon cultiva la terre et y sema des fèves. Le soir, elle retourna à l'endroit, disant : «Je vais voir ma récolte», et elle récolta toutes les fèves qu'elle avait semées, sans en laisser une seule. Les autres guenons qui étaient venues, elles aussi, pour récolter les fèves semées et les manger, ne trouvèrent plus rien, parce qu'elle les avait déjà récoltées. Elles allèrent donc chez elle, et lui dirent : «Pourquoi, ayant semé le matin, as-tu récolté le soir, pour que nous ne puissions pas manger les épis poussés?».

«C'est bon ce qu'on a en main», répondit celle-ci.

Après cela, les guenons cessèrent de dire : «Nous mangerons (ce que l'autre guenon a semé)»(1).

፲፯ተኛ ፡ ተረት ።

፩ ዲት ፡ ዝንጀሮ ፡ ቆፍራ ፡ ባጨላ(2) ፡ ዘራች ፡ ማታ ፡ ግን ፡ አዝመራዩን ፡ ልይ ፡ ብላ ፡ ተመለሰችና ፡ ፩ ድ ፡ ሳይቀር ፡ ዘሩን ፡ ለቀመችው ፤ ሌሎቹ ፡ ዝንጀሮዎች ፡ ዘሩን ፡ ለቅመው ፡ ሊበሉ ፡ ቢሄዱ ፡ አጡ ፡ ዘሩን ፡ ለቅማ ፡ ወስዳው ። ሄደውም ፡ እንዲህ ፡ አሏት ፤ ሲሸት ፡ እንዳንበላው ፡ ለምን ፡ ጡሀት(3) ፡ ዘርተሽ ፡ ማታ ፡ ሰለምን(4) ፡ ለቀምሽው ፡ ቢሏት ፤ በጅ ፡ የያዙት ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መለሰችላቸው ፤ እንዚያም ፡ እንበላለን ፡ ማለትን ፡ ተዉ ፡ ከዚሁ ፡ በኋላ ።

XVIII

LA GARDIENNE DU BLÉ.

Le matin, le pauvre à qui le riche avait dit : « Sois mon héritier », alla, sans l'ordre du riche, examiner le trésor, mais il ne le trouva plus. Il revint, en hâte, auprès du riche et lui dit : « Maître, je suis allé chercher ce que nous avions enterré et je ne l'ai plus trouvé ».

Le riche, sans lui demander qui l'avait pris, sans se perdre en longs discours, se borna à ces quelques paroles : « Qu'as-tu été faire? ».

Le pauvre, ne sachant que répondre demeura silencieux et tout rempli de honte et d'embarras.

Le riche alors parla ainsi : « Et maintenant de quoi hériteras-tu? notre argent est fini. Va-t-en où tu veux ».

Parlant ainsi, il lui donna des provisions de voyage et le renvoya (pensant dans son cœur) : « Pour les fripons, peu de choses sont nécessaires ».

፴፮ ተረት ።

፩ድ ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር ። ልጅ ፡ አልነበረውምና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ያዝናል ፡ መካን ፡ ሆኖ ፡ የገንዘቡ ፡ ወራሽ ፡

(1) Notez que *makkān* est employé au masculin.

በማግቱ ። ፩ድ ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ አምኖ ፡ እቤቱ ፡ ተጠግቶ ፡ ይኖር ፤ እንዲህ ፡ አለው ፤ አንተ ፡ ለገንዘቤ ፡ ወራሽ ፡ ቆራሽ ፡ ሁን ፡ አለው ። ያም ፡ ደሀ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ውረሰኝ ፡ ልጅ ፡ ሁነኝ ፡ አለው ። ፩ቀንም ፡ ይህ ፡ ባለጸጋ ፡ ደሀውን ፡ ሊፈትነው ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ ብሎ ፡ ወሰደው ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ወስዶም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ ከዱር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ እንከታለንና ፡ መሬቱን ፡ ቆፍር ፡ አለው ። ያም ፡ ደሀ ፡ መሬቱን ፡ አርቆ ፡ ቆፈረለት ፡ ያም ፡ ባለጸጋ ፡ ለደሀው ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ ይህን ፡ ስፍራ ፡ ተመልከተው ፡ ብሎ ፡ ፶ ብር ፡ ከተተና ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። ይህ ፡ ባለጸጋ ፡ ይህን ፡ ማድረጉ ፡ ደሀውን ፡ ለመፈተን ፡ ነው ፡ ⟨ያን ፡ ደሀ⟩ [1] ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ባለጸጋ ፡ ደኃው ፡ ሳያይ ፡ ፈጥኖ ፡ አወጣው ፡ መሬቱንም ፡ እንደነበረ ፡ መልሰውና ፡ ፪ተኛ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። በበነጋው ፡ ያ ፡ ትወርሰኛለህ ፡ ያለው ፡ ደሀ ፡ ባለጸጋው ፡ ሰያገዝ ፡ ሂዶ ፡ ቢያዬው ፡ አጣው ። ያ ፡ ደሀ ፡ ፈጥኖ ፡ ከባለጸጋው ፡ ዘንድ ፡ ሂዶ ፡ ነገረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ጌታዬ ፡ ያን ፡ የከተትነውን ፡ ነገር ፡ ብፈልግ ፡ አጣሁት ፡ አለ ። ማን ፡ ወሰደው ፡ ብሎ ፡ ሳይጠይቅ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ባለጸጋ ፤ ምን ፡ ታደርግ ፡ ሂደህ ፡ ኖሯል ፡ አለ ። ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ መለሰለት ። ያም ፡ ደሀ ፡ ቃል ፡ አልመለሰም ። መመለስ ፡ ስላልተቻለው ፡ እጅግ ፡ አፈረ ፡ ደነገፀ ። ባለፀጋ ፡ ግን ፡ ደሀን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ትወርሰኛለህ ፤ ገንዘቡም ፡ ጠፋብን ፤ አሁንም ፡ ከወደድኸው ፡ ኑር ፡ ብሎ ፡ ስንቁን ፡ ሰጥቶ ፡ ሰደደው ። ለወስላታ ፡ ትንሽት ፡ ነገር ፡ ትበቃዋለች ።

XXXVII

LA CERCOPITHÈQUE, ÉPOUSE DU SEPTICORNE.

L'animal qui a sept cornes et la cercopithèque s'épousèrent. Devenus mari et femme, le septicorne se prépara à partir pour un lointain voyage. «Je veux venir avec toi», dit Sœur cercopithèque. Bien que le mari lui eût dit : «Reste, tu ne seras pas en état de supporter la soif», elle ne voulut pas entendre raison et suivit son mari dans son voyage.

(1) Répétition inutile.

Comme il l'avait prévu, elle dit : «J'ai soif». Le mari, embarrassé, commença à creuser le sol pour tirer de l'eau. Tout d'abord il enleva beaucoup de terre, enfin, il parvint à une couche de boue humide et finalement il trouva de l'eau à force de creuser. Après l'avoir fait boire, il dit à son épouse : «Monte sur un arbre et garde l'eau», et alla à la recherche de nourriture.

Sur ce, tous les animaux assoiffés allaient, chacun pour son compte, en quête d'eau, la région en étant privée. Ce fut l'hyène qui la première la retrouva dans l'endroit creusé par le septicorne : «Sœur cercopithèque, à qui est cette eau? Fais-moi boire», dit-elle. Et elle : «Elle est au septicorne». — Et si le septicorne arrive, qu'en tire-t-il ? (qu'importe ?). — Il en tire des tripes et du foie en lambeaux», dit la cercopithèque.

A la pensée qu'il lui aurait enlevé les tripes et le foie, en lambeaux, l'hyène eut peur et s'en alla disant : «Je ne boirai pas l'eau de mon père. Adieu».

Arriva en second lieu la macaque. «Sœur cercopithèque, à qui est cette eau ? Fais-moi boire. — Elle est au septicorne. — Et si le septicorne arrive, que tire-t-il dehors ? — Il en retire des tripes et du foie en lambeaux, dit la cercopithèque». La macaque s'en alla sans boire disant : «Puisqu'il m'enlève les tripes et le foie je ne bois pas l'eau de mon père».

Le lion arriva en troisième lieu, et il demanda : «A qui est cette eau ?». — Elle est au septicorne, répondit-elle. — Et si le septicorne vient, que tire-t-il dehors ? — Il tire dehors des tripes et du foie en lambeaux», répondit cette fois encore la cercopithèque. Mais le lion : «C'est moi qui lui enlèverai les tripes et je ne lui accorderai pas son salut», dit-il. Il but toute l'eau, sans en laisser et s'en alla.

«L'eau du septicorne s'est réduite à un résidu fangeux», s'écria la cercopithèque. Le septicorne entendant ces mots, dit : «Qu'as tu dit ? — Je n'ai rien, dit-elle. J'ai dit seulement que l'eau du septicorne s'est réduite à un résidu fangeux», répondit la cercopithèque. Entendant cela, le septicorne acccourut et en vint aux mains avec le lion qui l'écorcha avec ses griffes. Alors Sœur cercopithèque s'interposa, disant : «Toi, septicorne, aiguise tes cornes, et toi, lion, mets tes griffes dans la boue : dans sept jours, vous reprendrez le combat». Ainsi elle les accorda et tous deux se séparèrent et s'en allèrent, chacun de son côté.

Après cela, la macaque, s'en alla faire visite au lion et lui demanda : «Comment vas-tu ? — J'ai mal aux griffes», répondit le lion. Alors

la macaque combina une intrigue aux dépens de la cercopithèque, disant ceci : «La cercopithèque est capable de coudre une paire de souliers pour tes griffes. Demande-lui de te les faire». Et le lion dit à la cercopithèque : «Couds-moi une paire de souliers». La cercopithèque pensa : «Que l'intrigue retombe sur son auteur»[1]; et, pour faire tuer la macaque, elle fit dire au lion : «C'est vrai, je sais bien les faire, mais on les fabrique avec de la peau de macaque et avec des tendons de macaque, comme fil. Procure-toi les matériaux et envoie-les moi». Le lion tua la macaque qui avait ourdi la trame (de cette affaire), prit la peau et ses tendons et fit dire à la cercopithèque : «Couds-moi (les souliers)».

La cercopithèque, pour gagner du temps, dit : «Il faut les laisser sécher» et les fit sécher. Quand il furent secs, elle dit : «Mettez-les (tremper) dans le lac pour qu'ils s'assouplissent», et elle mit la peau dans le lac qui était limpide et reflétait clairement les images.

Un autre jour, le lion lui fit dire : «Couds-moi (une bonne fois) les souliers et envoie-les moi !».

La cercopithèque s'étant rendue chez lui, lui dit : «Il (un autre lion) m'en a empêché. Il m'a dit «Je ne te les donnerai pas.» Je lui ai dit : «C'est au lion», mais il m'a répondu : «Ma crinière dépasse «la sienne, ma majesté est supérieure à la sienne. En quoi l'emporte-t-il «sur moi ? S'il ne vient pas lui-même, je ne les donne à personne!»

Le lion entra dans une violente colère et lui dit : «Montre-moi le lac où il est.»

«Suis-moi, allons», dit la cercopithèque et le lion alla. Arrivés au bord du lac, la cercopithèque, faisant signe de la main, dit au lion : «Voici celui qui m'a empêchée» ! et elle lui montra son image bien visible par suite de la limpidité de l'eau.

— Maintenant, j'entre dans l'eau, dit le lion.

— N'entre pas ainsi, il pourrait plonger. C'est pourquoi, afin qu'il ne puisse t'échapper, je t'attacherai une pierre sur le dos. Entre dans le lac en portant cette pierre sur toi et tu le rejoindras[2].

«Tu as raison», dit le lion, «lie-moi avec la pierre». Elle, au moyen d'une corde, le lia avec une pierre. Le lion sur la rive, ne réussissait pas à rentrer dans le lac : «Pousse-moi», lui dit-il. La cercopithèque

(1) Littéralement : «que l'affaire soit pire pour celui qui l'apporte» (sens de ገደደ tigriña). Ainsi m'a-t-on expliqué.

(2) La pierre doit aider le lion à aller au fond, pour y rejoindre son rival. La fin de ce récit correspond à la fable, du lion et du lièvre, dans la *Pañcatantra* et dans le *Kalīlah wa-Dimnah*».

lui donna une forte poussée, le jeta dans le lac et s'en retourna chez elle, tandis que l'autre resta dans l'eau.

Ainsi la cercopithèque, avec sa fourberie et son ingéniosité, fit périr ses deux ennemis : le lion et la macaque et se sauva de la mort.

Il est tout à fait vrai le proverbe qui dit qu'«Un peu de ruse c'est mieux que beaucoup de force».

፴፯ ተረት ።

፯ቀንድ ፡ ያለው ፡ አውሬና ፡ ጠጣ ፡ ተጋቡ ። ምሽት ፡ ባሏ ፡ ሆነው ፡ ከሩቅ ፡ ጎደና ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ልሂድ ፡ አለችው ፡ እቴ ፡ ጠጢት ። ባልዋ ፡ ግን ፡ ወሀውን[1] ፡ ጽምዕ[2] ፡ አትችይም ፡ ቅሪ ፡ ቢላት ፡ እምቢ ፡ ብላ ፡ ተከትላው ፡ መንገድ ፡ ሄደች ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ። አስቀድሞ ፡ እንደነገራት ፡ ወሀ ፡ ጸማኝ ፡ አለችው ፤ እርሱም ፡ ተቸግሮ ፡ መሬት ፡ ይቆፍር ፡ ጀመረ ። አወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ብዙኅ ፡ አፈር ፡ አወጣ ፤ ፪ ተኛ ፡ ዕርጥብ ፡ ጭቃ ፡ አወጣ ፤ ፫ ተኛ ፡ ቢቆፍር ፡ ወሀ ፡ አወጣ ፡ ከዚያም ፡ አጠጣት ። ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥተሽ ፡ ጠብቂው ፡ ወሀውን ፡ አለና ፡ እርሱ ፡ ምግብ ፡ ሊፈልግ ፡ ሄደ ። ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ሥፍራ ፡ ያሉ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ወሀ ፡ የለምና ፡ ተጸምተው ፡ በየራሳቸው ፡ ሲፈልጉ ፡ ጋሮብ ፡ አስቀድሞ ፡ አገኘው ፤ እቴ ፡ ጠጢት ፡ ይኸ ፡ ወሀ ፡ የማነው ፡ አጠጪኝ ፡ አላት ። እርሷም ፡ የሰባት ፡ ቀንደ ፡ ነው ፡ አለችው ። ፯ ትቀንደ[3] ፡ ቢመጣ ፡ ምን ፡ ያወጣ ፡ ቢላት ፡ እርሷም ፡ አንጀት ፡ ጉበት ፡ ዘረጋግፎ ፡ ያወጣ ፡ አለችው ። ጋሮቡም ፡ ፈርቶ ፡ ሳይጠጣ ፡ አንጀት ፡ ጉበቴን ፡ ዘረጋግፎ ፡ ከሚያወጣኝ ፡ ከአባቴ ፡ ወሀ ፡ አልጠጣም ፡ ብሎ ፡ ሄደ ፡ በዳኅና ፡ ያውልሽ ፡ ብሎ ። ፪ ተኛ ፡ ዝንጄሪት ፡ መጣችና ፡ እንዲህ ፡ አለቻት ፤ እቴ ፡ ጠጢት ፡ ይኸ ፡ ወሀ ፡ የማነው ፡ አጠጭኝ ፡ አለቻት ። የ፯ ቀንደ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ነገረቻት ፡ ዝንጀሮም ፡ ፯ ቀንደ ፡ ቢመጣ ፡ ምን ፡ ያወጣ ፡ አለቻት ። አንጄት ፡ ጉበት ፡ ዘረጋግፎ ፡ ያወጣ ፡ አለች ፡ ጠጢት ። ዝንጄሮም ፡ አንጀት ፡ ጉበቴን ፡ ዘረጋግፎ ፡ ከሚያወጣኝ ፡ ከአባቴ ፡ ወሀ ፡ አልጠጣም ፡ ብላ ፡ ሳትጠጣ ፡ ሄደች ። ፫ ተ

(1) On attendrait የወሀውን

(2) Archaïsme.

(3) Noter les désinences ቀንደ (ደ et non ድ).

ኛም ፡ አንበሳ ፡ መጣ ፤ ይህ ፡ ወሀ ፡ የማነው ፡ አለ ። የ፯ቀንደ ፡ ነው ፡ አለችው ። ፯ቀንደ ፡ ቢመጣ ፡ ምን ፡ ያወጣ ። አንጄት ፡ ጉበት ፡ ዘረጋ ግፎ ፡ ያወጣ ፡ አለች ፡ ጦጢት ፡ እንደቀደመው ። አንበሳም ፡ እኔ ፡ ዘረጋግፌ ፡ አላወጣውም ፡ አለና ፡ ወሀውን ፡ ፩ድ ፡ ወሀ ፡ ሳይቀር ፡ ጠጣውና ፡ ሄደ ። ጦጢትም ፡ የ፯ት ፡ ቀንደ ፡ ውሀ ፡ ጭልጥ ፡ ጭልጥ ልጥ ፡ አለች[አለች](1) ። ፯ ቀንደ ፡ ሰምቶ ፡ ምን ፡ አልሽ ፡ አላት ። ምንም ፡ አላልሁ ፡ አለችው ። አሁንም ፡ የ ፯ ቀንደ ፡ ወሀ ፡ ጭልጥ ፡ ጭልጥልጥ ፡ አለች ፡ አለች ፤ እርሱም ፡ ሰምቶ ፡ መጣ ፤ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ገጠሙ ፡ ከአንበሶ(2) ፡ ጋራ ። [አንበሳው](3) ፡ በጥፍሩ ፡ ፯ቀንደን ፡ ላጠው ። እቴ ፡ ጦጢት ፡ ገላገለቻቸው ። ፯ቀንዶ ፡ ቀንድህን ፡ እሹል ፤ አንበሶ ፡ ጥፍርህን ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ደብት(4) ፡ ፤ እስከ ፯ቀን ፡ ድረስ ፡ ትገጥማላችሁ ፡ አለችና ፡ ገላገለች ። ተለያዩ ፡ በየራሳቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮ ፡ አንበሳን ፡ ልትጠይቀው ፡ ሄደች ፡ እንደምን ፡ ሆንህ ፡ አለችው ። አንበሳም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ፤ ጥፍሬን ፡ ታምሜ አለሁ ፡ አለ ። ዝንጀሮም ፡ በጦጢት ፡ ነገር ፡ ሠራችባት ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፤ ጦጢት ፡ ለጥፍርህ ፡ ጫማ ፡ መስፉት ፡ ታውቃለች ፤ ስፊልኝ ፡ በላት ፡ አለችው ። አንበሶም(2) ፡ ጦጢትን ፡ ጫማ ፡ ስፊልኝ ፡ አላት ። ጦጢትም ፡ ነገር ፡ ለአምጭ ፡ ይግደደው ፡ አለችና ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ አዎን ፡ አውቃለሁ ፡ እጅግ ፡ አሳምራለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚሰፉ ፡ በዝንጅሮ ፡ ቆርበት ፡ በዝንጄሮ ፡ ጅማት ፡ ነው ፡ የሚሰፉ ፡ አለችና ፡ ላከችበት ፡ ከአንበሳ ፡ ዘንድ ፤ ፈልገህ ፡ ስደድልኝ ፡ ብላ ፡ ላከችበት ፡ ያችን ፡ ዝንጀሮ ፡ ልታስገድል ። ያችን ፡ የመከረችባት ፡ ዝንጀሮን ፡ ገድሎ ፡ ቆርበቷን ፡ ጅማቷን ፡ አውጥቶ ፡ ሰደደላት ፡ ስፊልኝ ፡ ብሎ ። ጦጢትም ፡ መሰንበቻ ፡ መስሏት ፡ ይድረቅ ፡ አለችና ፡ አደረቀችው ። ከደረቀ ፡ በኋላ ፡ እባህር ፡ ጣሉልኝ ፡ ይራስ ፡ አለች ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጣለችው ፡ ቆርበቱን ፤ ባሕሩም ፡ እጅግ ፡ የጸራ ፡ መልክዕ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። በሌላም ፡ ቀን ፡ ሰፍተሽ ፡ ስደጅልኝ ፡ አላት ፡ ጦጢትም ፡ ሄዳ ፡ ከለከለኝ ፡ አልሰጥሽም ፡ ብሎ ፡ አለችው ፤ ያንበሳ ፡ ነው ፡ ብየ ፡ ብለው ፡ ተጋማው ፡ ጋማዬ ፡ ከግርማው ፡ ግርማዬ ፡ በምን ፡ ይበልጠ

(1) Le second **አለች** manque dans le manuscrit.

(2) *anbaso : sic* dans le texte.

(3) Manque dans le manuscrit.

(4) Ce verbe se trouve seulement en Baeteman, col. 906, avec d'autres significations.

ኛል ፤ እርሱ ፡ ካልመጣ ፡ ለምንም ፡ አልሰጥ ፡ አለኝ ፡ አለችው ። አን
በሳም ፡ ተናደደና ፡ ያለበትን ፡ ባሕር ፡ አሳይኝ ፡ አላት ። ና ፡ ተከተ
ለኝና ፡ እንሂድ ፡ አለችው ፤ እርሱም ፡ ሄደ ። ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ ቆማ ፡
ጦጢት ፡ አንበሳን ፡ በ፳ ፡ ጠቅሳ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የከለከለኝ ፡ ብላ ፡ በወ
ሀው ፡ ጽሬት ፡ የሚታዩውን ፡ መልክሁን ፡ አሳዩችው ። ከወሀው ፡
ውስጥ ፡ ልግባ ፡ አላት ። ጦጢትም ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤ እንዲህም ፡
አይዶል ፤ ይጠልቅና ፡ እንደይጠፋህ ፤ ደንገያ ፡ ልሰርልህ ፡ በጀርባህ ፡
አገዝለህ ፡ ግባ ፡ ታገኘዋለህ ፡ አለችው ። አንበሳም ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡
እሠሪኝ ፡ ከደንገያው ፡ ጋራ ፡ አላት ። በገመድ ፡ ከደንገያ ፡ ጋራ ፡ አሰ
ረችው ። አንበሳንመ ፡ ከዳር ፡ ወደባሕሩ ፡ ለመግባት ፡ ተሳነው ፤ አል
ቻለም ። ግፊኝ ፡ አላት ። ጦጢት ፡ ገፋችና ፡ ከባሕሩ ፡ ጣለችውና ፡
ወደቤቷ ፡ ሄደች ፤ እርሱም ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ቀረ ። ጦጢት ፡ በብ
ልሐቷ ፡ በጥበቧ ፡ ዝንጀሮን ፡ አንበሳን ፡ ፪ ቱን ፡ ጠላቶቿን ፡ አጥፍታ ፡
ከሞት ፡ ዳነች ። ከብዙ ፡ ጉልበት ፡ ጥቂት ፡ ብልሀት ፡ ይሻላል ፡
እንዲሉ ።

XXXVIII

LA RÉPONSE INOPPORTUNE DE L'ORIGINAL.

Il y avait un homme qui avait une façon de se comporter tout à fait différente des autres. Son frère qui était un homme normal lui dit : «Mon frère, j'aime la viande. Faisons un petit festin d'agneau et de chèvre». L'autre répondit : «C'est bon!». Le frère, alors, pour se régler dans ses achats sur les goûts de l'autre, demanda : «Des brebis et des chèvres, quelles sont les plus grasses ?» (1).

«Le poisson est visqueux», dit l'original, ne faisant pas attention à la demande qui lui avait été faite et en répondant à ce qui ne lui avait pas été demandé.

፴፰ ተረት ።

፩ ሰው ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ ከሰው ፡ በግብር ፡ እጅግ ፡ የተለዩ ፡
ነው ። ምጥን ፡ ያለው ፡ ወንድሙ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ ወን

(1) Ou bien : entre la (viande de) brebis et la (viande de) chèvre quelle est a plus grasse (et par conséquent : a plus savoureuse)?

ድሜ ፡ ሥጋ ፡ አማረኝ ፡ እንብላ ፡ ከበግና ፡ ከፍየል ፡ አለው ። ለጊዜው ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ያም ፡ ወንድሙ ፡ የሚያምረውን ፡ ጠይቆ ፡ ሊገዛ ፡ ከበግና ፡ ከፍየል ፡ ማን ፡ ይሰባ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ይህ ፡ ግብሩ ፡ የተለዬ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለና ፡ መለሰለት ፡ ያልጠዬቀውን ፡ ዓሣ ፡ ይሙለጨልጫል (1) ፡ አለ ። የጠየቀውን ፡ ጥሎ ፡ ያልጠየቀውን ፡ መለሰለት ።

XXXIX

LE MAITRE D'ÉCOLE, LES POULES ET LES ÉCOLIERS.

Il y avait un homme qui exerçait la profession de maître d'école. Un jour, tandis qu'il faisait sa leçon aux enfants, il ne trouva plus le chasse-mouches à l'endroit où il l'avait mis. Pour faire vivre sa famille, il élevait des poules et les revendait. Peu de temps auparavant, il avait éloigné avec ce chasse-mouches, une poule qui lui salissait tout. Et voici qu'il ne retrouvait plus le chasse-mouches à l'endroit où il l'avait mis. Il réunit les enfants et leur dit : «Vous avez pris mon chasse-mouches, rendez-le moi». Tous les enfants répondirent : «Nous ne l'avons pas vu». — «Mais si vous ne l'avez pas pris, vous, personne d'autre n'est entré ici. Peut-être les poules mangent-elles les chasse-mouches ?», dit le maître.

Alors l'un des écoliers le railla, en lui disant : «Si la poule ne se nourrit pas ainsi, peut-être a-t-elle des fiefs ? Peut-être dispose-t-elle d'assignations de grains (*gamatā* ?)» (2).

Le maître ne sut que répondre, ni en bien, ni en mal.

(1) De ሞለጨለጨ, non signalé dans Guidi, qui a seulement ሙልጭ. Baeteman (col. 66, *sub* መለጠ) note seulement l'adjectif ሞለጮላጫ «glissant, qui échappe des mains».

(2) Jeu de mots intradwisible. En amharique *čerā* signifie aussi bien «chasse-mouches» que «grattant». «Si la poule ne mange pas en grattant (aussi : le chasse-mouches), vit-elle peut-être de rentes?», demande l'écolier.

፴፱ ተረት ።

፩ድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ ሥራው ፡ ማስተማር ። ፩ቀን ፡ ልጆ ቹን ፡ ጥበብ ፡ ሲያስተምር ፡ የዝምብ ፡ መከልከያ ፡ ጭራውን ፡ ከአኖረ በት ፡ አጣው ፤ ደሮም ፡ እያረባ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር ፡ ለምግቡ ። ከፊቱ ፡ በዚያ ፡ ጭራ ፡ ደሮይትን ፡ ከለከላት ፡ ትቢያ ፡ ብትመላበት ። ያን ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ እንደኖረው ፡ ጠፋው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጆችን ፡ ተሰብሰቡ ፡ ብሎ ፡ ሰበሰባቸው ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ ጭራዬን ፡ የወሰዳችሁ ፡ ስጡኝ ፡ አለ ። ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ አላየንም ፡ አሉት ። መምህራቸውም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እና ንት ፡ ካልወሰዳችሁት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አልመጣ ፡ ወይስ ፡ ደሮ ፡ ጭራ ፡ ትበላለች ፡ አለ ። ፩ዱ ፡ ተማሪ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቀለደበት ፡ በመ ምህሩ ፤ ደሮ ፡ ጭራማ ፡ ካልበላች ፡ ጕልት ፡ አላት ፡ ገመታስ ፡ አላት ፡ አለና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መምህሩ ፡ ከፋም ፡ መልካምም ፡ አልመለሰለ ትም ።

XL

LES ÉCOLIERS ET L'AIGUILLE.

Il y avait un maître d'école qui enseignait l'écriture. S'étant mis en route pour aller ailleurs : il donna cet ordre à ses élèves : « Quand vous viendrez, apportez-moi une aiguille ». Ceux-ci se disputèrent, disant : « C'est à toi de la porter ». Un écolier qui connaissait toutes les malices donna ce conseil : « Une aiguille est trop petite pour être portée à deux : enfonçons-la dans un gros et long pieu et tous tant que nous sommes, chargeons-le sur nos épaules, comme on fait les transports avec des perches ». Tous approuvèrent, disant : « C'est ça, c'est ça » ; et ils lui portèrent, sur leurs épaules, l'aiguille liée sur le pieu.

፵ ተረት ።

፩መምህር ፡ የቀለምን ፡ ጥበብ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። ለተማሪዎች[1] ፡ ከሌላ ፡ ስፍራ ፡ መንገድ ፡ በሄደበት ፡ ተማሮቹን[1] ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡

(1) Le narrateur oublie qu'il a déjà mentionné, sous la forme ለተማሪዎች le complément de አዘዘ et le répète sous la forme ተማሮቹን

አዘዘ ፤ ስትመጡ ፡ መርፌ ፡ ይዛችሁልኝ ፡ ኑ ፡ አለ ። እነዚያም ፡ ተፈካከሩ ፡ አንተ ፡ ያዘው ፡ አንተ ፡ ያዘው ፡ ተባብለው ። ፩ዱ ፡ ተማሪ ፡ ለክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከረ ። ፩ዲትን ፡ መርፌ ፡ ፪ት ፡ ሆነን ፡ ለመያዝ ፡ ታንሰብናለች ፤ በትልቅ ፡ ግንድ ፡ ረዛም ፡ ባለ ፡ ላይ ፡ እናድርጋት ፡ ግንዱን ፡ የሳንሳ ፡ ሁላችንም ፡ እንሸከም ፡ አለ ። ሁሉም ፡ ነገሩን ፡ ወደዱለት ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ በግንዱ ፡ ላይ ፡ መርፌውን ፡ አሰረው ፡ ተሸከሙና ፡ ወሰዱለት ።

XLI

LE NAIN ET SES FRÈRES.

Il y avait 7 frères. L'un d'eux était de petite stature, mais capable de toutes les ruses.

Ses autres frères égorgèrent son bœuf et le mangèrent à son nez.

«Donnez-moi seulement la peau de mon bœuf», dit-il. «Peu m'importe que vous me l'ayez égorgé. Elle me rapportera. Donnez-moi la peau pour que je la vende».

Il s'en alla et trouva une tanière de rats. Il replia [à la manière d'un sac] la peau du bœuf, en plaça l'orifice sur la tanière de façon à la recouvrir entièrement, et lorsque la peau fut pleine de rats, il en ferma l'ouverture, la chargea sur ses épaules et se remit en chemin.

Le soir étant venu, il monta sur un sycomore, portant la peau avec lui. Un peu plus tard arrivèrent des commerçants, avec une importante caravane de mulets chargés, et campèrent au pied de l'arbre.

Quand minuit fut arrivé, il jeta la peau sur eux. Les mulets s'emportèrent, et les hommes ayant tout abandonné, prirent la fuite en disant : «Qu'est-ce donc qu'il a plu sur nous?».

[Notre] homme descendit de l'arbre, s'empara de tout le butin qu'il put et rentra chez lui. «Vous avez tué mon bœuf. Eh bien, j'ai vendu la peau et en ai retiré tout ceci. Si vous égorgiez aussi vos bœufs, vous pourriez faire une bonne affaire comme moi», dit-il à ses frères.

Ceux-ci, croyant qu'il disait la vérité, tuèrent leurs bœufs et s'en allèrent vendre les peaux; mais les gens, entendant dire : «Achetez»

les prenaient pour des nigauds. Ils s'en revinrent donc furieux, comprenant qu'il leur avait joué un tour.

En second lieu, ils brûlèrent sa maison : «Vous avez brûlé ma maison?», leur dit-il. — Cela ne fait rien.

Il en chargea la cendre sur de nombreux ânes et partit, en emportant comme provisions de voyage, de la farine de *tief*, avec un peu de *tief* en grains.

Il marcha, marcha et arriva à la maison d'un homme riche et lui dit : «Je transporte la farine du roi».

A cette déclaration, le riche le reçut dans sa maison. A minuit, il porta dehors toute cette cendre et la répandit sur le sol; puis il se mit à crier et à se lamenter, faisant venir tout le monde : «Il m'a fait soustraire [par ses gens] la farine au roi et m'a laissé seulement ce genre de farine ici (c'est-à-dire la cendre) et ce *tief* en grains». Le riche lui dit : «Mets dans des sacs autant de farine que tes ânes peuvent en transporter et emporte-la, mais ne me conduis pas devant le roi».

Il chargea (ses ânes), retourna dans son pays et dit à ses frères : «Si vous avez brûlé ma maison, quel dommage en ai-je subi? En échange de la cendre j'ai reçu de quoi pourvoir à mes repas. Vous feriez bien de brûler aussi vos maisons. Vous en retireriez de la farine pour vos repas».

Ils crurent qu'il parlait sérieusement, et ayant brûlé leurs maisons, et ayant chargé les cendres de celles-ci sur des ânes, ils se mirent en chemin. «Si l'on vous demande de quelle famille vous êtes, dites que vous appartenez à la famille du petit nain», leur recommanda le frère.

Ils commencèrent à aller aux alentours en disant : «Nous avons de la cendre à échanger».

Ceux qui les entendaient, les insultaient, en disant : «De quelle race d'imbéciles sont-ils? Quelle espèce d'échange veulent-ils faire?».

Après cela, ils arrivèrent à la maison de ce riche.

— «D'où venez-vous?», leur demanda-t-il. «Nous sommes des parents du petit nain», répondirent-ils.

«Ah! Ils sont les frères de ce gredin», s'écria celui-ci et il les fit rouer de coups de bâtons.

«Comment a-t-il osé se moquer de nous une seconde fois? maintenant, dès que nous serons rentrés, nous le tuerons» [se dirent les frères].

Ils l'enfermèrent dans un panier servant de ruche et le transpor-

tèrent au bord d'un précipice, où ils le laissèrent pour aller tailler une branche en forme de fourche pour rouler le panier[1].

A ce moment-là survint un homme monté sur un mulet qui, croyant trouver du miel dans le panier, [s'approcha et ayant vu le nain à l'intérieur] dit : «Qui es-tu ?».

«Je suis un moine et je me tiens là-dedans dans le but de me sanctifier.»

Le propriétaire [du mulet] lui dit : «Moi j'entrerai dans le panier. Toi, sors et va-t-en avec mon mulet». Et il entra dans le panier.

Les autres étant arrivés, le poussèrent avec la branche fourchue dans le précipice, croyant que c'était le nain.

Celui-ci étant sorti du panier et monté sur le mulet, retourna dans son pays et dit à ses frères : «Dans le précipice où vous m'avez jeté j'ai trouvé ce mulet. Pourquoi n'allez-vous pas, vous aussi, dans le précipice ? Vous y trouveriez aussi un mulet».

Les frères croyant qu'il parlait sérieusement, lui dirent : «Jette-nous aussi dans le précipice».

Et il fit ainsi. Les ayant enfermés dans un panier, il les jeta dans le précipice et devint maître de leurs fortunes après s'être sauvé de la mort, par sa malice.

፵፩ ተረት ።

፯ ወንድማማቾች ፡ ነበሩ ፤ ፩ኛው ፡ ታናሽ ፡ ነው ፡ ቁመቱ ፤ ለከፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ ነበር ። የርሱን ፡ በሬ ፡ ፯ ቱ ፡ ወንድሞቹ ፡ አርደው ፡ በሉበት ፡ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የበሬዬን ፡ ቆርበት ፡ ስጡኝ ፡ እንጂ ፡ ግድ ፡ የለኝም ፤ ብታርዱትም ፡ ያተርፈኛል ፡ ቆርበቱን ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ ልሸጠው ፡ ብሎ ፡ ሄደ ። የአይጥ ፡ ጎሬ ፡ አገኘ ፡ ከዚያም ፡ ጎሬ ፡ የበሬውን ፡ ቆርበት ፡ አፍ ፡ እንደተጠቀለለ ፡ አስጠግቶ ፡ አኖረው ፤ የቀረውን ፡ የአይጥ ፡ ጎሬ ፡ ደፈነው ። አይጦቹ ፡ ከዚያ ፡ ቆርበት ፡ ሲሰበሰቡ ፡ የዚያን ፡ ቆርበት ፡ አፍ ፡ ገጥሞ ፡ ተሸክሞ ፡ ሲሄድ ፡ መሸበት ፤ ከወርካ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ቆርበቱን ፡ ይዞ ፡ ወጣ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዙህ ፡ ከብት ፡ የጫኑ ፡ ነጋዶች ፡ መጡና ፡ ከስሩ ፡ ሰፈሩ ። መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ያን ፡ ቆርበት ፡

(1) Il s'agit d'un *qafo*, grand panier cylindrique ou tronc d'arbre creusé servant de ruche.

ፀሓያቸው ፡ ላይ ፡ ጣለው ፤ በቅሎዎችም ፡ ደነበሩ ፡ ምን ፡ ዘነመብን ፡
ብለው ፡ ሰዎችም ፡ ጥለው ፡ ሸሹ ። ያም ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ወርዶ ፡
የቻለውን ፡ ያህል ፡ ብዙኅ ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ወደቤቱ ፡ ተመለሰ ፡ ወን
ድሞቹንም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ እናንተ ፡ በሬዬን ፡ ብታርዱብኝ ፡
ቆርበቱን ፡ ሽጬ ፡ ይህን ፡ አወጣልኝ ፤ እናንተም ፡ በሬዎቻችሁን ፡
ብታርዱ ፡ እንደኔ ፡ ይሸጥላችሁ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ እው
ነት ፡ ስለመሰላቸው ፡ በሬያቸውን ፡ አርደው ፡ ቆርበት ፡ ሊሸጡ ፡
ሄዱ ። ቆርበት ፡ ግዙ ፡ ሲሉ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ይሞኛሉ ፡ እያሉ ፡ ቢፈ
ርዱባቸው ፡ ተመለሱ ፡ እየተናደዱ ፤ ተጫወተብን ፡ ብለው ፡ ስለተ
ናደዱ ። ፪ተኛ ፡ ቤቱን ፡ አቃጠሉበት ። ቤቴን ፡ እናንት ፡ ብታቃ
ጥሉብኝ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ብሎ ፡ አመዱን ፡ በብዙኅ ፡ አህያ ፡ ጭኖ ፡
ሄደ ። ስንቁን ፡ ጤፍ ፡ ዶጨት[1] ፡ ይዞ ፡ ጥቂት ፡ ጥሬ ፡ ጤፍ ፡
ጨምሮ ፡ ይዞ ፡ ሲሄድ ፡ ከአንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ቤት ፡ ደረሰ ። ያን ፡ ባለ
ጸጋ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ የንጉሥን ፡ ዶጨት[1] ፡ ጭኛለሁ ፡ ብሎ ፡
ሲል ፡ አስገባው ፡ ከቤቱ ። በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ አመድ ፡
እያወጣ ፡ ከሜዳው ፡ ደፋው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡
ቁቁ[2] ፡ አለና ፡ ጮኸ ፡ የንጉሥን ፡ ዶጨት ፡ አስወሰደብኝ ፡ ይህችን ፡
ዶጨት ፡ ይህንን ፡ ጥሬ ፡ ጤፍ ፡ ብቻ ፡ ትቶልኝ ፡ አለ ። ያም ፡ ባለ
ጸጋ ፡ በሽልቻህ ፡ እየመላህ ፡ አህዮችህ ፡ እንደቻሉልህ ፡ ውሰድ ፡
ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ አትውሰደኝ ፡ ብሎ ፡ ሰጠው ። ጭኖ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡
ሄደ ፡ ለወንድሞቹም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ቤቴን ፡ ብታቃጥሉት[3] ፡ እኔ ፡
ምን ፡ እጎዳለሁ ፤ አመዱን ፡ መሳ[4] ፡ ለውጬው ፡ መጣሁ ፡ አለ ።
አሁንም ፡ እናንተም ፡ ቤታችሁን ፡ ብታቃጥሉት ፡ መሳ[4] ፡ ይለወጥ ፡
ነበር ፡ ለመሳ ፡ ዶጨት ፡ አላቸው ። እውነቱ ፡ መሰላቸው ። ቤታቸው ፡
አቃጠሉና ፡ አመዱን ፡ በአህያ ፡ ላይ ፡ ጭነው ፡ ሄዱ ። የማናችሁ[5] ፡
ብለው ፡ ቢጠይቋችሁም ፡ የድንክዬ ፡ ነን ፡ በሉ ፡ አላቸው ። አመድ ፡
ለውጡ ፡ ይሉ ፡ ጀመረ ። የሰሙአቸው ፡ ሰዎችም ፡ የወደሄት ፡ ከርፋ
ፎች ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ ይሰድቧቸው ፡ ጀመረ ፡ እንዴት ፡ አድር
ገው ፡ ሊለውጡ ፡ ነው ፡ እያሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ከባለጸጋው ፡

(1) ዶጨት = ዶቄት
(2) Onomatopéique.
(3) Le manuscrit a ብታቃጡሉት
(4) መሳ = ምሳ
(5) የማናችሁ = የማን ፡ ናችሁ

ወንድማቸው ፡ ዶጨቱን ፡ ከወሰደበት ፡ ሰው ፡ [ደረሱ][1] ። ከወደ
ዬት ፡ መጣችሁ ፡ አላቸው ። የድንክዬ ፡ ነን ፡ አሉ ። የዚያ ፡ የከፉ ፡
ወንድሞች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ አስደበደባቸው ። ፪ተኛ ፡ እንዴት ፡
አድርጎ ፡ ተጫወተብን ፤ አሁንም ፡ ተመልሰን ፡ እንግደለው ፡ አሉ ።
በቀፎ ፡ አድርገው ፡ ወሰዱት ። ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ሲደርሱ ፡ ገፍተን ፡
የምንጥልበት ፡ ባላ ፡ እንቁረጥ ፡ ብለው ፡ ከአፋፉ ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፩ ባለበቅሎ ፡ መጣ ። ማር ፡ አለበት ፡ መሰሎት ፡
ቀፎው ፡ ምንድር ፡ ነህ ፡ አለው ። መነኰሴ ፡ ነኝ ፡ እንድጸድቅ ፡ ብዬ ፡
ነው ፡ አለው ። ያም ፡ ባለበቅሎ ፡ እንዲህ ፡ አሌ ፤ እኔ ፡ ከቀ
ፎው ፡ ውስጥ ፡ ልግባ ፤ አንተ ፡ ውጣና ፡ በበቅሎዬ ፡ ሂድ ፡ አለው ።
ያም ፡ ከቀፎው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ በባላ ፡ ገፍተው ፡
ጣሉት ፡ ድንክያ ፡ መሰሏቸው ፤ ድንክዬም ፡ ከቀፎው ፡ ወጥቶ ፡ በበ
ቅሎ ፡ ሆኖ ፡ ወደሀገሩ ፡ ሄዶ ፡ ወንድሞቹን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እና
ንተ ፡ ገደል ፡ ገፍታችሁ ፡ ብትጥሉኝ ፡ ይህን ፡ በቅሎ ፡ አገኘሁ ።
እናንተም ፡ ገደል ፡ ብትገቡ ፡ እንደኔ ፡ በቅሎ ፡ ታገኙ ፡ ነበር ፡ አላ
ቸው ። ወንድሞቹም ፡ ዕውነት ፡ መሰላቸውና ፡ እኛንም ፡ ገደል ፡
ጣለን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ በቀፎ ፡ አድርጎ ፡ ገደል ፡ ጣላቸው ፡ እር
ሱም ፡ ንብረታቸውን ፡ ወርሶ ፡ ተቀመጠ ፡ በከፉ ፡ ጥበቡ ፡ ከሞትም ፡
ዳነ ።

XLII

LE PHILOSOPHE ET L'HOMME QUI DEMANDAIT CONSEIL.

Un homme se rendit chez un philosophe et lui dit : «Donne-moi un conseil. — Mon frère, que t'est-il arrivé pour que tu viennes chez moi ?» demanda le philosophe au visiteur.

— Je suis venu pour que tu me conseilles et m'instruises.

Et le philosophe : «A quoi bon donner des conseils. Est-ce que tu m'écouteras ?».

«Qu'entends-tu dire ?», demanda l'autre.

«Le cœur est pire qu'un cheval rétif», dit le philosophe.

[1] Ajouté par nous.

— Lorsqu'un cheval est rétif, on lui fait un mors pour le dompter. Si je ne voulais pas t'écouter pourquoi serais-je venu ? Je suis ici chez toi précisément pour t'écouter dit le visiteur.

— Je m'explique. Tu as deux partis dans l'esprit, et tu me demandes lequel des deux est le meilleur. Si je te dis de suivre celui que ton cœur préfère, alors c'est vrai, tu m'écoutes ; mais si je te dis de suivre celui que ton cœur n'agrée pas et rejette, alors tu ne m'écoutes pas. Quand un homme demande un conseil, il le fait pour que lui soit confirmée, qu'il a déjà décidé [de faire]. C'est le cœur qui commande à l'homme, non pas les étrangers.

Ainsi parla le philosophe, et il avait raison.

፵፪ ተረት ።

፩ ሰው ፡ ምከረኝ ፡ ብሎ ፡ ከ፩ድ ፡ ፈላስፋ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ያም ፡ ፈላስፋ ፡ እህንዲ ፡ አለ ፡ እንግዳውን ፤ ወንድሜ ፡ ከኔ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለህ ፡ የመጣህ ፡ አለው ። ያም ፡ እንግዳ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ትመከረኝ ፡ ታስተምረኝ ፡ ብየ ፡ ነው ፡ አለ ። ያም ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የምትሰማኝ ፡ ይመስል ፤ ምን ፡ ያስመክራል ፡ አለ ። ምነው ፡ ሲለው ፤ ልብ ፡ ከአጥባቂ ፡ ፈረስ ፡ ይብሳል ፡ አለው ። ለአጥባቂ ፡ ፈረስ ፡ ልጓም ፡ ይሰራለታል ፡ እንደመጠኑ ፡ ይመለሳል ፡ አለው ። ባልሰማህ ፡ ለምን ፡ መጣሁ ፤ ልሰማህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለ ። አሁን ፡ አንተ ፡ ፪ ነገር ፡ ታስባለህ ፤ ከ፪ቱ ፡ ከዚህና ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ ትለኛለህ ። ልብህ ፡ የወደደውን ፡ ነገር ፡ አድርግ ፡ ብዬ ፡ ብልህ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ትሰማኛለህ ። ፪ተኛ ፡ ልብህ ፡ ያልወደደውን ፡ የጠላውን ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ አድርግ ፡ ብዬ ፡ ብልህ ፡ አትሰማኝም ። ሰውም ፡ አማከረኝ ፡ የሚል ፡ ⟨ያልሁትን ፡⟩[1] ያሰብሁት ፡ ያልሁት ፡ ሲሆንልኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ አያዝዘውም ፤ ልብ ፡ ነው ፡ አዛዥ ፡ አለ ። ይህም ፡ እውነት ፡ ነው ።

(1) Voir *Favole e rime galla*, récit XXXVII, p. 64-69 ; E. Littmann, *Tales, customs, names and dirges of the Tigre Tribes*, récit 16, vol. I (Leyden, Brill 1910), Tigre Text, p. 18-23 ; vol. II (Leyden, Brill, 1910) English translation, p. 19-25.

XLIII

LE MOINE ET LA NONNE.

Il y avait un homme chaste et pur qui prit une nonne pour qu'elle l'aidât. Tandis que le moine était à l'église, elle se bourra de beurre et de sauce à l'ail et aux oignons, et quand cet homme revint et dit : «C'est l'heure du dîner, mangeons», elle, au lieu d'avouer qu'elle était déjà rassasiée, dit : «Je suis malade. Je n'ai pas envie de manger», et elle s'en alla au lit.

Un jour, se tenant sur la porte, le moine vit qu'elle mangeait une bonne sauce au beurre. Le soir, quand ce fut l'heure du dîner, la femme dit : «J'ai mal à une dent».

Et lui : «Sœur, laissez! Ne donnez pas d'importance à votre dent». Pour faire allusion au fait qu'elle avait mangé auparavant [1].

፵፫ተኛ ፡ ተረት ።

፩ ሰው ፡ ንጹሕ ፡ ድንግል ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ የምትረዳው ፡ ፩ ዲት ፡
መነኰሲት ፡ አገባ ። እርሷም ፡ በጊዜ ፡ ምግቧን ፡ በቅቤና ፡ በድልህ ፡
ትበላለች ፤ ያመነኰሴ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይውልና ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ራት ፡ ይቀርባል ፡ እንብላ ፡ ባላት ፡ ጊዜ ፡ ጠገብሁ ፡ ስለማለት ፡ ፈንታ ፡
አመመኝ ፡ እህል ፡ አያሰበላኝም ፡ እያለች ፡ ትተኛለች ። ከዕለታቱም ፡
፩ ድ ፡ ቀን ፡ ከደጅ ፡ ተቀምጠ ፡ ሳለ ፡ በቅቤ ፡ ወጥ ፡ ስትበላ ፡ አያት ።
ማታ ፡ ግን ፡ ራት ፡ ሲቀርብ ፡ አመመኝ ፡ ጥርሴን ፡ አለች ። ፡ እር
ሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ይቶት ፡ ተው ፡ ለጥርስሁ ፡ ፊት ፡ አትስጡት ፡
አለ ፤ ፊት ፡ የበላችውን ፡ ሊነግራት ።

(1) Le calembour intraduisible repose sur le double sens du mot *fit* qui signifie en amharique *visage* et *d'abord* et donne à la phrase ces deux significations : «ne donnez pas le visage (ne tournez pas le visage) à votre dent», c'est-à-dire : «ne lui donnez pas d'importance» et «ne donnez pas (à manger) d'abord à votre dent».

IMPRIMERIE NATIONALE.

XLIV

LE SERVITEUR QUI GRILLAIT LE SORGHO.

Il y avait un homme riche qui habitait sur le haut plateau. Ses parents qui résidaient dans la plaine lui envoyèrent du sorgho en même temps qu'un serviteur pour le lui préparer et le lui servir. Le soir, le serviteur commença à griller le sorgho et à le servir peu à peu, très chaud, mais à un beau moment, il commença à manger le sorgho grillé et cessa de le servir. Le riche, alors, ayant vu que le serviteur mangeait le sorgho [au lieu de le réprimander directement] dit aux gens de la maison, faisant semblant de se préoccuper de lui, comme si le feu lui avait brûlé les mains : «Prenez-le lui, pour qu'il ne se brûle pas».

፵፬ ተረት ።

፩ ባለጸጋ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ከደጋ ፡ የሚኖር ፤ ዘመዶቹ ፡ ግን ፡ ከቆላ ፡
ነበሩ ። እነዚያም ፡ ማሽላ ፡ ሰደዱለት ፤ አሽቶ ፡ የሚያበላ ፡ አሽከር ፡
ጨምረው ፡ ሰደዱለት ። ማታ ፡ ጊዜ ፡ እየጠበሰ ፡ ትኩስ ፡ ትኩሱን ፡
ይሰጣቸው ፡ ጀመር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ትኩሱን ፡ እየበላ ፡ ያ ፡ አሽከር ፡
የማይሰጣቸው ፡ ሆነ ። ሰለዚህ ፡ ነገር ፡ ባለጸጋ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ያዘ
ነለት ፡ መስሎ ፡ ለቤቱ ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረ ፡ እሳቱ ፡
እጁን ፡ የፈጀው ፡ አስመስሎ ። ተቀበሉት ፡ አይፍጀው ፡ አለ ።
ማሽላውን ፡ አሽከሩ ፡ ሰለበላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

XLV

LE MARI TROMPÉ ET PEUREUX.

Dans un pays habitait un homme qui avait pris femme. Celle-ci le trompa en prenant un amant. Son mari lui ayant dit qu'il partait en voyage, quand il fut parti, elle introduisit l'amant dans la maison.

Arriva le mari, avec un juge et des témoins[1] pour faire arrêter l'amant.

«Entre et prends-le», lui dirent ceux-ci.

Mais le mari qui avait peur dit : «Prenez-le vous-même : moi je suis partie dans le procès».

፵፭ ተረት ።

፩ ሰው ፡ በ፩ ሀገር ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ሲኖር ፡ እርሱን ፡ ትታ ፡ ሌላ ፡ ውሽማ ፡ ያዘች ። ባሏም ፡ ከሌላ ፡ ሀገር ፡ ሄድሁ ፡ ብሎ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ምሽቱም ፡ ከቤቷ ፡ ውሽማዋን ፡ ይዛ ፡ ተቀምጣ ፡ ሳለች ፡ ባሏም ፡ ውሽማ ፡ እይዛለሁ ፡ ብሎ ፡ መጣ ። ዳኛ ፡ እማኝ ፡ ይዞ ፡ እነ ዚያም ፡ ግባና ፡ ያዘው ፡ አሉት ። እንዲህ ፡ አለ ፤ እኔማ ፡ ጠበኛ ፡ ነኝ ፡ እናንተ ፡ ያዙት ፡ እንጂ ፡ አለ ፤ ስለፈራ ።

XLVI

LA FATIGUE INUTILE D'UNE FEMME.

Le roi, ayant réuni ses soldats, les envoya contre un rebelle qui s'était insurgé dans le territoire de son royaume. Un combat étant survenu avec le rebelle, les deux partis eurent des pertes. Apprenant qu'il y avait des pertes parmi les soldats, leurs femmes se rendirent sur le lieu du combat se disant : «Si nos maris ont été blessés, nous leur donnerons à boire, si nous les trouvons morts, nous leur lèverons la tête»[2].

Une de ces femmes, trouva son mari [simplement] blessé.

Elle poussa des cris d'allégresse, se réjouit et lui fit (une quantité) infinie de protestations de dévouement[3].

[1] *ĕmmāñ*, pas indiqué dans les vocabulaires : «personne de confiance que la partie désigne pour assister le juge».

[2] Expression abyssine correspondant à «fermer les yeux à un mort».

[3] Plus littéralement : «et elle lui demanda un nombre infini de fois : «Que puis-je faire pour toi?».

«Si tu as de la force, prends-moi sur tes épaules et porte-moi au camp», lui dit le mari.

«C'est bien», lui répondit-elle. Elle le chargea sur les épaules et le porta pendant un long trajet.

Puis comme elle le remontait, il fut touché à l'endroit de sa blessure et il cria : «Aïe, ça me fait mal».

Il se tenait assis à califourchon sur ses épaules. L'entendant dire «Aïe», la femme lui demanda :

— Qu'est-ce que c'est ?

— Je suis émasculé, lui répondit-il.

En entendant ces mots, la femme dit : «Alors, je porte un homme châtré sur mes épaules!»[1]. Elle le jeta par terre et s'en alla sans même se retourner pour le regarder.

Et elle regretta de s'être donné la peine de le transporter de l'endroit où il avait été émasculé à l'endroit où elle l'avait déchargé.

፵፮ ተረት ።

ንጉሥ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበ ፡ በሚገዛው ፡ ሀገር ፡ ሽፍታ ፡ ቢነሳበት ፡ ሄዱ ፡ ከዚያም ፡ ሽፍታ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ[2] ፤ ሰው ፡ ከሁሉም ፡ አለቀባቸው ። ሠራዊቱ ፡ አለቁ ፡ የሚል ፡ ወሬን ፡ በሰሙ ፤ ምሽቶቻቸው ፤ ቢቆስሉም ፡ ባሎቻችን ፡ ወሀ ፡ እናጠጣቸዋለን ፡ ቢሞቱም ፡ ሬሳቸውን ፡ እናነሳለን ፡ ብለው ፡ ሄዱ ፡ ከተዋጉበት ፡ ሥፍራ ። ከነዚያም ፡ ሴቶች ፡ ፩ ዷት ፡ ባሏን ፡ ቆስሎ ፡ አገኘችው ፤ እልል ፡ አለች ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላት ፡ ያለመጠን ፡ እንደምን ፡ ይሁን ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። ትችይኝ ፡ እንደሆን ፡ አዝይኝና ፤ ከሰፈራችን ፡ ውሰጂኝ ፡ አላት ። ይሁን ፡ ብላ ፡ አዘለችና ፡ ወሰደችው ፤ ብዙኅ ፡ ጎደና ። ወደ ላይ ፡ ከፍ ፡ ስታደርገው ፡ ቍስሉን ፡ ብትነካበት ፡ ሀይ ፡ አመመኝ ፡ አላት ። በጀርባዋ ፡ ላይ ፡ እንደፈረሰ ፡ አድርጎ ፡ ተቀምጦባት ፡ ነበርና ፡ ምሽቱም ፡ ሀይ ፡ ሲል ፡ ሰምታ ፡ ምንው ፡ አለችው ። ተሰልቤ ፡ አለሁ ፡ አላት ። እርሷም ፡ ይህን ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ እንግዲያው ፡

(1) Noter ce sens de *muqaṭā* qui veut dire habituellement «mortier». De *waqqaṭa* «écrasa» et aussi «châtrer en écrasant les testicules».

(2) ሰብስበ, የሚገዛው, ሄደ, ተዋጉ. Noter l'alternance du singulier et du pluriel «de majesté».

ሙቀጫ ፡ ተሸከሜ ፡ ነው ፡ መሄዴ ፡ አለችና ፡ ጥላው ፡ ሄደች ፡ ዘሬ ፡ አላዩችውም ። ከተሰለበበት ፡ ስፍራ ፡ እስከጣለችበት ፡ ሥፍራ ፤ ተሸ ክማ ፡ ስለአመጣችው ፡ ተጣጠተች ።

XLVII

L'HÔTE GLOUTON.

Un homme étant en voyage et voyant qu'il se faisait tard demanda l'hospitalité dans la maison d'un riche, en disant : «Je suis l'hôte de Dieu».

Le soir, ils lui donnèrent [les choses nécessaires] pour dormir et lui remirent un bâton en disant : «Il y a là, à côté, un veau. S'il s'approche, sers-toi de ce bâton pour qu'il ne te mange pas tes habits».

Le mari et la femme allèrent dormir à leur place [habituelle]. La femme de ce riche se leva pour donner à manger à son mari.

Ayant mis la casserole sur le feu, elle fit chauffer une bonne pitance avec une sauce au beurre et un hachis d'ail et d'oignons et le feu s'étant éteint, elle appela son mari, en disant : «Patron!».

Mais comme le maître de la maison n'entendait pas, l'hôte se fit passer pour le maître de la maison, s'approcha et mangea comme un ogre, servi par les mains mêmes de l'épouse du riche, puis il s'en retourna dormir à sa place.

La femme du riche lava le récipient avec lequel elle avait servi la nourriture et alla se coucher auprès de son mari. Celui-ci sentant l'humidité des mains [de sa femme] s'éveilla et lui dit : «Où es-tu allée ?».

«Que dis-tu ? Tu n'as pas mangé à l'instant la nourriture que je t'ai préparée ? Tu plaisantes sans doute?», dit la femme.

«Depuis hier au soir que je me suis mis au lit jusqu'à ce moment, je ne me suis pas réveillé», répondit le mari.

«Alors c'est l'hôte qui se faisait passer pour toi, qui est venu manger», dit la femme et pour s'en assurer, elle alla sentir la bouche de l'hôte [pour se rendre compte] si elle portait l'odeur de la sauce au beurre.

Pendant qu'elle le sentait l'hôte s'écria : «Le veau a mangé mes habits!», et il la frappa avec le bâton qu'elle lui avait donné le soir la laissant étendue sur le sol.

፵፯ ተረት ።

፩ ሰው ፡ መንገድ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከአንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ ስለመሸበት ። ማታ ፡ ጊዜም ፡ የሚተኛበት ፡ ሥፍራ ፡ ሰጡት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፤ ከአጠገቡ ፡ ጥጃ ፡ አለች ፤ ልብስህን ፡ እንዳትበላብሕ ፡ እንካ ፡ በዚህ ፡ በላት ፡ ሳትመጣብህ ፡ ብለው ፡ ሽመል ፡ ሰጡት ። እናዚያም ፡ ባልና ፡ ምሽቶች[1] ፡ ከሰፍራቸው ፡ ተኙ ። የዚያ ፡ የባለጸጋ ፡ ምሽት ፡ ሴት ፡ ተነሳች ፤ ለባሏ ፡ ምግብ ፡ ለመመገብ ፡ ምንቸት ፡ ጽዳ ፡ አሞቀችለት ፤ በቅቤ ፡ በድልህ ፡ አድርጋ ፡ አሠለሰችለትና ፡ እሳቱን ፡ አጥፍታ ፡ ባሏን ፡ ባለቤቱ[2] ፡ ብላ ፡ ጠራችው ። ባለቤት ፡ ሳይሰማ ፡ እንግዳው ፡ ባለቤት ፡ መስሎ ፡ ቀረበ ። የባለፀጋው ፡ ምሽት ፡ ለእንግዳው ፡ በጅ ፡ በጁ ፡ ላይ ፡ እያደረገችለት ፡ እስኪጠግብ[3] ፡ በላና ፡ አስቀድሞ ፡ ወደቀደመ ፡ መኝታው ፡ ተኛ ። የባለጸጋ ፡ ምሽትም ፡ ያበላችበትን ፡ ዕቃ ፡ አጠበችና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከባሏ ፡ ዘንድ ፡ ሄደች ። ስትተኛ ፡ የእጇ ፡ እርጥበት ፡ ከረሰሰው[4] ፡ ባለጸጋም ፡ ከዕንቅልፉ ፡ ተነስቶ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤ ወደሄት ፡ ሂደሽ ፡ ኖሯል ፡ አለ ። ምነው ፡ አሁን ፡ ምግብህን ፡ ደግሸልህ ፡ በልተህ ፡ ትቀልድብኛለህ ፡ አለችው ። ማታ ፡ ከተኛሁ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ አልተነሳሁም ፡ አላት ፡ ባሏ ። ምሽቱም ፡ ያ ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ መስሎ ፡ ቀርቦ ፡ በልቶብኝ ፡ ይሆን ፡ ብላ ፡ የቅቤውን ፡ ስልስ ፡ ከአፉ ፡ ልታሸት ፡ ከእንግዳ ፡ አፍ ፡ ቀርባ ፡ ስታፈነፍን ፡ ያ ፡ ዕንግዳ ፡ ሰው ፡ ጥጃ ፡ ልብሴን ፡ በላችብኝ ፡ ብሎ ፡ ማታ ፡ በሰጠችው ፡ ሽመል ፡ ራሷን ፡ መታና ፡ ጣላት ።

XLVIII

L'HYÈNE INDISCRÈTE.

Une hyène se rendit dans un pays lointain, où l'on ne la connaissait pas, et s'étant fait tard, elle entra dans une maison et disant :

(1) Cf. M. Cohen, *Traité de langue amharique*, chap. III, 24, p. 90.

(2) Doit être une erreur du copiste pour **ባለቤቱ**

(3) **እስኪጠግብ**; le texte a **እስኪጠብ**

(4) **ረሰሰ** est ignoré de mes informateurs. Peut-être est-il lié à **ራሰ** «être humide». Ou bien faudrait-il lire **ከራሰሰው**.

«Donnez-moi un gîte pour la nuit». Un peu de temps après elle dit : «J'ai fait un long voyage et je suis fatiguée. Étendez-moi une peau afin que je puisse reposer». Les maîtres de la maison qui ne la connaissaient pas et la prenaient pour une personne comme il faut, lui étendirent une peau dans la chambre des hôtes. L'hyène, bouchée par bouchée dévora la peau entière, et pendant la nuit, avant que les gens se lèvent, elle s'en retourna d'où elle était venue.

፵፰ ተረት ።

፩ ጅብ ፡ ከሩቅ ፡ ሀገር ፡ መንገድ ፡ ሄደ ፡ ከማያውቁት ፡ ሀገር ፤ ከዚያም ፡ በመሸበት ፡ ጊዜ ፡ አሳድሩኝ ፡ አለ ፤ ከቤት ፡ ገባ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሩቅ ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ የመጣሁና ፡ ደከሞኛል ፡ አሁንም ፡ ቆርበት ፡ አንጥፉልኝና ፡ ልረፍ ፡ አለ ። ባለቤቶችም ፡ አያውቁትምና[(1)] ፡ ጨዋ ፡ ስለመሰላቸው ፡ ከእንግዳ ፡ ቤት ፡ አነጠፉለት ፡ ቆርበት ። ጅቡም ፡ ያን ፡ ቆርበት ፡ ቁርጥም ፡ ተመገበና[(2)] ፡ ሰው ፡ ሳይነሳ ፡ በሌሊት ፡ ወደቀደመ ፡ ሥፍራው ፡ ሄደ ።

XLIX

LE CHIEN GÂTÉ.

Dans un pays, il y avait un chien. Son maître l'aimait comme un fils et pour que le déjeuner et le dîner ne lui fissent pas défaut, il lui avait assigné une ration. [Le chien] lui aussi, aimait beaucoup son maître. Un jour, des chiens affamés, voyant qu'on était en train d'abattre une génisse, étaient accourus sur les lieux et le chien en question se tenait avec eux. Les chiens affamés demandèrent au chien de ce riche : «Comment vas-tu» ? — «Je vis très confortablement répondit-il. Mon maître, me donne à manger ce qu'il mange

(1) **አያውቁትምና** : le texte a **አያውትምና**

(2) **ቁርጥም ፡ ተመገበ** : noter cette forme elliptique de composé descriptif équivalente à **ቁርጥም** (**ቍርጥም** de **ቈረጠመ**) **ብሎ ፡ ተመገበ** (voir M. Cohen, *Traité*, chap. vi, p. 83 et suiv.).

lui-même; et quand je flâne, il pense à me mettre de côté ma nourriture pour mon retour».

«Nous au contraire, nous avons faim et nous n'avons rien, dirent les autres.»

Ce chien leur dit : «Je m'aperçois que vous avez soif : allons boire à la rivière et puis revenons».

«Tu parles bien, toi, mais nous, si nous voulons manger, nous devons rester ici à attendre qu'on nous donne quelque chose. Nous ne pouvons pas en prendre à notre aise, comme toi».

«C'est vrai. J'ai la vie agréable», dit le chien et tandis qu'on était en train d'abattre la génisse, il s'en alla vers le fleuve au milieu de l'envie des autres chiens.

፵፱ ተረት ።

፩ዲት ፡ ውሻ ፡ በ ፩ ድ ፡ ሀገር ፡ ነበረች ፤ ጌታዋም ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ አድርጎ ፡ ይወዳታል ፤ ራትና ፡ ምሳ ፡ አይጐደልባት ፡ ብሎ ፡ ድርጎ ፡ አ፲ጣላት ፡ እርሷም ፡ እጅግ ፡ ትወደው ፡ ነበር ። ፩ ድ ፡ ቀንም ፡ ፍሪዳ ፡ ሲወድቅ ፡ ቢያዩ ፡ የተራቡ ፡ ውሾች ፡ ተሰበሰቡ ፡ ያችም ፡ ውሻ ፡ አብራ ፡ ተቀመጠች ። የተራቡ ፡ ውሾች ፡ ያችን ፡ የባለጸጋ ፡ ውሻ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ፤ እንደምን ፡ ችኖሯያለሽ[1] ፡ አሏት ። ያችም ፡ ውሻ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ እኔን ፡ እጅግ ፡ ደልቶኛል[2] ፡ ጌታዬም ፡ ይወደኛል ፡ ከበላው ፡ ያበላኛል ፡ ወዲያም ፡ ወዲህም ፡ ብሄድ ፡ ስመለስ ፡ አስበ ፡ ያቆዩኛል ፡ አለቻቸው ። እኛስ ፡ ጠም ፡ አዳሪዎች ፡ ነን ፡ ምንም ፡ የለን ፡ አሏት ። ያችም ፡ ውሻ ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ፤ ወሀ ፡ እንደ ፡ ጠማችሁ ፡ አውቃለሁ ፡ አሁንም ፡ ከወንዝ ፡ ወሀ ፡ ጠጥተን ፡ እንምጣ ፡ አለቻቸው ። እነዚያ ፡ የተራቡ ፡ ውሾች ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አሏት ፤ እኛስ ፡ ጠብቀን ፡ ቢሰጡን ፡ እንበላለን ፡ እንዳንች ፡ መቸ ፡ ደላን ፡ ብለው ፡ ነገሯት ። ያችም ፡ ውሻ ፡ አዎን ፡ ደልቶኛል ፡ ብላ ፡ ፍሪዳ ፡ ሲወድቅ ፡ ወደወንዝ ፡ ወረደች ፡ ውሾችም ፡ ቀኑባት ።

(1) ትኖሯያለሽ ፡ *sic* pour ትኖሯለሽ ou ትኖሪአለሽ, ትኖርያለሽ

(2) ደልቶኛል de ደላ (avec suffixe) «avoir aise, commodité». Voir I. Guidi, *Supplemento al vocabolario amarico-italiano, compilato con il concorso di* F. Gallina ed E. Cerulli, Roma, Instituto per l'Oriente, 1940, col. 163.

L

LE LIÈVRE QUI VOULAIT IMITER LE LION.

Un lièvre habitait un pays où l'on ne voyait aucun autre animal. «Il n'y a pas de bête qui soit grosse comme moi et qui égale ma voix», dit-il à l'un de ses compagnons.

«C'est vrai», répondit celui-ci, parce qu'ils n'avaient rien vu d'autre.

Un jour, entendant rugir le lion, le premier lièvre dit : «Je crierai moi aussi comme lui».

«C'est bien, je resterai à vous entendre. Crie», dit son compagnon.

«Écoute-moi»; dit le lièvre et, gonflant sa poitrine, il cria.

Son compagnon lui dit : «La voix du lion est forte; la tienne au contraire, on ne l'entend pas».

Le lièvre se mit en colère et dit une seconde fois : «Reste à écouter comme je crie».

Et dans son illusion de rugir comme le lion, il se fendit en deux et mourut.

Le même sort arrive au pauvre qui rivalise avec le riche[1].

፶ ተረት ።

፩ ዲት ፡ ቂንተል ፡ ከአንድ ፡ ሀገር ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ ሳታይ ፡ ትኖራለች ፡ ለባልንጀራዋ ፡ እንዲህ ፡ አለቻት ፤ እኔን ፡ የሚያህለኝ ፡ ትልቅ ፡ አውሬ ፡ የለም ፡ በድምጽም ፡ የሚተከለኝ ፡ የለም ። አዎን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አለቻት ፤ ፪ ቱም ፡ አላዩምና ፡ ሌላ ፡ ነገር ። ቀንም ፡ አንበሳ ፡ ሲጮህ ፡ ሰምታ ፡ እኔም ፡ እንደርሱ ፡ እጮሀለሁ ፡ አለቻት ። ባልንጀራዋ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለቻት ፤ እኔ ፡ ፪ ታችሁንም ፡ እሰማለሁ ፡ ጩሂ ፡ አለቻት ። ያችም ፡ ቂንተል ፡ ስሚኝ ፤ ብላ ፡ ሆዷን ፡ ነፍታ ፡ ጮኸች ፡ ባልንጀራዋም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ ያንበሳው ፡ ድምጽ ፡ ትልቅ ፡

(1) Cette fable correspond à l'apologue d'Ésope sur la grenouille qui éclate en voulant devenir aussi grosse que le bœuf.

(2) ቂንተል = ጥንቸል *ṭĭnčal* est devenu par métathèse *č̣intal* qui est *qintal* par confusion entre *q* palatalisé et *č̣*.

ነው ፡ ያንችስ ፡ ድምፅ ፡ አይሰማም ፡ አለቻት ። ፪ ተኛ ፡ ተናደደችና ፡ ሰሚኝ ፡ ስጮህ ፡ አለች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቂንተል ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እጮህለሁ ፡ ብላ ፡ ከ፪ ት ፡ ተሰንጥቃ ፡ ሞተች ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከባለጸጋ ፡ ጋራ ፡ የሚጣላን ፡ ደሀ ፡ ይህችን ፡ ያገኜ ፡ መከራ ፡ ያገኘዋል ።

LI

LES DEUX ÉPOUX AVARES ET L'HOTE.

Dans un pays habitaient un mari et une épouse qui étaient avares et qui pour cette raison n'aimaient pas exercer l'hospitalité.

Un jour, ils avaient apprêté la table pour déjeuner. Tandis qu'ils étaient en train de se laver les mains, avant de mettre le pain sur la table, arriva un hôte qui était leur parent. Les deux époux lui dirent : « C'est regrettable que tu ne sois pas venu un peu plus tôt et que tu ne te sois pas annoncé [1]. Tu es arrivé, alors que nous avons déjà fini de manger », et se mirent à desservir la table lui faisant croire qu'ils se lavaient les mains non pas pour manger, mais après avoir mangé. L'hôte étant parti, ils réapprêtèrent la table et se mirent à manger. A ce moment-là, l'autre revint et les trouvant en train de manger il les railla en ces termes : « Quel drôle de hasard! Vous mangez donc dix fois par jour! ».

Il parla ainsi parce que (les époux) avaient dit qu'il était arrivé quand ils avaient fini de manger. Et il se mit à manger avec eux.

፶፩ ተረት ።

፪ ት ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ በ፩ ሀገር ፡ ይኖራሉ ፡ እነርሱም ፡ ንፉግ ፡ ናቸው ፡ እንግዳንም ፡ መቀበል ፡ አይሆንላቸውም ፡ ነበር ። ምሳቸውን ፡ ሊበሉ ፡ ገበታ ፡ ዘረጉ ። እንጀራ ፡ ሳይጥሉ ፡ አስቀድመው ፡ እጃቸውን ፡ ሲታጠቡ ፡ ዘመዳቸው ፡ የሆነ ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ መጣ ፤ ባለቤቶ

[1] Littéralement : Si tu l'avais fait un peu avant, si tu avais dit : « Je viendrai à telle heure ».

ችም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ ያን ፡ እንግዳ ፤ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ስመጣ ፡ ብለህ ፤ በልተን ፡ ከጨረስን ፡ በኋላ ፡ መጣህ ፡ አሉት ፤ ሊበሉ ፡ የታጸቡት ፡ በልተው ፡ የታጸቡ ፡ መስለው ፡ ባዶ ፡ ገበታ ፡ አነሱና ፡ አኖሩት ። ያ ፡ እንግዳ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ፪ ተኛ ፡ አቅርበው ፡ ሊበሉ ፡ ተመለሱና ፣ መጣ ። ሲበሉ ፡ ቢያገኛቸው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቀለደባቸው ፤ ወይ ፡ ማግኘት ፡ ከ፩ ቀን ፡ ፲ ጊዜ ፡ ትበላላችሁ ፡ አለ ። ቀድመው ፡ በልተን ፡ ከጨረስን ፡ መጣህ ፡ ብለውት ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አብሮም ፡ በላ ።

LII

LA PRÉVOYANCE CONJUGALE DU MUSULMAN.

Un musulman avait pris deux femmes, toutes deux très belles. Une de celles-ci mourut. Pendant le jour, le musulman fut très chagriné; mais le soir il prit dans son lit la seconde épouse et en plaisantant, dans sa stupidité il lui dit : «Regarde un peu ce qu'aurait combiné Allah s'il avait eu à faire avec un imbécile. C'est précisément pour cette raison que j'ai pris deux femmes».

፶፪ ተረት ።

፩ ሰው ፡ እስላም ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ፪ ት ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ሲኖር ፡ ምሽቶቹም ፡ መልካቸው ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበር ፤ ፩ ዲት ፡ ምሽቱ ፡ ታማ ፡ ሞተችበት ። ያም ፡ እስላም ፡ ቀን ፡ እጅግ ፡ አዝኖ ፡ ዋለ ፤ ማታ ፡ ግን ፡ ፪ ተኛይቱን ፡ ምሽቱን ፡ ይዞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አላህ ፡ ሞኝ ፡ ቢያገኝ ፡ ምን ፡ ባደረገ ፤ እኔም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ፪ ት ፡ ምሽት ፡ ያገባሁ ፡ ብሎ ፡ ቀለደ ፡ ስለሞኝነቱ ።

LIII

LE BEAU-PÈRE MALTRAITÉ PAR SA BRU.

Vivait dans un pays un homme qui avait épousé une femme. Il avait pris chez lui son vieux père et l'assistait. Son épouse n'aimait pas le père de son mari et l'avait en aversion. Le mari, comme cela arrive aux hommes, ne s'en apercevait pas. Elle lui donnait à manger de la mauvaise nourriture et ne lui servait jamais un plat savoureux. Elle ne lui donnait à boire pas autre chose que de l'eau fraîche. Un jour, ayant préparé de la hière, et ayant mal réussi, elle dit à son beau-père : «Papa, puis-je vous donner de la bière ?». — «Elle est mauvaise, ma fille», lui répondit son beau-père.

Comme elle ne lui avait jamais donné de bonne bière, il dit [directement] : «Elle est mauvaise».

፶፫ ተረት ።

፩ ድ ፡ ሰው ፡ በ ፩ ዲት ፡ ሀገር ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ሲኖር ፡ አረጋዊ ፡ የሸመገለ ፡ አባት ፡ ነበረው ፡ በቤቱ ፡ ይዞ ፡ ይረዳው ፡ ነበር ። ምሽቱ ፡ የባሏን ፡ አባት ፡ አትወደውም ፡ ነበር ፡ ትጠላዋለች ፤ ባሏም ፡ ወንድ ፡ ነውና ፡ አያይም ። ከምግብም ፡ የከፋውን ፡ ታበላዋለች ፡ የጣፈጠ ፡ ምግብ ፡ አቅርባለት ፡ አታውቅም ፡ የሚጠጣ ፡ ነገር ፡ ሰጥታው ፡ አታውቅም ፡ ከጥሩ ፡ ወሀ ፡ በቀር ። ፩ ቀንም ፡ ጠላ ፡ ብታደርግ ፡ መጥፎ ፡ ሆነባት ፤ ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡ የባልዋን ፡ አባት ፤ አባቴ ፡ ጠላ ፡ ልስጥዎ ፡ ብትለው ፡ ክፉዕ ፡ ልጄ ፡ አላት ። ወትሮ ፡ ከመልካሙ ፡ ጠላ ፡ ሰታው [1] ፡ አታውቅምና ፡ ክፉዕ ፡ አለ ።

LIV

L'HOMME CHARITABLE ET L'AVEUGLE.

Il y avait un homme qui craignait Dieu et honorait les hommes. Un jour, s'arrêta à sa porte un homme affamé et aveugle qui allait en

(1) ሰታው = ሰጥታው

Après cela, après avoir séjourné cette année-là, dans un autre pays, il repassa par le même chemin. Arrivé à l'endroit où il avait tué le chien, il raconta l'histoire à l'un de ses compagnons, lui disant : «Ce sont les os du chien que j'ai tué»(1). Ainsi parlant, il frappa les os de la pointe de sa lame. Ceux-ci rebondirent et frappèrent au front le meurtrier du chien qui mourut de la blessure(2).

Et c'est pour cette raison qu'on dit : «Le Seigneur qui ne laisse pas [sans vengeance] le sang d'un chien».

Et c'est le Christ qui restitue à l'humble son sang, en le vengeant.

፹ ተረት ።

፩ ሰው ፡ ውሻውን ፡ በመንገድ ፡ አገኘው ፤ ምንምንም(3) ፡ ሳይለው ፡ በጦር ፡ ወጋው ፤ ያም ፡ ውሻ ፡ ሞተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዓመቱ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ኖሮ ፡ በዚያ ፡ ጎደና ፡ ውሻውን(4) ፡ በገደለበት ፡ ሥፍራ ፡ መጣ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለወንድሙ ፡ ነገረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ይህ ፡ ውሻ ፡ እኔ ፡ የገደልሁት ፡ ውሻ ፡ አጥንት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጦር ፡ ጀንፍ ፡ ቢመታው ፡ ተፈንጥሮ ፡ የውሻውን ፡ ገዳይ ፡ ግምባሩን ፡ ወጋው ፡ አጥንቱ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያ ፡ ሰው ፤ ቆስሎ ፡ ሞተ ። የውሻ ፡ ደም ፡ የማያስቀረው ፡ ጌታ ፡ የተባለ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ የድሀውንም ፡ ሰው ፡ ደም ፡ የሚመልስለት ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ተበቅሎ ።

(1) Plus littéralement : «ce chien est le squelette d'un chien que j'ai tué».

(2) Cf. *Favole e rime galla*, récit I, p. 2-5.

(3) ምንምንም = ምንም ፡ ምንም

(4) Le texte, par erreur du scribe, porte ወሻውን

LXXXI

LE SOLDAT FANFARON.

Un soldat, tout en marchant, racontait des mensonges à l'un de ses compagnons, disant ceci, cela : «En ce lieu immortel[1], j'ai accompli un grand acte de courage».

«Qu'as-tu fait?», demanda à ces mots son compagnon.

«Tandis que j'étais en chemin avec un bouclier [si petit et si mince] qu'il ressemblait à une petite galette de cire, et avec deux petits javelots [si fins] qu'ils ressemblaient à la langue [à deux pointes] d'un serpent, les fils d'un tel m'attaquèrent pour me tuer. Je donne un coup de javelot à l'un, je le transperce; je donne un coup de javelot à un autre, je le transperce, et...»

Tandis qu'il disait : «Je le transperce et...» il se retourna et vit derrière lui un de ceux qu'il se vantait d'avoir transpercés. Son compagnon qui ne l'avait pas vu, l'invita à terminer son discours sur l'homme à propos duquel il se vantait. — «Je le transperce et...», disait-il. — «Eh bien!», lui demanda l'autre.

Et le menteur qui, au contraire, avait vu celui qui arrivait : «On fait ainsi et ainsi», dit-il; faisant semblant de terminer son discours, il l'abandonna complètement sans le conclure.

፹፩ ተረት ።

፩ ወታደር ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ የውሸት ፡ ነገር ፡ ነገረው ፡ ለባልንጀራው ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ከዚህች ፡ ካልሞተችት ፡ ሥፍራ ፡ የጅግንነት ፡ ሥራ ፡ ሠራሁባት ፡ እያለ ። ባልንጀራውም ፡ እንደምን ፡ አድርገህ ፡ ሠራህ ፡ ቢለው ፤ የሰም ፡ እንጎቻ ፡ የመሰለች ፡ ጋሻ ፡ ይዤ ፡ የዕባብ ፡ መላስ ፡ የመሰሉ ፡ ፪ ት ፡ ጦሮች ፡ ይዤ ፡ ስሄድ ፡ የእገሌ ፡ ልጆች ፡ መጡብኝ ፡ ሊገድሉኝ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ጦር ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ጦር ፡ ወጋሁና ፡ ብሎ ፡ ሲል ፤ ወጋኋቸው ፡ ብሎ ፡ ከሚፎክርባቸው ፡ ፩ን ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ ከወደኋላው ፡ አዬው ።

[1] Littéralement : «En cet endroit qui n'est pas mort», c'est-à-dire qui est resté en témoignage éternel de mes gestes.

የሚያጫውተው ፡ ወንድሙ ፡ ግን ፡ አላየምና ፡ የፈከረበትን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ሊያስጨርስ ፡ ወጋሁና ፡ ሲል ፡ እህ ፡ አለው ። ያ ፡ ዋሽ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አይቶቃልና ፡ እንዲያ ፡ እንዲያ ፡ ይደረጋል ፡ አለ ፤ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ ሳይጨርስ ፡ የጨረሰ(1) ፡ መሰሎ ።

LXXXII

COCU, MAIS ÉNERGIQUE.

Il y avait un sot. En sa présence, sa femme prit un amant. Alors il dit qu'il partait en voyage, pour surprendre l'amant. Et étant revenu de nuit, après que l'amant fut entré dans la maison, il resta à l'attendre sur la porte.

Le lendemain matin l'amant lui dit en sortant : «Comment as-tu passé la nuit ?».

«Que t'importe comment j'ai passé la nuit ?» ; lui répondit le mari sur un ton irrité.

Estimant que ces paroles seraient considérées comme une preuve d'énergie et de courage, le mari racontait l'incident à tous, en disant :

«L'amant prit ma femme et resta avec elle toute la nuit. Le matin, quand il sortit, il me demanda : «Comment as-tu passé la nuit?». Et moi : «Que t'importe comment j'ai passé la nuit ?».

Celui à qui il faisait ce récit, le railla ainsi : «Quelle audace, mon ami !». — «Pour un peu, il mourait d'épouvante !», dit le mari, qui avait pris le compliment au sérieux.

፹፪ ተረት ፡

፩ ድ ፡ ሞኝ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ሳለ ፡ ምሽቱ ፡ ሌላ ፡ ውሽማ ፡ ያዘች ፤ መንገድ ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ ተነሳ ፡ ውሽማዋን ፡ ሊያይ(2) ። ውሽማ(3) ፡ ከቤቱ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ በጨለማ ፡ መጥቶ ፡ ከቤቱ ፡ ደጅ ፡ ሲጠብቀው ፡ አደረ ። ውሽማዋም(3) ፡ ማለዳ ፡ ሲወጣ ፡ እንዴት ፡

(1) የጨረሰ = የጨረሰው
(2) Ou bien ሊያየው Le manuscrit a, par omission du copiste, ሊይ
(3) Par oubli du copiste, le manuscrit a ውሰማ.

አደርሀ ፡ አለው ፡ ውሽማ ። ባሏ ፡ ግን ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ መለሰለት ፤ እንዲሀ ፡ ብሎ ፤ ባድር ፡ ባላድር ፡ ምን ፡ ቸገረሀ ፡ አለ ። ባሏም ፡ ይሀ ነን ፡ ነገር ፡ ከወንድነት ፡ ከጅግንነት ፡ ይቈጠርልኝ ፡ ስለመሰለው ፡ ለሁሉ ፡ ይነግራል ፡ እንዲሀ ፡ እያለ ፤ ውሽማዋ ፡ ምሽቴን ፡ ይዟት ፡ አደረና ፡ ሲወጣ ፡ ማለዳ ፡ እንዴት ፡ አደርሀ ፡ ቢለኝ ፤ ባድር ፡ ባላ ድር ፡ ምን ፡ ቸገረሀ ፡ ብዬ ፡ አልሁት ፤ ቢለው ፡ ያ ፡ የነገረው ፡ ሊቀ ልድበት ፡ መደፈርሀ ፡ ወንደሜ ፡ ቢለው ፡ ሞት ፡ ይቀራል ፡ ስለፈራ ፡ አለ ፡ ባሏ ፤ እውነት ፡ ስለመሰለው ።

LXXXIII

LES OUTILS DE FER ET LES BOIS.

Les fers se réunirent et tinrent conseil, disant : «Nous taillerons les arbres et nous les détruirons». La délibération fut entendue par le manche de la lance qui avait participé à la conférence et il alla la rapporter aux bois disant : «Les haches ont décidé de vous extermi-miner».

Les arbres tinrent conseil, et tous dirent : «Si nous sommes unis qui nous touchera?». Parlant ainsi avec des fanfaronades sans bornes : «Échangeons, disent-ils, un serment réciproque».

Parmi tous les bois, il n'y en avait pas un qui fût de travers, tous étaient droits comme une barre de fer. Ils convinrent donc que la formule du serment serait : «Que celui qui, se séparant de nous, se soumettrait à l'ennemi, devienne de travers». Et ils lancèrent des imprécations en ces termes. A ces imprécations, s'associa le manche de la hache qui était le plus droit de tous.

Après cela, ils envoyèrent un espion en lui disant : «Rapporte-nous tout ce qu'il advient, toutes leurs délibérations».

Étant arrivé près des fers, l'espion les trouva dans l'embarras, parce qu'ils ne savaient quoi pas faire.

Après cela, le manche de la hache, qui était très droit, se sépara de ses compagnons et se soumit aux haches, violant ainsi son serment. En conformité avec l'imprécation qui avait été prononcée il devint immédiatement de travers. Lui aussi commença à conspirer. L'espion alla une seconde fois pour rapporter aux bois leurs délibérations et

leur dit : «Ils ne vous laisseront pas passer [tranquillement] la journée de demain. Les bois lui demandèrent : «Y a-t-il quelqu'un d'entre-nous qui soit passé du côté des fers ?». — «Oui, dit-il, il y a un de ces honteux»[1].

Les bois en furent attristés, surpris, et se virent perdus.

Le lendemain, les fers, les laissèrent tous taillés [ils les taillèrent tous].

Ainsi un homme ne met pas en déroute, avec son inimitié, une personne venue d'un pays lointain, mais l'ennemi intérieur le ruine faisant semblant d'être son ami, son partisan, son parent. En voulez-vous une preuve ? Lorsque Ménélik II vainquit l'Italie, les Italiens qui, débordant leurs frontières, étaient venus de Rome, non seulement ne s'emparèrent pas de son royaume, mais, bien qu'ils aient déchargé leurs canons et leurs fusils, ne tuèrent pas un seul de ses soldats. Ceux, au contraire, qui infligèrent de fortes pertes à son armée furent les francs-tireurs Abyssins[2].

፹፫

ብረቶች ፡ ተሰበሰቡና ፡ ምክር ፡ ያዙ ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፤ እንጨቶችን ፡ እንቁረጥና[3] ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለው ። ከዚያ ፡ ምክር ፡ ሰምቶ ፡ የጠር ፡ ዛቢያ ፡ አብሮ ፡ ሲመክር ፡ ነበረና ፡ ሄደ ፡ ነገረ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለእንጨቶች ፤ ምሳሮች ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለው ፡ መከሩባችሁ ፤ ብሎ ፡ ቢነግራቸው ፡ ዕንጨቶችም ፡ እንምክር ፡ ብለው ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሁሉም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤ እኛ ፡ ፩ ድ ፡ ከሆን[4] ፡ ማን ፡ ይነካናል ፡ እያሉ ፡ ፈከሩ ፡ እጅግም ፡ ደነፉ ፡ ያለመጠን ። ነገር ፡ ግን ፡ መሐላ ፡ እንማማል ፡ አሉ ። ከዕፀው ፡ ሁሉ ፡ ፩ እንኳን ፡ የጠመመ ፡ ዕንጨት ፡ አልነበረምና ፡ ሁሉም ፡ እንደዘንግ ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ። መሐላው ፡ እንዲህ ፡ ይሁን ፡ አሉ ፤ ከኛ ፡ ተለይቶ ፡ ለብረቶች ፡ የገባ ፡ ጠማማ ፡ ይሁን ፡ እያሉ ፡ ረገሙ ። ከሁሉ ፡ የምሳር ፡ ዛቢያ ፡ እጅግ ፡

(1) Littéralement : «il y a un cou-tordu». Dans le sens de celui qui baisse le cou par honte de ce qu'il a fait. Allusion aussi à la forme du manche du *m°sār* qui est courbe.

(2) C'est-à-dire, si je ne m'abuse, les bandes érythréennes et tigréennes qui combattaient avec les Italiens.

(3) እንቁረጥና = እንቍረጥና

(4) ከሆን = ከሆንን *ka-honn.*

የቀና ፡ ነበር ፤ አብሮ ፡ ረገመ ። ከዚህ ፡ በኋላ[1] ፡ የሚጎበኝ ፡ ሰደዱ ፤ የሆነውን ፡ የመከሩትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ሰደዱት ። ከብረቶችም ፡ ዘንድ ፡ ቢደርስ ፡ ተቸግረው ፡ የሚያደርጉትን ፡ ነገር ፡ አጥተው ፡ አገኛቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የምሳር ፡ ዛቢያ ፡ እጅግ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የቀና ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ተለይቶ ፡ መሐላውን ፡ አፍርሶ ፡ ከምሳሮች ፡ ሲገባ ፡ ጥቂት ፡ ሳይቆይ ፡ ረግመው ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ጠማማ ፡ ሆነ ። እርሱም ፡ ይመክር ፡ ጀመረ ። የዕንጨቶች ፡ ሰላይ ፡ ፪ተኛ ፡ ሄደ ፡ የመከሩትን ፡ ለዕንጨቶች ፡ ሊነግር ። ነገን ፡ አያውኋችሁም ፡ ብሎ ፡ ነገረ ። ዕንጨቶቹም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፤ ከኛ ፡ ቤት ፡ ሰው ፡ ወደብረታቶች ፡ የገባ ፡ አለ ፡ ቢሉት ፡ አዎን ፡ አለ ፡ ከአንገቱ ፡ ደፋ ፡ ያለ ፡ ነው[2] ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። አዘኑ ፡ ደነገፁ ፡ መሸነፋቸውን ፡ አወቁ ። በበነጋው ፡ ቆርጠው ፡ ጣሏቸው ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ሰውን ፡ ከዕሩቅ ፡ ሀገር ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ በጠላትነት ፡ አያሸንፈውም ፤ ከውስጡ ፡ ያለ ፡ ጠላት ፡ ወዳጅ ፡ ወገን ፡ ዘመድ ፡ መስሎ ፡ ያጠፋዋል ፡ እንጂ ። ይህም ፡ ነገር ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ኢጣልያንን ፡ ድል ፡ ያደረጉት ፡ ጊዜ ፡ ወሰናቸውን ፡ አልፈው ፡ ከሮም ፡ የመጡ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ስንኳንስ ፡ መንግሥቱን ፡ መውሰድ ፡ መድፍና ፡ ጠበንጃ ፡ ተኵሰው ፡ ከሠራዊቱ ፡ ፩ ሰው ፡ አልገደሉም ፤ የሐበሻ ፡ ጦር ፡ ባዙቅ[3] ፡ ሠራዊትዎን[4] ፡ ፈጀው ፡ እንጂ ።

LXXXIV

SEULEMENT SI DIEU LE VEUT.

Un oiseau fit son nid sur une tige de sorgho[5] et y eut des petits. Quand le sorgho donna des épis, le propriétaire vint et dit : «Il est

[1] ከዚህ ፡ በኋላ répété par erreur dans le texte.

[2] Voir Guidi, col. 693 : እንገቱን ፡ ደፋ «tenir la tête inclinée, comme qui est triste ou honteux», እንገቱ ፡ ተደፋ «se tenir les yeux baissés, etc.; être déshonorée (femme)».

[3] ባዙቅ, du turc باشي بوزوق, «soldat irrégulier», passé dans la nomenclature de l'armée égyptienne et ensuite des forces armées érythréennes.

[4] Le suffixe *-ĕwo* est ici une forme de référence polie; voir le texte n° LXIV.

[5] *zungādā* : proprement *eleusina multifera*, sorgho rouge à petits grains employé surtout pour la fabrication de la bière.

mûr à présent. Demain nous le moissonnerons». Tandis qu'il s'entendait avec ses hommes, le petit de l'oiseau l'entendit, et quand il revint [au nid] du lieu où il avait passé la journée, il dit à sa mère : «Maman, ils ont décidé et ont dit : «Nous le couperons demain». Ils veulent démolir notre maison».

«Quand ils ont décidé de le couper», ont-ils ajouté : «Si Dieu nous fait bien passer la nuit ?», demanda l'oiseau. «Ils ne l'ont pas dit», répondit le petit.

«Et alors, dit la mère, ne crains rien; elle ne sera pas démolie».

Au jour fixé pour la moisson, le fils chéri du propriétaire du sorgho mourut. Il ne vint pas et resta une semaine en deuil.

Vint la semaine suivante, il regarda le sorgho tout autour et dit : «Ce sorgho est sec. Demain, si Dieu nous fait bien passer la nuit, il sera moissonné». Et il s'en alla.

Le petit vint du lieu où il avait passé la journée et dit : «Maman, aujourd'hui, il a dit qu'on fera le fauchage demain. Notre maison sera démolie».

— A-t-il dit : «Si Dieu nous fait bien passer la nuit»?.

— Oui, il l'a dit, répondit-il.

— S'il en est ainsi, allons chercher un logement, dit l'oiseau. Et le lendemain, il s'en alla après avoir prononcé la bénédiction. «Celui qui a semé, celui qui a reproduit, que soit bénie sa vallée». Et le maître coupa le sorgho et démolit la maison de l'oiseau. Parce qu'il avait reconnu l'empire de Dieu en disant : «Si Dieu me fait passer une bonne nuit», ce qu'il avait projeté se réalisa[1].

፹፩ ተረት

፩ ዲት ፡ ያፍ ፡ ከዘንጋዳው ፡ አገዳ ፡ ላይ ፡ ጎዠ ፡ ሠርታ ፡ ወለደች ። ዘንገዳውም ፡ አሼተ[2] ፤ ባለዘንጋዳው ፡ ሰው ፡ መጣና ፤ እንግዲህ ፡ ደረሰ ፤ ነገ ፡ እንቆርጠዋለን ፡ አለና ፡ ከሰዎች ፡ ጋራ ፡ ሲመክር ፡ ሰምታ ፡ የያፍ ፡ ግልገል ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ነገረቻት ፤ ከዋለችበት ፡ ሥፍራ ፡ ስትመጣ ፡ ለናቷ ፡ ነገረቻት ፤ እናቴ ፡ ነገ ፡ እንቆርጠዋለን ፡

(1) L'oiseau qui entend que sera coupée la plante où il a son nid est un sujet des fables indiennes.

(2) አሼተ = አሸተ

ብለው ፡ ተማከሩ ፤ ቤታችነን ፡ ሊያፈርሱብን ፡ ነው ፡ አለች ። ያችም ፡ ዮፍ ፡ እንዲህ ፡ ብላ[1] ፡ ጠየቀቻች ፡ እንዲህ ፡ ብላ[1] ፤ እንቆርጠዋለን ፡ ብለው ፡ ሲማከሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደኅና ፡ ቢያሳድረን ፡ አሉ ፡ ብላ ፡ ብትጠይቃት ፤ አላሉም ፡ አለቻት ። እናቷም ፤ እንዲያውስ ፡ አይዞሽ ፡ አይፈርሱብንም ፡ ብላ ፡ ነገረቻት ። ዘንጋዳውን ፡ እቆርጠዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በተቃጠረበት ፡ ቀን ፡ የሚወደው ፡ ልጁ ፡ ሞተበት ፤ ሳይመጣ ፡ ቀረ ፤ አዝኖ ፡ ፯ት ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ። በ፰ተኛው ፡ ፯ት ፡ መጣና ፡ ዘንጋዳ ውን ፡ ዞሮ ፡ አዬና ፡ ይህ ፡ ዘንጋዳ ፡ ደረቀ ፤ ነገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደ ኅና ፡ ቢያሳድረን ፡ ይቆረጣል ፡ አለና ፡ ሄደ ። ያች ፡ የዮፍ ፡ ግልገል ፡ ፱ተኛ ፡ ከዋለችበት ፡ ስትመጣ ፡ እናቴ ፡ ዛሬም ፡ ነገ ፡ ይቆረጣል ፡ አለ ፤ ቤታችን ፡ ይፈርስብናል ፡ አለች ። እግዚአብሔር ፡ በደኅና ፡ ቢያ ሳድረን ፡ አለ ፡ ብትላት ፤ አዎን ፡ ብሏል ፡ አለቻት ። ይህን ፡ ካለ ፡ ቤታችነን ፡ እንፈልጋለን ፡ ብላ ፤ በበነጋው ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ መረ ቀች ፤ የዘራው ፡ የወለደው ፡ ወንዙ ፡ ይባረክ ፡ ብላ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄደች ። ባለ ፡ ዘንጋዳውም ፡ ቆረጠው ፡ ቤቷንም ፡ አፈረሰው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ደኅና ፡ ቢያሳድረኝ ፡ ብሎ ፡ ጌትነቱን ፡ ስለ ፡ አወቀለት ፡ ያሰበ ውም ፡ ተደረገለት ።

LXXXV

LES DEUX NONNES.

Deux nonnes cheminaient venant d'un lointain pays. L'une d'elle était jeune, l'autre était vieille. Elles rencontrèrent un berger qui était en train de garder son troupeau. Celui-ci saisit la jeune nonne, la jeta à terre et coucha avec elle.

L'autre nonne, croyant qu'il avait jeté sa compagne à terre contre sa volonté, s'approcha pour le frapper avec un bâton. Mais la nonne qui avait été prise par le berger lui dit : «Mère, il dira que vous m'avez aidée [et s'en prendra à vous]; laissez que nous vidions l'affaire entre nous deux».

Elle parla ainsi, pour ne pas perdre la seconde fois.

[1] እንዲህ ፡ ብላ est répété par une distraction du copiste.

፹፭ ተረት

፩ት ፡ ሴት ፡ መነኰሴዎች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ መንገድ ፡ ሲሄዱ ፤ ፩ ዲት ፡ መነኰሲት ፡ ሕፃን ፡ ናት ፡ ፩ ዲት ፡ መነኰሲት ፡ አሮጊት ፡ ናት ። ከብት ፡ የሚጠብቅ ፡ እረኛ ፡ አገኛቸው ፤ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ ያችን ፡ ሕፃን ፡ መነኰሲት ፡ ጣለና ፡ ይዟት ፡ ተኛ ። ፩ተኛይት ፡ መነኰሲት ፡ ግን ፡ ያለፈቃዷ ፡ ጣላት ፡ መሰሏቸው ፡ በሽመል ፡ ሊመቱት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ እረኛ ፡ የያዛት ፡ መነኰሲት ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ እማ ሆይ ፤ ረዳችብን ፡ ይልኋል ፤ ፪ታችን ፡ ይዋጣልን [1] ፡ አለች ። ሲቀራት [2] ፡ ስለሆነች ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ተናገረች ፡

LXXXVI

LE CHAT AFFAMÉ.

Il y avait un chat qui était très affamé par un long jeûne et qui ne pouvait pas se procurer sa nourriture en chassant. Un jour, il alla à l'endroit où avait été abattue une génisse et dit : «J'ai faim, donnez-moi, je vous prie, un peu de rate».

«Nous ne te donnons rien», lui répondirent ceux qui avaient abattu la génisse et ils le chassèrent.

Le chat se réfugia dans sa maison et étant là, en sûreté, il dit : «Envoyez-moi du grand muscle et du petit muscle [de la cuisse]» [3].

(1) ይዋጣ ፡ ልን ፡ de ተዋጣ ፡ de la racine ወጣ ፡
Littéralement : «Nous deux que vienne dehors à nous deux respectivement (la fin)». Ce sens n'est pas indiqué dans les dictionnaires.
Voir Guidi, col. 598. አዋጣ «aider à porter dehors».

(2) ሲቀራት ፡ parce que (avec l'intervention de sa compagne, le second tour auquel elle tenait) serait venu à lui manquer.

(3) Ce qui revient à dire qu'on est humble dans le danger et qu'on fait le fanfaron lorsqu'on est en sûreté.
tannâś et *tallâq* sont des termes techniques de boucherie.

፹፮ ተረት

፩ ድመት ፡ ነበረች ፡ ጠም ፡ አዳሪ ፤ እርሷም ፡ እጅግ ፡ ረኃብ ፡ ጸና ባት ፤ አድኖ (1) ፡ ለመብላትም ፡ አልቻለች ። ፩ ቀንም ፡ ድመት ፡ ፍሪዳ ፡ ከታረደበት ፡ ሥፍራ ፡ ሄዳ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤ እርበኛል ፤ አባካችሁ ፡ ጣፊያ ፡ ሥጋ ፡ አለች ። እለዚያም ፡ ፍሪዳ ፡ ያረዱ ፡ አንሰጥሽም ፡ አሏት ፡ ከፊታቸውም ፡ አባረሯት ። ድመትም ፡ ከቤቷ ፡ ሄደች ፡ ከዚያም ፡ ሆና ፡ አለች ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ቃኖሽና ፡ ቃላቅ ፡ ሥጋ ፡ ሰደዱ ልኝ ፡ አለች ።

LXXXVII

LES DEUX MENTEURS.

Il y avait deux hommes qui faisaient du mensonge leur capital. Unis comme la mèche et la cire [de la chandelle], ils ne disaient pas une chose qui fût vraie.

L'un d'eux dit au second, son compagnon : «Regarde, compagnon, dans cette plaine, on est en train de battre le blé avec des bœufs.»

Le second ne demanda pas : «Où ?». Il admit pour vrai qu'on était en train de battre le blé et répondit : «Les yeux me font mal».

— Comment donc ? demanda l'autre.

— Quand tu m'as fait signe et que tu m'as dit : «Dans cette plaine on bat le blé, je me suis tourné pour voir et la poussière [soulevée par le battage] m'a rempli les yeux».

Ils se turent l'un et l'autre.

Tous deux avaient le mensonge comme capital et pour cette raison ils s'étaient associés.

፹፯ተረት

፪ ት ፡ ሰዎች ፡ ሐሰትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገዋት ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ፪ ቱም ፡ ሰዎች ፡ እንደፈትል ፡ እንደሰምዕ ፡ ተስማምተው ፡ ዕውነትን ፡ ነገር ፡ ሳይጨምሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ፩ ለሁለተኛው ፡ ወን

(1) Noter le masculin : impersonnellement.

ድሙ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ እየው ፡ ወንድሜ ፡ ከዚያ ፡ ሜዳ ፡ እህል [1] ፡ ይበራያል [2] ፡ ቢለው ፤ እርሱም ፡ ወደዬት ፡ ነው ፡ ሳይል ፡ እህል ፡ መበራዩቱን ፡ አምኖ ፡ እኔንም ፡ ዓይኔን ፡ ዓመመኝ ፡ አለ ። ምን ፡ ሆንህ ፡ ቢለው ፤ ከዚያ ፡ ሜዳ ፡ ይበራያል ፡ ብለህ ፡ ያሳዩኸኝ ፡ ጊዜ ፡ በዓይኔ ፡ ምሉዕ ፡ አበቁ ፡ መላብኝ ፡ እያለው ፡ ብዬ ፡ ሬቴን ፡ እንደመ ለሰው ። ሁለቱም [3] ዝም ፡ አሉ ፤ ሁለቱም [3] ፡ ኃሰት ፡ ገንዘባቸወና ፡ ተባበሩ ።

LXXXVIII

LES HUIT FRÈRES AU TEMPS DE LA DISETTE.

Il y avait une femme qui avait huit fils. Survint une disette et ils n'avaient pas de quoi manger. Ils possédaient une vache. Au temps où ils avaient la nourriture en abondance, celle-ci donnait chaque jour quatre coupes de lait : quand la disette devint sérieuse, elle se mit à donner quotidiennement, pour ces huit personnes, huit coupes de lait avec lesquelles ils purent se nourrir et purent vivre.

Chacun de ceux-ci souhaitait dans son cœur la mort d'un d'entre eux. Avec cela, ils ne demandaient pas expressément :

« Qu'un tel meure ! » [4]. Ils disaient ceci, parce que leur nourriture était mesurée exactement et si l'un d'eux mourait ils comptaient diviser le lait entre sept personnes.

Le Christ n'oublie pas ce qui lui est dit et ne refuse pas ce qui lui est demandé. Un des frères effectivement mourut. Au lieu de pleurer son décès, ils s'en réjouirent et restèrent sept.

Mais le Christ, voyant leur méchanceté, répartit à leur désavantage le lait qui leur servait de nourriture. Ils attendirent avec impatience que le soir fût venu, pour qu'arrivât la vache.

Celle-ci finalement, lorsque le soir fut venu, arriva ; mais quand ils

(1) Le manuscrit a እህ, le copiste ayant omis ል

(2) ተበራየ se dit des céréales battues par piétinement des bœufs; voir Guidi, col. 327, Baeteman, 421.

(3) Le manuscrit avait ሁሉም... ሁሉም; le second ሁሉም seul a été corrigé ensuite en ሁለቱም

(4) Ils priaient génériquement pour la mort d'un entre eux, sans désigner individuellement la victime.

se partagèrent le lait avec la coupe habituelle, trouvèrent qu'une coupe manquait et en furent amèrement surpris.

Après cela, chacun d'eux commença à prier dans son cœur pour la vie (des autres). «Dieu, garde-nous en bonne santé, ne nous sépare pas par la mort.» Parce qu'ils avaient constaté que le lait de leur frère ne leur avait pas profité.

፻፰ ተረት ።

፩ ት ፡ ሴት ፡ ፰ ት ፡ ልጆች ፡ ነበሯት ። ረኃብ ፡ ዘመን ፡ ሆኖ ፡ የሚበሉት ፡ ምግብም ፡ አጡ ። ፩ ላም ፡ ነበረቻቸው ፤ እሀል ፡ እሀል ፡ ይበሉ ፡ የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ፱ ት ፡ ጽዋዕ ፡ ወተት ፡ ትታለብ ፡ ነበር ፤ ረኃብ ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ለ፰ ቱ ፡ ፰ ፡ ጽዋዕ ፡ ወተት ፡ በየራሳቸው ፡ ደረሳቸው ። ያን ፡ ሲመገቡ ፡ ኖሩ ። ፰ ቱም ፡ በየራሳቸው ፡ ለ፩ ዱ ፡ ሞት ፡ ተመኙ ፤ ስለተመኙ ፡ አገሌ ፡ ይሙት ፡ ብለው ፡ አለመኑም[1] ፤ እንዲሀ ፡ ማለታቸው ፡ ግን ፡ ምግባቸው ፡ ልክ ፡ ትክክል ፡ ነበር ፤ ስለዚሀ ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ወተቱን ፡ ለመከፈል ፡ ነው ፡ ከ፯ ቱ ፡ አድርገው ። ክርስቶስም ፡ የነገሩትን ፡ የማይረሳ ፤ የለመኑትን ፡ የማይነሳ ፡ ነውና ፡ ፩ ዱ ፡ ወንድማቸው ፡ ሞተ ። ስለ ፡ ልቅሶ ፡ ፈንታ ፡ ቢሞት ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ ፯ ቱ ፡ ቀሩ ፡ ልጆች ። ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ከፉታቸውን ፡ አይቶ ፡ ምግባቸውን ፡ ወተቱን ፡ ከፈለባቸው ። እነዚያም ፡ እስኪመሽ ፡ ላሚት ፡ ላሚት[2] ፡ እስክትመጣላቸው ፡ ቸከሉ ። ማታ ፡ ጊዜ ፡ መጣች ፤ አለቡና ፡ በወትሮው ፡ ጽዋዕ ፡ ወተቱን ፡ ቢካፈሉት ፡ ፩ ዱ ፡ ጹዋዕ ፡ ጐደለባቸው ። ተሰቀቁ ፤ ከዚሀ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በየራሳቸው ፡ አውን[3] ፡ በደኅንነት ፡ በሞት ፡ አትለያዮን ፡ እያሉ ፡ ይለምኑ ፡ ጀመሩ ፡ ሕይወትን ፤ የዚያ ፡ የሞተ ፡ ወንድማቸው ፡ ወተት ፡ እንዳልጠቀማቸው ፡ ቢያውቁ ።

(1) አለመኑም = *al* + *lammanu* + *m*.

(2) Ce n'est pas une diplographie mais une répétition expressive · «ils attendaient impatiemment que revienne la vache, la vache!».

(3) *Qu'est* አውን? *Peut-être* ተወን *«laisse-nous». Ou bien* አውልን de አዋለ

LXXXIX

LE DORMEUR ET L'HYÈNE.

Un homme qui voyageait ne trouva pas une maison pour s'y retirer et dormit à la belle étoile, en se servant de son bouclier comme oreiller. Survint tout doucement une hyène affamée, qui lui emporta son bouclier. Cet homme ayant peur, ne songea pas à récupérer son bouclier et lança derrière l'hyène ce bon mot : «O hyène, il n'y a pas d'animal qui rivalise avec toi[1]. Figurons-nous maintenant que tu possèdes aussi un bouclier!».

፹፱ ተረት

፩ ሰው ፡ መንገድ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የሚገባበት ፡ ቤት ፡ አጣና ፡ ከአዳሬ ፡ ጋሻውን ፡ ተንተርሶ ፡ ተኛ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጅብ ፡ መጥቶ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ራበና ፡ ጋሻውን ፡ ነጥቆ ፡ ይዘበት ፡ ሄደ ። ያም ፡ ሰው ፡ አስቀራለሁ ፡ ጋሻዬን ፡ ብሎ ፡ አላለም ፡ ስለ ፡ ፈራ ። እንዲህ ፡ አለ ፤ ጅብ ፡ ከአራዊት ፡ ሁሉ ፡ የሚተህከልህ[2] ፡ አይገኝም ፡ ነበር ፤ እንኳንስ ፡ ጋሻ[3] ፡ ጨምረህበት ፡ እያለ ፡ ቀለደ ።

XC

LE CONSEILLER DES DEUX ROIS.

Il y avait dans un pays un homme qui possédait le don de la sagesse mondaine.

Un roi et un [autre] roi se disputèrent la possession du pays; prétextant chacun qu'il était le sien. Et ils réunirent leurs troupes pour la guerre.

(1) Mieux : «il n'y avait aucun animal qui rivalisât avec toi».
(2) ተህከለ = ተከከለ ፡ ተኸከለ
(3) Le manuscrit a ጋሺ

Après cela cet homme doué de la sagesse humaine, parla aux deux rois comme suit. Il dit à l'un sans que l'autre l'entende : «Livre bataille tel jour. Tu auras de la chance. Et si tu réussis accorde-moi de la terre. Puis sans que le roi auquel il avait ainsi parlé, l'entendît, il dit à l'autre roi : «Tel jour est celui de ta fortune. Livre bataille. Tu remporteras un succès. Et tu m'accorderas de la terre». — «C'est bien», lui répondit le roi.

Les deux rois livrèrent bataille au jour qui leur avait été indiqué à tous deux comme propice. Personne n'avait vu l'homme à l'exception des deux rois. En agissant ainsi, il avait fait ce raisonnement : «Quand ils livreront bataille l'un vaincra et l'autre sera vaincu. Je n'ai pas été vu. Le vainqueur me donnera des terres».

Les deux rois livrèrent donc bataille. L'un fut vainqueur et lui accorda des terres. L'autre roi qu'il avait fait s'acharner, mourut en s'écriant : «C'est un menteur».

፺ ተረት

፩ ሰው ፡ በ፩ ሀገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ ሥጋዊ ፡ ጥበብ ፡ የተሰጠው ፡ ነው ። ንጉሥና ፡ ንጉሥ ፡ ተጣሉ ፡ በግዛት ፡ የኔ ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በሀገር ፡ ፪ቱም ፡ ሊዋጉ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ሰበሰቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የሥጋዊ ፡ ጥበብ ፡ የተሠጠው ፡ ሰው ፡ ለ፪ለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ነገረ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ። ፩ዱ ፡ ንጉሥ ፡ ሳይሰማ ፡ ለአንዱ ፡ ይህን ፡ ቀን ፡ ተዋጋ ፤ ክፍልህ (1) ፡ ነው ፡ አለው ፤ የቀናህ ፡ እንደሆን ፡ ሀገር ፡ እንደትሰጠኝ ፡ አለው ። ፪ተኛ ፡ ነገረው ፡ ንጉሥ ፡ ሳይሰማ ፡ ለ፪ተኛው ፡ ንጉሥ ፤ ይህ ፡ ቀን ፡ ክፍልህ ፡ ነው ፡ ተዋጋ ፤ ይቀናሃል ፤ ሀገር ፡ እንድትሰጠኝ ፡ አለ ። ንጉሥም ፡ ይሁን ፡ አለው ። በ፩ዲት ፡ ቀን ፡ ፪ቱን ፡ ነገሥታት ፡ ክፍላችሁ ፡ ነው ፡ ተዋጉ ፡ ባለበት ፡ ቀን ፡ ተዋጉ ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ያዩው ፡ አልነበረም ፡ ከ፪ቱ ፡ ነገሥታት ፡ በቀር ። እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ግን ፡ ከተዋጉ ፡ አንዱ ፡ ያሸንፋል ፡ ፪ተኛው ፡ ግን ፡ ይሸነፋል ፤ አያዩኝም ፤

(1) *kĕfl* a la même signification que l'arabe *naṣib*. Aussi le mot qui signifie ordinairement en amharique : «fortune», *ĕddĕl*, a étymologiquement la valeur de «portion».

ያሸነፈ ፡ ሀገር ፡ ይሠጠኛል ፡ ስለ ፡ እውቀቱ ፡ ብሎ ፡ ነው ። ተዋጉ ። ፩ዱ ፡ አሸነፈ ፤ ከዚያ ፡ ሀገርን ፡ ተቀበለ ። ያም ፡ ፪ተኛው ፡ ንጉሥ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንቀፈውም (1) ፡ ሞተ ።

XCI

LE PAYSAN ET LES PILLARDS.

Un paysan fit ainsi. S'approchant des soldats qui circulaient aux environs pour piller, au lieu de cacher son bétail et son argent il égorgea une brebis à la porte de sa maison, en répandit le sang et jeta dessus un vêtement; ensuite il dit aux pillards : «Ma femme est morte d'hémorragie en accouchant (1), aidez-moi à l'enterrer». Ainsi leur parla ce maître de maison.

Les pillards qui étaient sur le point de voler ses richesses demeurèrent désorientés et voyant le sang de la brebis et croyant aux paroles [du paysan] s'en allèrent en le laissant (en paix).

፺፩ ተረት

፩ ባላገር ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ። ዘራፊ ፡ ወታደር ፡ ቢመጣበት ፡ ከብቱን ፡ ገንዘቡን ፡ ሳይሠውረው ፡ ስለሆነ ፡ ፩ በግ ፡ ከደጃፍ (1) ፡ ከቤቱ ፡ አርዶ ፡ ደሙን ፡ ረጭቶ ፡ ልብስ ፡ አልብሶ ፡ ዘራፊዎችን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ ያ ፡ ባለቤት ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ ምሽቴ ፡ ወልዳ ፡ ደም ፡ በላት ፤ አቃብሩኝ ፡ አላቸው ። ዘራፊዎችም ፡ ገንዘቡን ፡ ሊዘርፉት ፡ የነበሩ ፡ ደንግፀው ፡ ሄዱ ፡ ትተውት ፤ የበጉን ፡ ደም ፡ አይተው ፡ የነገራቸውን ፡ አምነው ።

(1) *Sic.* Corriger en እነቀፈውም

(2) *dam ballât,* littéralement : «le sang, il l'a mangée». Ce récit se trouve avec des détails plus importants en un style plus alerte dans E. Mittwoch, *Abessinische Erzählungen und Fabeln,* Berlin, Reichsdruckerei, 1911, p. 8-9, texte III.

(3) Le manuscrit a ከጃፍ

XCII

L'ÉCRIVAIN ET LE SINGE.

Dans un pays habitait un *dabtarā* qui faisait le scribe. Tandis qu'il était en train d'écrire, un singe se mit à l'observer de loin, en attendant qu'il s'en aille. Quand il fut fatigué, l'écrivain se leva pour aller se reposer, laissant là le manuscrit et l'encrier[1]. Le singe voulut écrire comme lui et barbouilla le parchemin d'encre, le rendant inutilisable. L'écrivain entra dans une terrible colère et pensa à le tuer. Ayant aiguisé un couteau en présence du singe, il en passa le tranchant sur la peau de sa nuque, faisant semblant de se couper le cou; puis il l'affila de nouveau, le laissa là et s'en alla.

Selon ses habitudes, le singe fit comme il l'avait vu faire par l'écrivain et se trancha le cou avec la lame.

Quand l'écrivain revint, il le trouva mort; il l'avait tué avec son ingéniosité personnelle.

፺፪ ተረት

፩ ጸሐፊ ፡ ደብተራ ፡ በ፩ ሀገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ እርሱንም ፡ ሲጽፍ ፡ ፩ ዺት ፡ ጦጣ ፡ አይታ ፡ እስኪሄድላት ፡ ርቃ ፡ ትጠብቀዋለች ። ያም ፡ ጸሐፊ ፡ በደከመው ፡ ጊዜ ፡ ለመናፈስ ፡ ተነሳ ፡ መጽሐፉን ፡ ቀለም ፡ ቀንዱን ፡ ትቶ ። እርሷም ፡ እንደርሱ ፡ እጽፋለሁ ፡ ብላ ፡ ብራናውን ፡ ቀለም ፡ ቀባችው ፡ አጠፋችበት ። ጸሐፊውም ፡ ተናደደ ፡ ለመግደልም ፡ አሰባት ። ቢላዋ ፡ ስሎ ፡ ከጦጣዋ ፡ ፊት ፡ ሆኖ ፡ በደንደሱ ፡ ስለቱን ፡ አዙሮ ፡ አንገቱን ፡ ገዘገዘና[2] ፡ ዳግመኛ ፡ ስሎ ፡ ጥሎላት ፡ ሄደ ። እርሷም ፡ እንደለመደች ፡ ጸሐፊውን ፡ እንዳየች ፡ በሥለቱ ፡ አንገቷን ፡ በጠሰችው ። ጸጠፊውም ፡ ቢመለስ ፡ ከዚው ፡ ሞታ ፡ አገኛት ፤ በጥበቡ ፡ ገደላት ።

(1) *qand :* «corne qui sert d'encrier». L'histoire est très connue en Europe.

(2) Le manuscrit a ገዘገና

XCIII

LA PERFIDIE DE L'ESCLAVE.

Deux hommes se rencontrèrent, tandis qu'ils allaient au marché. L'un d'eux dit : «Je vais vendre ma mule, parce qu'elle rue et je cours ainsi le risque qu'elle me tue des gens». L'autre dit : «Mon esclave est si médisant qu'il suscitera des meurtres. C'est pourquoi je vais le vendre».

«Faisons l'échange», proposa le propriétaire de la mule au maître de l'esclave.

«Accepté. Accepté.» Ils firent l'échange et chacun d'eux s'en retourna chez lui.

En faisant entrer la mule dans la maison, le maître reçut une ruade qui le tua.

Quant au maître de l'esclave il avertit ses familiers en ces termes : «Cet esclave est une mauvaise langue. Ne l'écoutez pas.»

Ainsi son épouse et tous les gens de la maison surent à qui ils avaient à faire et les méchancetés de l'esclave n'eurent pas de conséquences.

Un jour l'esclave demeura seul auprès du brasero : «Moi, je l'éteindrai, le feu !», dit-il.

Les maîtres de la maison, après que leur lit eut été préparé, étaient allés dormir.

Il prit de l'eau, la fit chauffer et en versa sur le lit au beau milieu entre le patron et la patronne. Ceux-ci s'éveillèrent et trouvèrent le drap humide. Le patron accusa sa femme. Celle-ci crut que son mari avait uriné dans le lit. Ils s'accusèrent l'un l'autre. Ils secouèrent le drap.

Le lendemain, le maître se rendit au champ pour présider aux semailles. La semence étant venue à manquer, il dit à son esclave : «Va en prendre à la maison». Le maître avait rassemblé les femmes autour de lui et était en train de surveiller leur travail. Et alors l'esclave lança cette calomnie : «Le maître, dit-il à sa patronne, a ri de vous avec les paysans». — «Qu'a-t-il dit ?» demanda-t-elle.

Et ce calomniateur qui connaissait bien ce qu'il avait combiné, dit : «Il a dit : aujourd'hui, ma femme a uriné au lit».

La patronne fut stupéfaite, elle entra en fureur, impatiente de demander des explications à son mari.

En attendant, ce semeur de discordes ayant pris de la semence était retourné auprès de son patron. — «Pourquoi as-tu tardé?», lui demanda celui-ci.

«Madame avait réuni toutes les femmes et leur racontait que vous aviez uriné dans le lit. Tout le monde riait. Je voulais m'en aller mais elles m'ont dit : «Reste» et m'ont ainsi retardé.»

Le mari fut très étonné et demeura très peiné. Le soir, il rentra chez lui. Le dîner était prêt. Son épouse lui dit : «Je ne mange pas avec toi». Le mari entra dans une violente fureur. «Pendant le jour, elle n'a fait que rire de moi et maintenant elle me dit qu'elle ne veut pas manger avec moi. Et je devrais me taire?». Il pensa ainsi et ayant pris un bâton, il l'assomma. Puis il dit à l'esclave : «Émigrons : toi, occupe-toi de conduire le bétail». L'esclave alla chez le frère de la femme et lui dit : «Il a tué ta sœur». Le frère accourut, empoigna le meurtrier et le tua. Et ainsi [l'esclave] les conduisit tous deux à la mort.

Après cela, il dit : «Puisque mon maître et ma maîtresse sont morts, je me retirerai dans un couvent». Ayant creusé une fosse dans sa propre cabane, il dit aux moines : «Je vais vous enseigner à faire des miracles». Ceux-ci croyant qu'il disait la vérité, lui dirent : «Fais-nous voir». Il ferma la maison et de l'intérieur il y mit le feu et descendit ensuite dans la fosse qu'il avait creusée.

Quand l'incendie de la maison eut pris fin et que les cendres se furent refroidies, il sortit de là. Ceux-ci furent ébahis et dirent : «Fais-nous voir comment tu as fait». C'est bien répondit-il et il fit périr dans les flammes à l'intérieur de la maison les moines d'un pays entier, sans qu'un seul en échappât. Il resta ainsi l'unique occupant du couvent.

፺፫ ተረት

፪ ሰዎች ፡ ወደገቢያ ፡ ሲሄዱ ፡ ተገናኙ ። ፩ እንዲህ ፡ አለ ፤ በቅሎየ ፡ እየተራገጠች ፡ ሰው ፡ ልትገድልብኝ ፡ ቢሆን ፡ እርሷን ፡ እሸጣለሁ ፡ ብየ ፡ ነው ፡ አለ ። ፪ ተኛው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኔም ፡ ባር ያዬ ፡ አሳባቂ ፡ ሆነብኝ ፡ ነፍስ ፡ የሚያስገድል ፡ ሆነብኝ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ልሸጠው ፡ ነው ፡ አለ ። ባለበቅሎም ፡ ባለባሬውን ፡ ለውጠኝ ፡ አለ ። ይሁን ፡ ይሁን ፡ ተባብለው ፡ ተለዋወጡ ። ሁሉም ፡ በየቤታ

ቸው ፡ ተመለሱ ። ባለበቅሎውን ፡ አስገባለሁ ፡ ከቤት ፡ ብሎ ፡ ረግጣ ፡ ገደለችው[1] ። የባጀ ፡ ጌታም ፡ ለቤተ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ፤ ይህ ፡ ባርያ ፡ አሳባቂ ፡ ነውና ፡ ነገሩን ፡ አትስሙት ፡ አለ ። ምሽቱም ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ አወቁበት ፡ ያም ፡ ባርያ ፡ ሰብቅኛ ፡ አልመቸው ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታቱ ፡ ፩ቀን ፡ ከማንደጃው ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ። እኔ ፡ እደፍነዋለሁ ፡ እሳቱን ፡ አለ ። ባለቤቶቹ ፡ አንጥፈው ፡ ተኙ ፤ እርሱም ፡ ወሀውን ፡ አሞቀና ፡ በጌታውና ፡ በመቤቱ ፡ መካከል ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰው ። ቢነሱ ፡ ምንጣፉ ፡ ርሶ ፡ አገኙት ። ጌታው ፡ ምሽቱን ፡ አማ ፤ ምሽቱ ፡ ጌታውን ፡ ባሏን ፡ ሼነ ፡ መሰላትና ፡ ተማሙ ። ምንጣፉን ፡ አራገፉ ። በበነጋው ፡ ጌታው ፡ ከርሻው ፡ ሊያሳርስ ፡ ሔደ ። ሀር ፡ አለቀና ፡ ከቤት ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ። እመቤቱም ፡ ሴቶችን ፡ ሰብስባ ፡ ስታሰራ ፡ ባርያው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አሳበቀ ፡ ለመቤቱ ፤ ጌታ ፡ ከገባሬዎች ፡ ጋራ ፡ ሳቁብዎ ፡ አላት ። ምን ፡ ብሎ ፡ አለችው ። ያም ፡ ሰብቀኛ ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ ያውቃልና ፡ ዛሬስ ፡ ምሽቴ ፡ ሸነችብኝ ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ እያለ ፡ ነው ፡ አላት ። እመቤቱም ፡ ደነገጠች ፡ እጅግም ፡ ተናደደች ፡ በኋንም ፡ ለመጠየቅ ፡ ቸከለች ። ያ ፡ ሰብቀኛም ፡ ዘርእ ፡ ይዞ ፡ ከጌታው ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ምነው ፡ ቆየሀ ፡ ቢለው ፤ ሴቱ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበ ፡ እመይቴ ፡ እርስዎን ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ሸኑ ፡ እያሉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይስቃል ። ልሂድ ፡ ብየ ፡ ብል ፡ ቆይ ፡ እያሉ ፡ አቆዩኝ ፡ አለው ። ባሏም ፡ ደነገጠ ፤ እጅግ ፡ አዘነ ። ማታም ፡ ከቤት ፡ ሄደ ። ራት ፡ ቀረበ ። አልበላም ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ ተናደደ ። ቀን ፡ ስትሰቅብኝ ፡ ዋለች ፤ አሁን ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ አልበላም ፡ አለችኝ ፤ እኔ ፡ ዝም ፡ ብላት ፡ ብሎ ፡ በሽመል ፡ መጥቶ ፡ ገደላት ። ያን ፡ ባርያ ፤ እንስደድ ፤ ከብት ፡ ንዳ ፡ ቢለው ፡ ሄደ ፤ ለወንድሟ ፡ እትሀን ፡ ገደላት ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። መጥቶ ፡ ያዘው ፡ ገደለው ። ፪ቱንም ፡ አስፈጃቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገዳም ፡ እሄዳለሁ ፡ እመቤቴም ፡ ጌታዬም ፡ ከሞቱብኝ ፡ ብሎ ፡ ከቤቱ ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፡ መነከሳትን ፡ ጽድቅ ፡ ላስተምራችሁ ፡ አለቸው ። እለዚያም ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ሰለመሰላቸው ፡ አሳዩን ፡ አሉ ። እርሱም ፡ ቤቱን ፡ ዘግቶ ፡ ከውስጥ ፡ ሆኖ ፡ አቃጠለው[2] ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከማሰው ፡ ጉድጓድ ፡ ገባ ፤ ቤቱ ፡ ተቃጥሎ ፡ ከበረደ ፡ በኋላ ፡

(1) Le manuscrit a ገደችው

(2) Le manuscrit a አቀጠለው

ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ወጣ ። እለዚያም ፡ አደነቁ ፤ እኛንም ፡ እንዳንተ ፡ አድርገን ፡ አሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ከቤት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፡ የ፩ ድ ፡ አገር ፡ መነከሳቱን ፡ ከቃጠላቸው ፤ ገዳሙን ፡ ይዞ ፡ ቀረ ።

XCIV

PAROLES ADRESSÉES À DIEU PAR UN AFFAMÉ.

Un homme, parce que le Seigneur l'avait fait passer d'une dure période à une époque de disette, dit à Dieu ceci :

Vers.

1er Sens.

Tu es bon de faire passer d'une époque à l'autre
Mais tu ne donnes rien, parce que tu ne veux pas!
Oh ! qu'est ceci ? Pourquoi m'as-tu laissé sans rien ?
Tu m'as fait arriver à la faim.

2e Sens.

Tu es bon de servir à table.
Mais tu ne me donnes pas de ta bière !
Oh ! qu'est ceci ? Pourquoi m'as-tu laissé sans rien,
Du moment que mon tour était arrivé ?

፺፬ ተረት ፡

፩ ሰው ፡ ከክፉ ፡ ቀን ፡ ከረኃብ ፡ ዘመን ፡ ጌታ ፡ ስላደረሰው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔርን ።

(1) Ce sont des vers à double sens, comme on en trouve souvent dans la poésie amharique. Dans le premier sens, il reproche à Dieu de l'avoir sauvé ; mais de l'avoir fait tomber de Charybde en Scylla, en le faisant échapper à une situation difficile pour le mettre aux prises avec la faim. Dans le second, il le compare à un serviteur qui, en passant la bière à table, saute un invité dont le tour est arrivé.

ማሳለፉንስ[1] ፡ ታውቃለሀ ።
አትሰጥም ፡ እንጅ ፡ ተጠላሀ[2] ።
ምነዋ[3] ፡ ለምን ፡ ነማሀኝ ።
ተሬ ፡ ባደረስኸኝ[4] ።

XCV

LES DEUX ESCLAVES.

Il y avait deux esclaves qui étaient au service du même maître. L'un des deux avait fait le projet de s'enfuir. Les deux serviteurs dormaient auprès de leur maître. Une contestation éclata alors entre eux au sujet de la place [qu'ils devaient occuper]. Le serviteur qui pensait s'enfuir dit : «Peu m'importe, puisqu'il s'agit d'un seul jour». Entendant ces mots le maître lui dit : «Et où vas-tu demain ?».

Le serviteur réfléchit un peu et lui répondit : «Je reprendrai demain mon ancienne place». Le maître croyant qu'il disait la vérité ne pensa ni à l'attacher ni à le punir, et le lendemain l'esclave s'enfuit, exactement comme il l'avait dit la veille au soir. Le maître se mit en colère [contre lui-même] : «Il me l'avait dit, et je me suis tû»[5].

፺፭ ተረት ።

፪ት ፡ ባሮች ፡ በ፩ ጌታ ፡ ገብተው ፡ ሲኖሩ ፡ ፩ዱ ፡ መከዳት ፡ ይፈልገዋል ፤ የ፪ቱም ፡ አሽከሮች ፡ መኝታቸው ፡ ከጌታቸው ፡ አጠገብ ፡ ነበር ። ፪ቱም ፡ በሥፍራ ፡ ተጣሉ ። ያ ፡ መከዳት ፡ የፈለገው ፡ አሽ

(1) አሳለፈ a ici la double signification de : «faire passer (d'une époque à l'autre)» et de : «servir à table».

(2) ተጠላሀ veut dire : «puisque tu as haï (tu refuses, tu ne veux pas)» et «de ta bière».

(3) ምነዋ = ምን ፡ ነው ፡ አ (አ interjection de surprise).

(4) Double lecture : ተሬብ ፡ አደረስኸኝ et ተሬ ፡ ባደረስኸኝ ። والله أعلم.

(5) Le maître avait compris que l'esclave voulait reprendre son ancienne place pour dormir. L'esclave au contraire, avait l'intention de lui dire qu'il retournerait dans son pays.

ከር ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ለ፩ ቀን ፡ አዳር ። ይሆን ፡ ሰምቶ ፡ ጌታው ፡ ነገ ፡ ሄት ፡ ትሄዳለህ ፡ ቢለው ፡ ጠንቅቆ ፡ መለሰለት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ነገማ ፡ ቀድሜ ፡ ሥፍራዬን ፡ እይዛለሁ ፡ አለ ። ጌታውም ፤ እውነት ፡ ነገር ፡ ስለመሰለው ፤ ልሰረው ፡ ልቀጣው ፡ አላለም ። ያም ፡ ባርያ ፡ ማታ ፡ ለ፩ ፡ ቀን ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ከዳ ። ጌታውም ፡ ሲነግረኝ ፡ ዝም ፡ አልሁ ፡ ብሎ ፡ ተናደደ ።

XCVI

LA SERVANTE BRULÉE AU SEXE.

Dans un pays habitait un homme qui, ayant abandonné son épouse, avait pris sa servante pour la traiter comme telle.

L'épouse précédente, rongée par le ressentiment et par la jalousie, attacha la servante et lui brûla les parties sexuelles avec le feu.

Un parent de la servante alla chez le juge réclamer une indemnité. «Elle a fait comme ceci, comme cela, dit-il, et elle l'a brûlée avec le feu, et maintenant l'autre est sur le point de mourir.» Un bel esprit lui demanda : «Dis-moi, ami, le feu l'a-t-il brûlée aussi bien à droite qu'à gauche?».

«Oui, répondit le parent de la servante». Le bel esprit le railla en disant : «Le feu n'aurait jamais pu traverser une vallée»[1].

፺፮ ተረት ።

፩ ሰው ፡ በ፩ ሀገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ ምሽቱን ፡ ትቶ ፡ ገረዱን ፡ ያዘ ፡ እንደምሽት ፡ አድርጎ ። የቀደመች ፡ ምሽቱም ፡ ቀንታ ፡ ተመቅኝታ[2] ፡ ያችን ፡ ገረድ ፡ አሥራ ፡ ሀፍረቷን ፡ አቃጠለቻት ፡ በእ

(1) Traduction incertaine. Il fait probablement allusion à la largeur de la vulve de la servante et dit que le feu n'aurait jamais pu traverser une vallée semblable d'une extrémité à l'autre.

(2) Noter l'hendyadys.

ላት ። ወገንዋ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ተካሰና [1] ፡ ከዳኛ ፡ ሄደ ፤ እንዲህ ፡ አድርጋ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለቻት ፡ አሁንም ፡ ልትሞት ፡ ሆነ ፡ ነገረው ። አንድ ፡ ተረበኛ ፡ ሰው ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፤ በልንጅ [2] ፡ ወንድሜ ፡ እሳቱ ፡ ግራኝ ፡ ቀኙን ፡ ፈጀው ፡ ብሎ ። የዚያች ፡ ገረድ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አዎን ፡ አለው ። ያም ፡ ተረበኛ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ወትሮ ፡ እሳት ፡ ሸጥ [3] ፡ አይሻገርም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ቀለደበት ።

XCVII

LE VERBE S'EST FAIT CHAIR.

Un Seigneur, se tenant-dans le pavillon de réception, passa la journée en donnant à manger et à boire [à ses invités].

A la fin, il distribua peu de viande à la population [qui se tenait dehors]. Le maître, cependant les fatigua à force de dire qu'il avait distribué beaucoup de viande.

Alors un homme le railla en ces termes : «Puisque la viande était en petite quantité, la Parole s'est faite chair» [4].

Le maître en éprouva une grande colère.

፺፯ ተረት

አንድ ፡ ጌታ ፡ በአደራሽ ፡ ተገኝቶ ፡ ሲያበላ ፡ ሲያጠጣ ፡ ዋለ ። ኋላም ፡ ጥቂት ፡ ሥጋ ፡ አቀረበ ፡ ለሕዝቡ ። ባለቤት [5] ፡ ግን ፡ ብዙ ፡

(1) ተካሰ veut dire : «recevoir une indemnité». Ici a évidemment la valeur de : «demander une indemnité». Ou bien ተካሰሰ se plaignit.

(3) በልንጅ = በል ፡ እንጂ

(4) Les indigènes que j'ai consultés ignoraient le mot ሸጥ. Le *Supplemento al vocabolario amarico-italiano* de I. Guidi, G. Gallina et E. Cerulli (Rome, 1940), lui donne, sur l'autorité de Afeworq, la valeur de : «vallée, bande de terrain».

(4) Allusion à l'Incarnation du Christ, le Verbe de Dieu.

(6) Les deux ባለቤት représentent une répétition faite par inadvertance, bien que le premier soit sujet de አደከማቸው et le second de አቀረበ.

ሥጋ ፡ እንዳቀረበ ፡ ባለቤት ፡ ብሎ ፡ ብሎ[1] ፡ እያለ ፡ አደከማቸው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ቀለደበት ፤ ሥጋ ፡ ሰላነሰ[2] ። ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ[3] ፡ አለ ። ባለቤትም ፡ ተናደደ ።

XCVIII

LE FITAORARI-BALAMBARAS.

Un homme ayant été nommé Fitaorari continua d'être appelé Balambaras. Se sentant humilié, il composa ces vers :

«Rends-moi témoignage», me dit-il pour palper ma voix [ou parole].

Suis-je vraiment l'homme que j'étais ?[4].

፺፰ ተረት ።

፩ ሰው ፡ ተሾሞ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባላምባራስ ፡ ሲባል ፡ ኖረ ። ኋላ ፡ ስለ ፡ ተዋረደ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገጠመ ።

መስክርልኝ ፡ አለኝ ፡ ቃሌን ፡ ሊዳስሰው ።
እውን ፡ እኔ ፡ ነኞይ[5] ፡ የነበርሁት ፡ ሰው ።

(1) Ici, la répétition ብሎ ፡ ብሎ a une fonction expressive.

(2) Le manuscrit a ሰላነሰ

(3) En ge'ez. «Verbum caro factum est.» Peut-être serait-il mieux de dire pour la rime :

ሥጋ ፡ ሰላነሰ
ቃል ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ
«Le Verbe s'est revêtu de chair».

Mais ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ correspond mieux au texte de l'Évangile et à l'intention satirique, puisque le maître de maison donne des paroles au lieu de viande.

(4) Les Éthiopiens que j'ai consultés sur la signification de ce dystique m'ont déclaré qu'ils ne réussissaient pas à en venir à bout.

Peut-être s'agit-il de quelqu'un qui, invité par d'autres à prouver son identité en faisant entendre sa voix, doute lui-même de cette identité, c'est pourquoi le Fitaorari se demanderait : «Suis-je la personne qui a été nommée Fitaorari ou une autre, du moment qu'ils me donnent encore le titre inférieur de Balambaras? Dans ce cas «palper» signifierait «explorer».

(5) ነኞይ = ነኝ ፡ ወይ

XCIX

L'HOMME QUI A ACHETÉ UN ANE.

Un homme dit : «J'irai au marché». Tandis qu'il se préparait : prout ! il lui échappa un pet. Sa femme l'entendit, mais resta silencieuse.

Il alla au marché et n'ayant pas trouvé la marchandise qu'il cherchait, il acheta un âne et rentra avec lui à la maison.

Sa femme le railla en ces termes : «Depuis ce matin, je savais, moi aussi, que tu aurais acheté un âne».

፺፱ ተረት

አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ገቢያ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲታጠቅ ፡ ዛጥ[1] ፡ አድርጎ ፡ ፈሳ ፤ ምሽቱም ፡ ሰምታ ፡ ዝም ፡ አለች ። ገቢያ ፡ ሄደም ፡ የሄደበትን ፡ ገቢያ ፡ አጥቶ ፡ አህያ ፡ ገዝቶ ፡ መጣ ። ምሽቱም ፡ ቀለደ ችበት ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፤ አህያ ፡ እንድትገዛ ፡ እኔም ፡ ጧት ፡ አወቄዋ ለሁ ፡ አለች ።

C

L'HABITANTE STUPIDE DU BAS PAYS.

Une femme habitait dans le bas pays. Elle monta un jour sur le haut plateau. En chemin, elle rencontra un jeune homme qui lui demanda :

«Comment vas-tu ?».

«Comment me connais-tu ?», lui demanda l'habitante du bas pays.

«Je te connais», lui répondit-il.

«Si tu me connais, appelle-moi ainsi», répliqua celle-ci, et elle lui dit son nom.

(1) ዛጥ ፡ አደረገ, onomatopéique, comme ጧጥ ፡ አደረገ, manque dans les dictionnaires.

Et celui-ci l'appela du nom qu'elle lui avait dit.

Dans le bas pays, la bêtise n'est pas rare. «Regarde, il me connaît donc!», s'écria la femme dans sa stupidité.

፻ ተረት ፡

፩ ዲት ፡ ሴት ፡ በቆላ ፡ ትኖር ፡ ነበር ፤ ከዕለታቱ ፡ ፩ ቀን ፡ ወደ ፡ ደጋ ፡ ወጣች ፤ ከዚያም ፡ በመንገድ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ አገኛት ፤ እር ሱም ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ ቢላት ፤ ያች ፡ ቆለኛም ፡ የት ፡ ታውቀኛ ለህ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ አውቅሻለሁ ፡ አላት ። እርሷም ፡ ስሜን ፡ ነግሬ ፡ እስኪ ፡ ታወቅኸኝ ፡ እገሌት ፡ በለኝ ፡ አለችው ። እንደ ፡ ነገ ረችው ፡ ጠራት ። ከቆላ ፡ በታ ፡ ሞኝነት ፡ አይታጣምና ፡ እረግ ፡ ያውቀ ኛል ፡ አለች ፡ ስለ ፡ ሞኝነቷ ።

TABLE DES MATIÈRES.